ሰንደቅ

ዘአርቶዶክስ ተዋሕዶ

ነሐሴ - 1988 ዓ.ም

4ኛ ዓመት ቁጥር 2

‘አንቲ ውእቱ ተስፋሁ ለአዳም አመይለደድ
እምነነት – ከገነት በተሰደደ ጊዜ የአዳም
ተስፋው አንቺ ነሽ ።’

ስጦታ ናት

የሐ.19፡27
ክፍርትነቷ ቁ፩
ለተወዳጅ ደቀመዝሙር
እምነት ይዞ ለተጓዘ
በክህደት ባሕር ሰጥሞ
ባለማመን ላልፈዘዘ
የፍትርን ሰንሰለት ታጥቆ
ቀራንዮ ሜዳ ለተገኘ
ሕይወቱን ከሰጠው ጌታ
በረከቱን ለተመኘ
የጌታውን ቃል ለሰማ
የመስቀል ላይ አደራውን
ሲሰጠው ለተቀበለ
ለጠበቀ የያዘውን
ድንግል ማርያም ስጦታ ናት
ለታደለ በሕይወቱ
እምላክ ላከበረው ትውልድ
ላደለው ከበረከቱ
በእርግጥ–ድንግል ስጦታ ናት
የጥንት ናት የጠዋቱ
በምንም የማትለወጥ
የመድኀኒዓለም ርስቱ።
መስቀሉት ለእግዚአብሔር

የካቲት ፲፮ ቀን
አመቢታችን ቃልኪዳን የተቀበለችበት ዕለት።

©ማኅበረ ቅዱሳን

ከአንባብያን ለአንባብያን

ሥነ ግጥም

እኛም ይሁዳን ነን
አምላክን በጉብ በጥቅም ከሸጥነው፣
ለጊዜያዊ ተድላ ብለን ክለወጥነው፣
እንደ አምላክነቱ ክብር ካልሰጠነው።
ከእግዚአብሔር ከለረትን፣
አሥራቱን ከበላን፣
ለልጅነት ክብር በጥምቀቱ ጠርቶን፣
መስቀሌን ይዛችሁ ተከተሉኝ ሲለን፣
ጥቅግጥቅሙ ስበን ወደኋላ ከሠርን፣
ከሃዲው ይሁዳን ለምን እንነትፋለን
ሰዎች እናስተውል...
ይሁዳም እኛን ነው እኛም ይሁዳን ነን።

(መ/ር ዓለምቀረ ሙሉ – ነገሌ ቦረና)

የቀደመውን ባንተው!

በዜተክርስቲያናችን ከዚህ በፊት ያልነበረ አዲስ የጸሎት ሥርዓት እየተለመደ መጥቷል። ይኸውም አንዳንድ ሰዎች ጌታ ያላደረገውን፣ በቅዱስ መጽሐፍ ያልተጻፈ ውን፣ አበው ያላስተማሩትን በመከተል ዓይን ዉፍኖ መጸለይን መልመዳቸው ነው። ይህ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ያልሆነ ሥርዓት ነውና ብንተወው መልካም ነው።

(የግታው አበባው – አዲስ አበባ)

በጊዜውና እንደአቅም ቢሆን

ነና በወላጆቻቸው አስተዳደር ሥር ያሉ አንዳንድ የሰንበት ት/ቤት ወጣቶች ሥስትና አራት የጽዋ ማኅበራት ውስጥ እየገቡ በቶክክር ያለ አትግቸው ወላጆቻቸውን በድግስ አያ ስመረሩና ብአላስፈላጊ ወጪም እየዳረጓቸው ነው። በጽዋ ማኅበር ተሰብስቦ መዘከሩ የተ ቀደሰ ተግባር ቢሆንም በጊዜውና እንደ አትም ቢሆን መልካም ነው። አለበለዚያ በጻድት ስም ተሰባስቦ ወላጆችን ምሬት ላይ መጣል ለይ ያመጣልና ቢታሰብበት መልካም ነው።

በሌላ በኩል ደግሞ በዜተሰባቸው ሜንታ ላይ ሳሉ ሲደግሱና ዘውትር ከዜተ ክርስቲያን አይጠፉ የነበሩት እነዚሁ ወጣቶች ራሳቸውን ችለው ጉጆ ከወጡ በኋላ ግን ነገር ዓለሙን መተዋቸው ስላሳሰበኝ ‹እንዴት ነው?› ለግለት ደረጡ።

(ጻ/ዜለቀ ረጂ – ሊሙ ገነት)

ንስሐ ሳይገቡ ቁርባን?

ባለፈው ታኅሣሥ ወር 1988 ዓ.ም ለሥራ ጉዳይ ወደ ምዕራብ ወለጋ መንዲ ከተማ ተጉዤ ያጋጠመኝ ነገር በጣም አስደን ግሮኛል። ታለ እግዚአብሔር ያልገባቸው አንዳንድ ምዕመናን ቅዱስ ቁርባንን «የጌታ ራት» (ሉቱ ስብሐት) በግለት በድፍረት ይቀበላሉ። መቀበላቸው ባልከፋ ነገር ግን የሚገባውን ክብር በመስጠት ዓላግው ንብቷቸውና ንስሐ ንብተው መሆን ነበረበት። አምኖበት በፍርሃትና በትሕትና ለሚቀበለው አባ ሕርያቆስም እንዳለው የሚያድን እሳት ነው፣ በድፍረትና በትዕቢት ሳይገባው ለሚቀበለው ደግሞ የሚበላ እሳት ነው። ይኼ የመናፍቃኑ ሥነ ልቡናዊ ተፅዕኖ ያመጣው ነገር ነው። ምዕመናን የንስሐ አባት ይዘው ንስሐ ንብተው፣ በጾም በጸሎት በስግደትም ራሳቸውን ገዝተው ወደዚህ መለኮታዊ ምሥጢር እንዲቀርቡ አንድ በሏቸው።

(ንብረ ኢየሱስ – አዲስ አበባ)

ወረተኞች አንሁን

በብዙ ሰንበት ትምህርት ቤቶች ስዘየወር የታዘብኩት አንድ ነገር አለ። ይኸውም አዳዲስ መዝሙሮችን ብቻ የመዘመር ወረት ነው። አዳዲስ መዝሙሮች የወጡ ሰሞን የቀድሞዎቹ ሙሉ በሙሉ ይረሱና አዳዲሶቹ ብቻ ይዘመራሉ። እነርሱም ወረታቸው እስኪያልፍ። በተጨማሪም የቸብቸቦ ወረቦች ብቻ ናቸው ቅድሚያ የሚሰጣቸው። መዝሙሩ በከበሮና በጭብጨባ ካልደመቀና የንስሐ መዝሙር ከሆነ የዘመሩ የማይመስላቸው ብዙዎች ናቸው። ስለዚህ ወረተኝነቱን ትተን የቀደሙትን ከአዳዲሶቹ፣ ወረቦቹን ከንስሐ መዝሙሮቹ አጣምረን መዘመር ይልመድብን።

ዳሮት ገዛው – አርባ ምንጭ

የቤተ ክርስቲያን ጉልላት በጠንቋይ ቤት ጣሪያ ላይ!!

ጌታችን ነገረ ምጽዓቱን ባስተማረበት ምዕራፍ እንደተናገረው «የጥፋት ርኩሰት በተቀደሰ ቦታ ቆሞ ስታዩ አንባቢው ያስተውል (ማቴ.24፥15) የሚለው ቃል ዛሬ ተፈፅሟል ብል ግጋነን አይሆንብኝም። ይኸውም በአካባቢያችን አንድ ቀላጢ ለሦስት ዓመታት ያህል በቤቱ ጣሪያ ላይ የቤተ ክርስቲያን ጉልላት በግድረግ ሕዝቡን ሲያስከትል ነበረ። ጉልላቱን ለግውረድ ግንም አይሞክርም። ምክንያቱም ሰው ያልቃል፣ መሬት ትሰረጉዳለች፣ መዓት ይወርድብናል ወዘተ... ተብሎ ይታሰብ ነበርና። ይሁን እንጂ በቤተ ክርስቲያን አገልጋዮችና በምዕመናን ትብብር በጎዳር 1988 ዓ.ም ጉልላቱ ከቤቱ ጣራ ላይ ወረደ። ሰውዬውም በፖሊስ ቁጥጥር ሥር ዋለ። ሰይጣን የተመረጡትን ላይቀር እያሳተ ከቤተ እግዚአብሔር እየለየ አምልኮተ ጣዖትን በእግዚአብሔር ስም እስከግድረግ እየደረሰ ነውና የትንቢቱ መፈፀሚያ ከመሆን በግስተዋል ልንጓዝ ያስፈልገናል።

(ዘውዱ አላምረው – ምሥራት ጉጃም ዕድ ውታ)

በመንፈስ ጅምረን በሥጋ አንፈፅም (ገላ.3፥3)

በብዙ ቦታዎች ለቤተ ክርስቲያን ግሥረያና ግሳደሻ፣ ለበጉ አድራጉት ዐሚል «ባዛር» ግዘጋጀት እየተለመደ መጥቷል። ዓላግው መልካም ሆና ሳለ ለመንፈሳዊ ሥራ ተብሎ በሚዘጋጀው «ባዛር» ላይ የሚቀርበው የአልኮል መጠጥ ብዛትና ዓይነት እንዲሁም የሚጋበዘው የሙዚቃ ባንድ ዓላግውን በመንፈስ ጅምሮ በሥጋ መፈፀም ያደርገዋልና በቶሎ ቢታረም መልካም ነው።

ትርሲት– ክብረ መንግሥት

ከአዘጋጁ – እህታችን ጥሩ ታዝበዋል። ክርስቲያን ከእውነት ለመድረስ በውሸት ጉዳና አይጓዝምና ሁሉም ቢታረም መልካም ነው።

ምን ትወዳለህ ጌታ?

በድንገት እንደበራ መብረቅ
ዙሪያ ጥምጥም ብብርሃን ሲጥለቀለቅ
ዐቅም አጥተህ መሬት ስትወድቅ
ድምፅ ከሰማየ ሰግያት ሲመጣብህ
‹ሳኦል ሆይ ለምን ታሳድደኛለህ?› ሲልህ
ምን ተሰማህ ውስጠትህን የዚያን ለታ
ለሰማያዊ ታል እጅ ስትሰጥ ስትረታ፣
አልክ አይደል? ምን ትወዳለህ ጌታ?

አበባው ዘውዴ
(ከ6 ኪሎ አ.አ.ዩ)

መልካም አዲስ ዓመት

ግኅበረ ቅዱሳን ከዚህ በፊት ያደርግ እንደነበረው ለአዲስ ዓመት የሚሆን የአጽዋማትን ዝርዝር፣ የዘመን መቁጠሪያ እና ስለ አዲስ ዓመት መግለጫ የያዘ ፖስት ካርድ ግዘጋጀቱን በደስታ ይገልፃል።

ቅድስት ግርያም ሽዋ ዳቦ ፊት ለፊት ወደሚገኘው ማከፋፈያችን ብት ይበሉ ያገኛሉ።

ሐመር

4ኛ ዓመት ቁጥር 2
ነሐሴ - 1988 ዓ.ም

ይዘት

የማኅበሩ መልእክት 2
ደብዳቤዎች 3
ከሰሞኑ በረከት
✤ ፍልሰታ 5
ትምህርተ ሃይማኖት
✤ የእግዚአብሔር ሕግ 7
✤ ምሥጢረ ትንሣኤ ሙታን . . 9
✤ አዲስ ኪዳን በብሉይ ኪዳን . . 12
ኪነጥበብ
✤ ሶልያና 15
✤ አንጢላርዮስ 16
እናስተዋውቃችሁ
✤ ደብረ ጽሙና ገዳም 18
✤ አቡነ ኢየሱስ ሞዓ 21
ዓመደ ወራዙት
✤ ንስሐ–ለምንና እንዴት . . 22
✤ አፈን በምላሌ እከፍታለሁ . . 24
✤ የዘጠኙ ቅዱሳን ሥራ ዛሬም መደገም አለበት! 25
ክርስትና በማኅበራዊ ኑሮ
✤ የፈቃድ ዕብደት 28
✤ ክርስትናና ከአንድ በላይ የትዳር ጓደኛ 30
ቤተ ክርስቲያንህን ዕወቅ
✤ የንዋየ ቅድሳት ዝርፊያ – ከትናንት እስከ ዛሬ 31
✤ የቤተ ክርስቲያን ታሪክ . . 32

ከመጽሔቱ ይዘት

✤ ‹ከነሐሴ 1–16 ያለው ጊዜ የጸም፣ የጸሎት፣ የስግደት፣ የዝግሬ እና የሌሊትም መንፈሳዊ ምግባራት መፈጸሚያ ወቅት ነው።› ቅዱስ መጽሐፍስ ስለዚህ በዓል ምን ይላል?

ገጽ 5

✤ ‹ሥጋ ሚችፈራሽ በስባሽ ሲሆን ነፍስ ግን እንደ መላእክት ፍፁም የማትሞት የማትፈርስ የማትበሰብስ ዘወትር ሕያው ሆና የምትኖር ናት።› ስለ ትንሣኤ ሙታን

ገጽ 9

✤ ‹በማናቸውም ምክንያት ይፈጠር ከአንድ በላይ ሚስት ወይም ባል በአንድ ጊዜ ማግባት (Polygamy) በክርስቲያኖች ሕይወት ሊኖር የማይገባ ልቅ የሆነ ዝሙትና ሥርዓት አልበኝነት ነው።›

ገጽ 30

✤ ‹በ1928 ዓ.ም ፋሺስት ጣሊያን በሙሶሎኒ መሪነት በኢትዮጵያ ላይ ባወጀው ጦርነት ዋና የጥፋት ዒላማ የነበሩት አብያተ ክርስቲያናት፣ ገዳማትና አድባራት፣ ካህናት፣ ዲያቆናትና ምዕመናን፣ ባሕታውያንና መነኮሳት እንዲሁም ዘመን የማይተካቸው ንዋየ ቅድሳት ነበሩ።› ለምን?

ገጽ 31

ማስታወቂያ

ስምዐ ጽድቅ – ዘአርቶዶክስ ተዋሕዶ

እግዚአብሔር አምላክ የሠራቸውን ድንቅ ገቢረ ተአምራት፣ በዘመናችን ለተነሡ የኑፋቄ ትምህርቶች መልስ፣ በክርስቲያናዊ ሕይወት ለሚገጥሙ ችግሮች መፍትሔ፣ እና የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርትን በሰፊው የያዘች ጋዜጣ ናትና አታምልጥዎት። በሀገር ውስጥም ሆነ ከሀገር ውጭ ላሉ አንባብያን ለማዳረስ ዝግጁዎች ነን።

ለደንበኝነት		
	የዓመት	የ6 ወር
ለክፍለ ሀገር	ብር 21.00	ብር 10.50
ለአዲስ አበባ	ብር 20.00	ብር 10.00
ከሀገር ውጪ	12 ዶላር	6 ዶላር

አድራሻዎንና የከፈሉበትን ማስረጃ በፖ.ሣ. 80078 ይላኩልን።
የመጽሔታችን ደንበኛ ቢሆኑ እንዲትም አትም አታልፎትም።

	የዓመት	የ6 ወር
ለክፍለ ሀገር	ብር 38.40	ብር 19.20
ለአዲስ አበባ	ብር 37.80	ብር18.70
ከሀገር ውጪ	24 ዶላር	12 ዶላር

አድራሻችን – ለመ/ት ዓይናለም ታዬ ደመቀ
4 ኪሎ ባንክ ቅርንጫፍ
የሂሳብ ቁጥር – 79808
ፖ.ሣ. – 80078
ስልክ – 550099 Ext 46 – አ.አ

በኢትዮጵያ አርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን የሰንበት ት/ቤቶች ማስተባበሪያ መምሪያ በማኅበረ ቅዱሳን የመዝሙርና ሥነ ጽሑፍ ክፍል የሚዘጋጅ ትምህርታዊ መጽሔት።

የኢትዮጵያ አርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያንን ትምህርተ ሃይማኖት፣ ሥርዓትና ትውፊት ጠብቆ የሚወጣ።

ዋና አዘጋጅ – ብርሃኑ ጎበና ካሣ
ም/ዋና አዘጋጅ – ዲ.ደጀኔ ሺፈራው
ስልክ – 550099 Ext. 46
ፖስታ 80078
አዲስ አበባ

©ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org

የማኅበረ ቅዱሳን መልእክት

ቤተ ክርስቲያን የሁሉም ናት

ቤተ ክርስቲያን ቅድስት፣ ሐዋርያዊት፣ አንዲትና ምልዕት ናት። በእነዚህ ጠባዮቿ የምትታወቀው ቤተ ክርስቲያን በክርስቶስ ደም የተመሠረተች አማናዊት ናት። በክርስቶስ በማመን ወደ እርሷ የተሰበሰቡትን ሁሉ ከሥጋና ከነፍስ ጥፋት ታድናለች። በዚህም የቤተ ክርስቲያን ሊቃውንት ምሳሌዋ አድርገው ከሚያስተምሯት ከኖሓ መርከብ ትበልጣለች። የኖሓ መርከብ ስምንት ሰዎችንና በውስጧ የተጠለሉትን ነፍሳት በሙሉ ከሥጋ ጥፋት ብቻ ማዳኗን ቅዱስ መጽሐፍ ያስተምረናል። ዘፍ.7፥1–ፍ.ም

ለነፍስና ለሥጋ መዳኛ፣ መጠለያ የሆነችውን ይህችን አማናዊት ሐመር (መርከብ) መጠበቅ፣ መንከባከብ የማን ኃላፊነት ነው? ስለ ደኅንነቷ ማሰብ ያለበት ማን ነው? ብለን ብንጠይቅ ብዙ የተለያዩ መልሶችን እናገኛለን።

በቤተ ክርስቲያን አገልግሎት ላይ በውስጥም ሆነ በአፍአ (በመቅደስና በውጭ) ከተሰማሩት አንዳንዶቹ የቤተ ክርስቲያን ጉዳይ የሚመለከተው እነርሱን ብቻ ይመስላቸዋል። ቢያጠፉም ቢያለሙም ከራሳቸው ሐሳብ በስተቀር ሌላው ምንም የማያገባው እንደሆነ ለማስረዳት ይሞክራሉ። እኔ እያለሁ እርሱ ምን አገባው በማለት ስለቤተ ክርስቲያን የሚያስቡ ቢያገኙ ከመገሰጽና ዝም ከማሰኘት አይመለሱም። በአንጻሩ ደግሞ በቤተ ክርስቲያን አገልግሎት ላይ ድርሻቸው በውል ተለይቶ ያልተሰጣቸው ደግሞ እነ እገሌ እያሉ እኔ አያገባኝም እኔ ምን ቸገረኝ በማለት ዳር ቆመው መመልከትን ይመርጣሉ። ይህንንም በማድረጋቸው ትክክል የሠሩ ይመስላቸዋል።

በመሠረቱ ቅድስት ቤተ ክርስቲያን ከተመሠረተች ጀምሮ የአገልግሎት ሥርዓት አላት። ለዚህም ያመቻት ዘንድ በተለያዩ ደረጃዎች መሪዎችን ለይታ አስቀምጣለች። ሁሉም የሚመለከተው የራሱ የሆነ የአገልግሎት ክፍል አለው። ምዕመኑ የዲያቆኑን፣ ዲያቆኑ የቄሱን፣ ቄሱ የጳጳሱን፣ ጳጳሱ የሊቀ ጳጳሱንና የፓትርያርኩን ድርሻ አውቆና ለይቶ የራሱ የሆነውን ብቻ ይፈፅማል። ከላይ ወደ ታች ያለውም አፈጻጸም ይኸንኑ የተከተለ ነው። ቄሱ የዲያቆኑን ትምህርትና አገልግሎት (ድርሻውን) አስቀድሞ የሚያውቀው በመሆኑ የዲያቆኑንም ድርሻ እኔው ደርቤ ልስራው፣ ከእንግዲህ ዲያቆን አያስፈልግም፣ አያገባውም ማለት አይችልም። ሁሉም ድርሻ አለው፣ ሁሉም የየድርሻውን በትህትና እና በመከባበር መወጣት ይጠበቅበታል።

የቤተ ክርስቲያንን የአገልግሎት ሥርዓት አባቶቻችን በመንፈስ ቅዱስ በመመራት እንዴት አስተካክለውና አሳምረው እንዳስቀመጡት ከቤተ ክርስቲያናችን የጸሎት መጽሐፍት መገንዘብ እንችላለን። የካህኑን ድርሻ ዶካ (ይበል ካህን)፣ የዲያቆኑን ድርሻ– ይዲ (ይበል ዲያቆን)፣ የምዕመኑን ደግሞ ይሕ (ይበል ሕዝብ) በማለት የሁሉንም ለይተውታል። በእውነቱ የቅዳሴ፣ የሰዓታትና የሌሎቹም የቤተ ክርስቲያን የጸሎት ዓይነቶች የክህነትን አገልግሎት ከሌላው ሥራ ሁሉ በበለጠ ሁኔታ የሚፈልጉ ሆነው ሳለ ለምዕመኑም ድርሻውን ለይተው ከሰጡት በሌሎቹ ሥራዎች ምዕመናን በይበልጥ መሳተፍ ያለባቸው መሆኑን እንመለከታለን። ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስም እያንዳንዱ የክርስቶስ አካል መሆኑን ከገለጸ በኋላ በእያንዳንዱ ክርስቲያን መልካም አገልግሎት ቤተ ክርስቲያን እንደምትታነጽ ገልጿል። 1ቆሮ.12፥27፣ ኤፌ.2፥22።

ችግሩ ግን ምዕመናን ራሳቸው ቤተ ክርስቲያን የካህናት ብቻ እንደሆነች አድርገው ስለሚወስዱ፣ ራሳቸውን ገለልተኛ በማድረግ የሚጠበቅባቸውን ያህል እርምት ለማድረግ አይዘጋጁም። ምናልባትም ለቤተ ክርስቲያን ማሰብ ያለባቸው በክህነት አገልግሎት ላይ ያሉ የተወሰኑ ሰዎች ብቻ አድርገው ይወስዳሉ። አንዱ ሲያጠፋ ሌላው ሊያርም አይፈልግም። ሌላውም እንዲታረም አይፈቅድም። ይልቁንም አንዱ በሌላው ላይ የተመለከተውን ስህተት ከማረም ይልቅ ማጋነን በጉልህ የሚታይ ክስተት ሆኗል። አንዳንዶች የሰበካ ጉባዔ አባል በመሆናቸው መሥራት የሚገባቸው ምን እንደሆነ ያልተገነዘቡ ስለሆኑ ለመሥራት የግድ መመረጥ ያልባቸው ይመስላቸዋል። ለቤተ ክርስቲያን አገልግሎት በሰበካ ጉባዔም ይሁን በሌላ የተመረጡና የተቀመጡ ካሉ ሁሉም ነገር የሚመለከታቸው እነርሱን ብቻ እንደሆነ በግልጽ ማንኛውንም ነገር ለእነርሱ አላልፈው ይሰጣሉ። በሰንበት ት/ቤቶችና በሌሎችም ቤተ ክርስቲያንን ለማገልገል በሚቋቋሙ ማኅበራት የዚህ ዓይነት ሁኔታ በተለያየ መንገድ ሲገለጽ ይታያል።

የቤተ ክርስቲያን አገልግሎት ከሌላው ዓለማዊ የአሠራር ሥርዓት ሁሉ የሚለየው ሁሉም ክርስቲያን ለመልካም ሥራ የራሱ የሆነ ድርሻ ስለአለው ነው። መልካም የሆነውን ሁሉ ስለእምነቱ ሲል ሥርዓቱን ጠብቆ ማከናወን ይጠበቅበታል። በዚህም ከዚህ ምድር ባለሥልጣን ሳይሆን ከሰማያዊው ንጉሥ ከእግዚአብሔር ዋጋውን ይቀበላል። ታዲያ በዚህ መልካም ሥራ ማን ይሰማራ? ቤተ ክርስቲያንን በመጠበቅ ተጠቃሚው ማን ነው? ቤተ ክርስቲያንስ የማን ናት? መልሱ ከእያንዳንዱ የቤተ ክርስቲያን ልጅ ይጠበቃል።

ለሁሉም መልካም ሥራን ሠርተን ሰማያዊ መንግሥትን ለመውረስ የእግዚአብሔር መልካም ፈቃድ የድንግል ማርያም አማላጅነት አይለየን። አሜን።

ወስብሐት ለእግዚአብሔር

©ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org

ደብዳቤዎች

መጽሔታችሁ መልካም የሆነ መንፈሳዊና ሥጋዊ ትምህርቶችን በመያዟ በጥቂ_ ረተሰቡ ዘንድ በጣም ተወዳጅ ከሆነች ውላ አድራለች። በተለይም ክርስትና በማኅበራዊ ኑሮና የእናስተዋውቃችሁ ዓምዶች አርቶዶክሳውያንን ብቻ ሳይሆን የሌሎችንም የማንበብ ፅድል ከፍ ስለሚያደርጉ በጨው ተጥሉ። ወደፊትም ከወጣቱ ሕይወት ጋር የሚሄዱ ሃይማኖታዊ ጽሑፎችን መጻፉን እንደምትቀጥሉ ተስፋ አደርጋለሁ።

እኔም ለወደፊቱ ቋሚ ደንበኛ ለመሆን ቃል እገባለሁ።

እግዚአብሔር ሥራችሁን ይባርክ።

መ/ር እጅጉ

(ባሌ መ/ፀ/መድኃኔዓለም ሰ/ት/ቤት)

ኪንዶ ኮያሻ

እርስዎም ቃልዎን በማክበሩ ይኀሩበት እኛም እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ አገልግሎታችንን እንቀጥላለን።

✣ ✣ ✣

መጽናኛ ሆናችሁናል!

መንፈሳዊ እንቅስቃሴያችሁ በአገር ውስጥ ብቻ ሳይወሰን ለእኛ ከሀገራችን ርቀን ለምንኖር ወገኖች ጭምር ትልቅ ትምህርት እየሰጠ ነው። ለወደፊቱም ምኞታችን በተቻለ መጠን በጥንታዊቷ የአርቶዶክሳዊት ቤተ ክርስቲያን ሥርዓት ጸንቶ መገኘት፣ ለተተኪውም ትውልድ ግልጥግር ነው። ታዲያ ለመንፈሳዊ ሕይወታችን ፈተና የሚሆኑ አስቸጋሪ ሁኔታዎች ሰላሉብን እንዲሁም የምዕራቡ ዓለም የባሕል እንቅስቃሴ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ቀስ በቀስ ሥር እንዳይሰድና ሥርዓታችንን አጥፍቶ ማንነታችንን እንዳያስረሳን የእናንተ ድጋፍና የዘወትር ጸሎታችሁ ያስፈልገናልና በርቱልን። የቅዱሳን አምላክ የተመሰገነ ይሁን እሜን።

(የመካነ ሰላም መድኃኔዓለም—ሐመረ ኖኅ መዘምራን ካሊፎርኒያ—ቡርክሊያ)

እንደዚህ ፈተና በሚበዛበት አካባቢ መውጫ ቀዳዳው፣ መሸሸጊያ ጥላው ቤተ ክርስቲያን ናትና በጀመራችሁት ጽኑ የያዛችሁት የተጠልላችሁበትም ከሁሉ የሚበልጠው ነው።

✣ ✣ ✣

ቢታሰብበት

በካሴት የሚወጡ መዝሙሮች እየበዙ መምጣታቸው ቢያስደስተንም የቤተ ክርስቲያንን ሥርዓት የመጠበቃቸው ሁኔታ ግን እየተጣሰ የመጣ በመሆኑ የቤተ ክርስቲያን የሆኑትን በመጽሐፍ ብታሳትሙልን መልካም ነው። በተጨማሪም የኔታችንና የቅዱሳንን ሥነ ሥዕል በልብስ ላይ መሥራት እየተለመደ መጥቷል። ልብሱ ሲታጠብ ሲያልቅና ሲቀደድ መንገላታት ለሥዕሉ ክብር አለመስጠት ይሆንብናልና ቢታሰብበት።

ከአዘጋጁ — የመዝሙሩን በተመለከተ የናስ አሳታሚ ድርጅት ያወጣቸው «መዝ ሙረ ተዋሕዶ» ቁጥር 1 እና 2 ሰላሉ ቢመለከቷቸው መልካም ነው። ሁለተኛውን ጥያቄ በተመለከተ ጥንቃቄው ሁሉንም አርቶዶክሳዊ የሚመለከት ነውና የተቀደሰውን በተቀደሰ ቦታ እናኑረው።

✣ ✣ ✣

ማመስገን አለብን

አምላኬ እግዚአብሔርን ዕለት ተዕለት ማመስገን አለብኝ ምክንያቱም።

- ካለመኖር ወደመኖር፣ ካለመታወቅ ወደ መታወቅ አምጥቶኛልና፣
- ከሥነ ፍጥረታት የተመረጠ የክብረና በአምላክ የተወደደ አድርጐኛልና፣
- አዳምን ለማዳን የተደረገው ቸርነት ተካፋይ ሆኜአለሁና፣
- አላዋቂና ድሀ ስሆን እግዚአብሔር በዝናብ አብቅሎ፣ በፀሐይ አብስሎ፣ የኀጢአት ልብሴን፣ የዕለት ጉርሴን ሰጥቶኛልና፣
- በተምሮት ያገኘኋትን ልጅነት ሳንድፍ ከኃጢአቴ መመለሻ ንስሐን አዘጋጅቶልኛልና፣
- በኃጢአት ስመላለስም እስከመለስ ድረስ በትዕግስት ጠብቆኛልና፣
- ኃያልና ብርቱ በሆነ ጠላት ፊት ደካማ የሆንኩ እኔን አድንቶ አቁሞኛልና፣

ምክንያር ጉዶሉ ብሆንም ዋስ ጠበቃ የሚሆኑ ቅዱሳንን ሰጥቶኛልና ሁል ጊዜ አመሰግነዋለሁ።

(ላኖቹው አምበርብር — አሥጣ)

✣ ✣ ✣

እርምት

በ3ኛ ዓመት ቁ.4 እትማችን ወርሃ ጽጌ በሚለው ጽሑፍ ውስጥ እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም በስደት ወቅት ይደርስ ነንደር መሲሆን በእስቲ ወረዳ ጉበጣሮት የሚባል ቦታ ከልጇ ጋር አርፋለች የተባለው እስቲ ወረዳ ሳይሆን ደራ ወረዳ ተብሎ ይስተካከል።

ምስጋናው ፈንታ

(ደራ ወረዳ)

✣ ✣ ✣

እኔ የመረጥሁት ጾም

- ከፈታደ ሥጋ ይመለየት (ኢሳ.58÷3)።
- ከሥጋና ከመጠጥ በመከልከል (ዳን.3÷3፤ መዝ.108÷24)።
- ከኃጢአት ቀንበር በመላቀቅ (ገላ.5÷1)።
- የጸብን እሥራት በፍቅር በመፍታት (ማቴ.5÷23)።
- እንጀራን ለተራበ በመቁረስ (ኢሳ.58÷7፤ ያዕ.2÷15)።
- ስደተኞችን ወደ ቤት በማስገባት (ኢሳ.58÷7፤ ዕብ.13÷1)።
- የተራቆተውን በማልበስ (ያዕ.2÷15፤ ኢሳ.58÷7) የሚፈፀመውን ነው። እኔ የመረጥሁት ጾም ይህ አይደለምን?» (ኢሳ.58÷1—11) ይላል እግዚአብሔር።

ዲ/ፍስሐ ለማ

(ሲላሞ ለኩ/ት/ጊዮርጊስ/ሰ/ት/ቤት)

✣ ✣ ✣

የቤተ ክርስቲያን አመሠራረት ተምሳሌት

የቤተ ክርስቲያኑ፣

- መቅደሰ — የአብ ምሳሌ
- ቅድስት — የመንፈስ ቅዱስ ምሳሌ
- ቅኔ ማኅሌት — የወልድ።

©ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org

- መዝጊያ– የቅዱስ ሚካኤልና የቅዱስ ገብርኤል ምሳሌ
- ነበኩ – የዮሴፍና የኒቆዲሞስ ምሳሌ
- ጣራው – የሰማዕታት ምሳሌ
- ግንፋሎ – የተዋሕዶ ቃል ምሳሌ
- ክዳን – ሄሮድስ ያስፈጃቸው ሕፃናት ምሳሌ፤
- ታቦት – የእሳተ መለኮት ምሳሌ
- ጽንሐው – የሥላሴ ምሳሌ
- የጽንሐውክር – የእመቤታችን ምሳሌ
- እሳቱ – የወልድ ምሳሌ
- ድምው – የመላእክት ምሳሌ
- ሕንፃው – የሐዋርያት ምሳሌ
- ገበታው – የእግዚአብሔር አብ ምሳሌ መሆናቸውን ያውቃሉ።

(ብርሃነ መስቀል ጠና
ባሕር ዳር ፕሳጉ)።

መጽሔታችሁ ለምን ትዘገያለች?

የምታወጧቸው ጽሑፎች መካሪና አስተማሪ ናቸው። ሆናም መጽሔታችሁ ከሁለት ና ከሦስት ወራት በላይ የምትዘገይበት ጊዜ አለ። ምክንያቱ ምንድን ነው? ለወደፊቱ ቢቻል በየወሩ ለማውጣት ጥረት ብታደር ጥልን መልካም ነው።

ተመስገን ከተማ እና ገረመው እንግዳሸት
አዲስ አበባ

ከአዘጋጁ – መጽሔቷ የምትዘገየው አዘጋጆቹ ባለባቸው ተደራራቢ ሥራዎችና በሌሎች ውስጣዊ ምክንያቶች ነው። ይህንን ችግር ለመቅረፍ እየጣርን ነውና በትብብርዎ ይግፉበት።

በእጅ መባረክ አይቻልም?

በአካባቢያችን ያሉ መምህር ሲያስተምሩ ሥልጣነ ክህነት የሌለው ሰው በእጁ መአዱን መባረክ አይችልም አሉን። ከዚህ በፊት እናደርገው የነበረ ነገር ነውና አሁን እንዴት መባረክ እንዳለብን ተጨንቀናልና አንድ በሉን።

ከአዘጋጁ – ማንኛውም ክርስቲያን ምግብ ከመመገቡ በፊት በስመ እግዚአብሔር አማትቦ ጸሎት እድርም መብላት አለበት። ሥልጣነ ክህነት የሌለው ሰው የእጅ መስቀል ይ። መባረክ አይፈቀድለትም። በተረፈ ግን የራሱን ግዕድ ባርኮ እንዳይመገብ የሚከ ለክለው ሥርዓት የለም።

የዕድሜ ገደብ አለው?

ዕድሜያቸው ከ30 ዓመት በላይ የሆኑ ምዕመናን እግዚአብሔር በሰጣቸው ጸጋ በሰ/ት/ቤት ውስጥ በመዝሙሩ፣ በትም ህርቱና በሥነ ጽሑፉ ለማገልገል የዕድሜ ገደቡ ችግር ፈጥሮብናል። ምን ይሻላል? ለመሆኑ ሰ/ት/ቤት ለመሳተፍ የዕድሜ ጣራ አለው?

(የሸኖ ሮቢት ደ/ገ/ት/ማ/ሰንበት ት/ቤት)

ከአዘጋጁ – የሰንበት ት/ቤቶች ማ/መምሪያ አሻሽሎ ባወጣውና ቅዱስ ሲኖዶስም ግንቦት 2 ቀን 1986 ዓ.ም ባጸደቀው መመሪያ መሠረት ሰ/ት/ቤት ለመካፈል የዕድሜ ገደብ አልተደረገም። ለበለጠ ማስረጃ ስምዐ ጽድቅ ጋዜጣ 3ኛ ዓመት ቁጥር 2 ከሰንበት ት/ቤቶች አምባ የሚለውን ዓምድ ተመልከቱ።

የነቢያት ጸም ጋድ አለው?

«ገሃድ» ከሰባቱ አጽዋማት አንዱ እንደሆነ እናውቃለን። ይህም ጥምቀት በጸመ ድኀነት ቀን ዓርብና ረቡዕ ከዋለ በዋዜማው ያለውን ቀን ይጾማል። የእኛ ጥያቄ ግን ገና (ልደት) ገሃድ አለው ወይ? ካለው ጸመ ነቢያት ከሰባቱ አጽዋማት ቁጥር እንዴት መግባት ይችላል? በተጨማሪም ጥምቀት ከረቡዕና አርብ ውጪ ቢውል ጋድ ይኖረዋል።

ዘውድነሽ ዘለለውና ገ/ሚካኤል
ከለዋሽ መካነ ሥላሴ ሰ/ት/ቤት

ከአዘጋጁ – ገሃድ ማለት ለውጥ ልዋጭ ማለት ነው ፍቹ ከዘይቤው አይገናኝም። ሀይም እንደ ዘይቤው (ግልጥ) ማለት ነው።

ገሃድ የጥምቀት ብቻ ነው። ጥምቀት በረቡዕና በዓርብ በሚውልበት ጊዜ በኋላው የሚጥሉት ማክሰኞና ሐሙስ ይጾማሉ። በነሱ ለውጥ ጥምቀትን የሚውልባቸው የጾም ቀናች (ረቡዕና ዓርብ) የፍስክ ቀን ሆነው ይከበራሉ። ገሃድ የረቡዕና የዓርብ ለውጥ ነው ብለናል። ነሺ ግን በሌላም ቀን ቢውል የጥምቀት የዘጣ ይጾማል። ለምሳሌ ጥምቀት አሑድ ቢውል ቅዳሜ ጥሉላት አይበላም።

ገሃድ ለጥምቀት ብቻ ነው። በልግድ ግን የልደትንም የዘጣ ገሃድ እንለዋለን። ነገር ግን ልደት የሚውልባቸው ዓርብ ወይም ረቡዕ የፍሰክ ቀን ሆነው እንዲከበሩ ቢታዘዝም (ስንክሳር ጥር 10 ቀን) በዋዜማው የሚጥሉት ማክሰኞና ሐሙስም ከጸመ ነቢያት ጋር የተያያዙ ስለሆኑ መጾማቸው የግድ ነው። የሚያጸሙ ሰዎች ግን ከሰባቱ አጽዋማት አንዱ የሆነውን ጸመነቢያት ሲበሉ ቆይተው ዋዜማውን ብቻ ገሃድ ነው ብለው ይጾማሉ።

ምንጭ – የኢትዮጵያ ቤ/ን ታሪክ
በብፁዕ አቡነ ጎርጎርዮስ። ገጽ 154

መገዛጋት መፍትሔ ይሆናል?

አንዳንድ የቤተ ክርስቲያን አስተዳዳሪዎች ወይም የሰበካ ጉባዔ ተመራጮች በሰንበት ት/ቤቶች አካባቢ ችግር መፈጠሩን ከለሙ ምንም ማጣራት ሳያደርጉ፣ ጨምሮውን ከበሽተኛው ለመለየት ሳይሞክሩ፣ ውሳኔ ሁሉ አጥፊ እየመሰላቸው ወሬውን በሰሙ ማግሰት ሰ/ት/ቤቱን ዘግተው ወጣቱን ከቤተ ክርስቲያን ማባረርን ይመርጣሉ። አንዳንዶቹማ ወጣቶች በቤተ ክርስቲያን ተሰብስበው ማየትን እንኳን አይወዱምና እባካችሁ የሰ/ት/ቤትን ዓላማ ደጋግማችሁ አሳውቁልን።

ብርሃነ ትንሣኤ ግዛው– ከአዲስ አበባ

ከአዘጋጁ – ሰንበት ት/ቤት አርቶዶክሳዊ እምነታችንን የምንማርበት የትምህርት ማዕከል እንጂ የሕፃናት አቧራ ማቡነኛ፣ ውኃ መራጫ ብቻ አይደለም። ስለዚህም በወጣቶቹ መካከል ችግር ሲፈጠር ችግሩን አጥንቶ መፍትሔ መፈለግ እንጂ በደፈናው መዝጋት ብቻውን መፍትሔ አይሆንም። በዚህ ነጥብ ላይ በበለጠ አስተያየቶችን ለመስጠት ግኅኙ በስምዐ ጽድቅ ጋዜጣ ላይ ከሰንበት ት/ቤቶች ዓምባ የሚል ዓምድ ከፍቷልና ሀሳባችሁን በዚያ በኩል ለውይይት አቅርቡት።

©ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org

ከሰሞኑ በረከት

ነሐሴ ሲመጣ በልጅ – በዐዋቂው ጎኒና የሚመላለስ፣ ሁሉም በናፍቆት የሚጠብቀው አንድ ነገር አለ – ጾመ ፍልሰታ። በግንኛውም ኦርቶዶክሳዊ ልቡና የእመቤታችንን ፍቅር ከትቦ የሚያልፈው ይህ ጊዜ የጾም፣ የጸሉት፣ የስግደት የዝግረ እና የሌሎችም መንፈሳዊ ምግባራት መፈፀሚያ ነው።

እናታችን ቅድስት ድንግል ማርያም ሦስት ዓመት በእናት በአባቷ ቤት፣ አሥራ ሁለት ዓመት በቤተ መቅደስ፣ ሠላሳ ሦስት ዓመት ከሦስት ወር ከጌታችን ጋር፣ አሥራ አምስት ዓመት በወንጌላዊው በዮሐንስ ቤት ከኖረች በኋላ በ64 ዓመቷ ጥር 21 ቀን ዐርፋለች። በሐዋርያትም ውዳሴ፣ ዝማሬ እና ማኅሌት ነሐሴ 14 ቀን ከተቀበረች በኋላ በነሐሴ 16 ተነሥታ በይባቤ መላእክት ወደ ሰማይ ዐርጋለች። ቅዱስ ያሬድ በመዝሙሩ ‹ተለዐለት እምድር ወበህየ ነበረት ዘምስለ ወልዳ፣ በየማነ አብ ወመንፈስ ቅዱስ – እመቤታችን ድንግል ማርያም ከምድር ወደ ሰማይ ዐረገች። በሰማይም ከልጅዋ ጋር በአብና በመንፈስ ቅዱስ ቀኝ ተቀመጠች።» እና ከሺህ ዓመትም በፊት አባቷ ዳዊት ‹በወርቅ ልብስ ተጐናጽፋና ተሸፋፍና ንግሥቲቱ በቀኝህ ትቆማለች።› (መዝ.44÷9) እንዳለ።

ይህ እንደ እንግዳ ደራሽ እንደ ውሃ ፈሳሽ ያልሆነ በቅዱስ መጽሐፍ የተደገፈ ነውና ማመሳከሪያውን እነሆ።

ፍልሰታ የሚለው ቃል የእመቤታችን ሥጋ ከጌቴሴማኒ ወደ ገነት መፍለሱን ኋላም በገነት በዕፀ ሕይወት ሥር ከነበረበት መነሣቱን ለማመልከት የሚነገር ነው። (ወላዲተ አምላክ በኢትዮጵያ – ገጽ 68)።

ንግሥተ አርያም ድንግል ማርያም ድንግልና ከእናትነት፣ እናትነት ከድንግልና ተባብሮላት በክብረ ወሊድ ላይ ክብረ ድንግልና ተጨምሮላት የአምላክ እናት፣ ዘለዓለም ድንግል፣ በሁለት ወገን ድንግል መሆንዋን ቅዱስ መጽሐፍ እንደሚመሰክር ሁሉ ምትን በልጅዋ ኃይል ድል አድርጋ መነሳትዋንም ይኸው ቅዱስ መጽሐፍ ያስተምረናል።

ፍልሰታ

(ከብርሃኑ ጎበና)

ነቢዩ ልበ አምላክ ዳዊት የእመቤታችን ትንሣኤ አስቀድሞ በትንቢት መስተዋትነት ታይቶት ‹ተንሥእ እግዚኦ ውስተ ዕረፍትከ አንተ ወታቦተ መቅደስከ – አቤቱ ወደ ዕረፍትህ ተነሥ አንተና የመቅደስህ ታቦት።» በግለት ተናግሯል። መዝ.131÷8። እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያምን እመአምላክ ወላዲተ አምላክ (Theotokos) ናት፣ ሥጋዋ ፈርሦ በስብሶ አልቀረም ተነስታለች ብሎ ለማመን፣ ያመኑትንም በአንደበት ለመመስከር፣ በምግባር ለመግለጽ እንደ ነቢዩ ዳዊት፣ እንደ ኤልሳቤጥ በመንፈስ ቅዱስ መታኘት ያስፈልጋል።

ቅዱስ ዳዊት ለያዕቆብ አምላክ ለእግዚአብሔር ማደሪያ እስካገኝ ድረስ ወደቤቴ አልገባም፣ ወደ ምንጣፌም አልጋ አልወጣም ብሎ ማለ። የያዕቆብ አምላክ እግዚአብሔርም በአማናዊቱ ቤተ መቅደስ በድንግል ማርያም ማኅፀን ተወሰነ። ልዑለ ባሕርይ አምላክ የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር ራሱ በድንግልና በንጽሕና ባስጌጣት በድንግል ማርያም ማኅፀን አደረ። ኤፍራታ ተብላ በምትጠራው በቤተልሔም የሰውን ባሕርይ ባሕርይው አድርጎ ከድንግል ማርያም ተወልዶ በግዕዘ ሕፃናት ሲያለቅስ ሰማነው፣ በበረት ተጥሎ በመጨረቅም ተጠቅልሎ አገኘነው ሲል ‹እነሆ በኤፍራታ ሰማነው በዱር ውስጥም አገኘነው› ብሎ ተነበየ። በመስቀል ላይ የፈፀመውንም የድኅነት ሥራ ‹እጆቼና እግሮቼን ቸነከሩኝ› (መዝ.21÷16) በማለት አስረዳ።

ከጽንሰት አንስቶ በመስቀል ላይ እስከዋለበት ድረስ ያለውን ከገለጸም በኋላ ትንሣኤውን ሲነገር ‹አቤቱ ወደ ዕረፍትህ ተነሥ።› አለ። በዚህም ጌታ ወደ ቀደመ ክብሩ ሞትን ድል አድርጎ መነሣቱን መናገሩ ነው። የእናታችን የድንግል ማርያምንም ትንሣኤ አያይዞ ሲናገር ‹አንተና የመቅደስህ ታቦት› ብሏል።

ድንግል በክልኤ እመቤታችን በወንጌል መቅደስ ተብሎ ለተጠራው ለጌታ–ለኢየሱስ ክርስቶስ ታቦት (ማደሪያው) ሆናለች። በመዋዕለ

©ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org

ትምህርቱ ስለ ራሱ ሲናገር ‹ይህን ቤተ መቅደስ አፍርሱት በሦስት ቀንም አነሣዋለሁ አላቸው። ስለዚህ አይሁድ ትንሣኤዋን ‹ወዳጄ ሆይ ተነሺ፣ ውበቴ ሆይ ነዪ› በማለት ተነበየ። ስለዚህ አባቶቻችን ይኸንን አስቀድሞ ለነብያት የተገለጠ ከሰው ልጅ መዳን ሥጋዋን ለማግኘት ሲሉ ቀን ወስነው፣ ቀኖና ሠርተው የጾሙትን የፍልሰታን ጾም ደግሞ እንደ ጥንተ ታሪኩ ከነሐሴ 1–16 እየጾምን እየጸለይን እንድናስበው፣ የትንሣኤዋን በዓልም በነ ሐሴ 16 እንድናከብረው አዝዘውናል። በእመቤታችን ትንሣኤ ኢየሱስ ክርስቶስ የሰጠንን የዘለዓለም ሕይወት በርስዋ የጀመረ መሆኑን ይገልጥ ልናል። አልፎም የሰጠን ተስፋ ተስፋ ብቻ ሆኖ አለመቅረቱን በእመቤታችን ትንሣኤ አይተነዋል። ብልህ ልጅ እናቱን ይከተላል።

እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያምን እመአምላክ ወላዲተ አምላክ (Theotokos) ናት፣ ሥጋዋ ፈርሦ በስብሶ አልቀረም ተነስታለች ብሎ ለማመን፣ ያመኑትንም በአንደ በት ለመመስከር፣ በምግባር ለመግለጽ እንደ ነቢዩ ዳዊት፣ እንደ ኤልሳቤጥ በመንፈስ ቅዱስ መቃኘት ያስፈልጋል።

የእመቤታችን አማላጅነት የእግዚ አብሔር ቸርነት አይለየን። አሜን። ቁ

ይህ ቤተ መቅደስ ከአርባ ሰድስት ዓመት ጀምሮ ይሠራ ነበር። አንተስ በሦስት ቀን ታነሣዋለህን? አሉት። እርሱ ግን ስለ ሰውነቱ ቤተመቅደስ ይል ነበር። ስለዚህ ከሙታን ከተነሣ በኋላ ደቀ መዛሙርቱ ይህን እንደ ተናገረ አሰቡና መጽሐፍንና ኢየሱስ የተናገረውን አመኑ።› ዮሐ.2፥19–22።

መጽሐፍ የተናገረውን አመኑ ሲል በቅዱስ ዳዊት አስቀድሞ የተነገረውን መሆኑን ማስተዋል ያስፈል ጋል። በዚህም የጌታን ትንሣኤ የገለጸ ዳዊት የእመቤታችንንም ትንሣኤ የዘመን ግድግዳ ሳይከልለው ተመ ለከተ።

መፍቀሬ ጥበብ ሰሎሞንም «ወዳጄ ሆይ ተነሺ፣ ውበቴ ሆይ ነዪ፣ እነሆ ክረምት – ዝናቡም አልፎ ሄደ። አበበች በምድር ላይ ተገለጡ። የዜማም ጊዜ ደረሰ። የቁርዩውም ቃል በምድራችን ተሰማ። በለሱ ጐመራ። ወይናችም አበቡ። መዓዛ ቸውንም ሰጡ።› (መኃ.2፥10–14) በማለት በስደት፣ በአይሁድ ዛቻ፣ በልጁ ሕማም ልብዋ በኃዘን ፍላፃ ሲነደፍ የናረበት የዚህ ዓለም የመከራ ጊዜ (ክረምት) ማለፉን ተናገረ። በዚህም ትንሣኤው በምድር ላይ መገለጡን፣ መሰበኩን፣ የሐዋርያት ድምፅ በመላው ዓለም መድረሱን፣ ክርስትና ማፍራት መጀመሩን፣ አቢያተ ክርስቲያናት በመላው ዓለም ማበብ መዓዛ ምግባራቸውንም ማቅ ረብ መጀመራቸውን መሠከረ። በእግ ዚአብሔር መንፈስ የተቃኘ ነውና ጋር የተያያዘ፣ የእመቤታችንን ክብርና ቅድስና የሚገልጥ ምሥጢር በመረዳት ‹ክቡር ሞቱ ለጻድቅ› ነውና ዕረፍቷን በጥር 21 ቀን፣ ሐዋርያት አርድእቱ አጉሣ፣ ድሪቶ አቅርበው የሚፈሰሰውን እንባውን እየተቀበሉ በዚያ እያራሱ ግራምጣ ይሰፉበት ሰሌን ይታቱበት ነበር።

- (እናንተ አሁን የምታለቅሱ ብፁዓን ናችሁ፣ ትስቃላችሁና። ሉቃ.6፥21)
- (የሚያዝኑ ብፁዓን ናቸው፣ መጽ ናናትን ያገኛሉና። ማቴ.5፥4) ቁ

አባ አጋቶን መነኩሴ ጌታን ሲበድል ኃጢአት ሲሠራ ባየ ጊዜ ሕሊናው የፈረደበትና፣ የነቀፈበት እንደሆነ ነፍሱን እንዲህ ይላት ነበር:-

- «ወንድምሽን የነቀፍሽው ስለምን ነው? በፍዳ አንቺን ይመረምሩ ሻልን? ነቀፋሽን ተያ። በሰው ከመፍረድ ተከልከዪ። በአንቺ ኃጢአት በድንቁርናሽ ብቻ ነው እንጂ በሌላው ኃጢአት አይመረ ምሩሽምና።» እንዲህ እያለ ሕሊናውን ከነቀፋ ይመልስ ነበር።
- (አትፍረዱ አይፈረድባችሁምም፣ አትኮንኑ አትኮነኑምም። ሉቃ. 6፥37።)

መጻሕፍተ መነኮሳት (2ኛ መጽሐፍ) ፊልክስዩስ ገጽ 56፥136

ሥ/ር ቴዎድሮስ በየነ–ቡራ ደ.መ.ቅ.ጊ.ሲ.ት.ቤት ኢሉባቦር።

«ከቅዱሳት መጻሕፍት»

እነሆ ብዙ ሰዎች ከልዑል ፍቅረ እግዚአብሔር ደርሰው ዳግመኛ ወረዱ፣

- .ንፁሕም ብትሆን ጌታን የምትወ ድድ፣ ብልሕ አዋቂ ብትሆን ጌታን የሚወድድ ያን ጠቢቡን ሰሎሞንን አስበው በወጣትነቱ አዋቂ ነበር፣ ኋላ ግን አላዋቂ ዘማዊ እንደሆነ።
- ነቢይም ብትሆን ያ ነቢይ እንደምን ተዋረደ? (1ኛነገ.13፥1–34)
- ሐዋርያም ብትሆን ጋኔን ብታወጣ ተዓምራት ብታደርግ ይሁዳ ‹ሐዋ ርያ› ከተባለ ጋኔን ካወጣ በኋላ በፍ ቅረንዋይ እንደተሰነካከለ አስብ።
- ወንበዴ፣ ነፍሰ ገዳይም ብታይ አዳ ምን ቀድሞት እንደገባ፣ ‹ቀድሞኝ ገነት ይገባ እንደሆነ እኔ ምን አውቃለሁ? በል።»
- ዘማዊ ብታይ፣ ኃጥእም ብታይ «ክርስቶስ ይወድደው ዘንድ እንዳለው ከእኔ ይልቅ ስለኃጢአቱ ያዝን፣ ያለቅስ እንደሆነ ምን አውቃለሁ?› በል።

አባታችን አባ አርሳንዮስ የዓይኑን ሽፋሽፍቶች ተመዝዘው ተነቃቅለው እስኪወድቁ ድረስ ያለቅስ ነበር። ከብዛቱ የተነሳ

©ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org

ትምህርተ ሃይማኖት

ባለፈው እትም የአሠርቱን ትእዛዛት ዝርዝር በማቅረብ የመጀመሪያውን ትእዛዝ የመጀመሪያ ሐረግ በመዘርዘር እንደመንደርደሪያ ተመልክተነው ነበር። ዛሬ ደግሞ የዚህን ትእዛዝ ዋነኛ ክፍል በመተንተን ለመመልከት እንሞክራለን።

«ከእኔ በቀር ሌሎች አማልክት አይሁኑልህ»

ሰዎች ይህን ትእዛዝ በሚያነቡበት ወይም በሚሰሙበት ጊዜ «ይህ ከእኔ ጋር ምን ግንኙነት አለው፣ ይህ ሊነገር የሚገባው ለክሐድያንና ለመናፍቃን ወይም ከሥጋዊ ዕውቀታቸው የተነሣ አሊያም ከፍልስፍና በመነጨ ሁኔታ ከሃይማኖት ያፈነገጡትን ነው። እኔ ግን በሳምንት ይሽን ያህል ቀን እጸ ግለሁ፣ አሥራት አወጣለሁ፣ በየሰ ዓቱ እጸልያለሁ፣ ከልቤ እዘምራለሁ፣ የቤተ ክርስቲያን መርሐ ግብሮችን ያለማቋረጥ እከታተላለሁ፣ ስለሆነም ይህ ትእዛዝ አይመለከተኝም» ይሉ ይሆናል።

ነገር ግን ይህ ትእዛዝ ማንንም ሳይለይ ሁሉንም ሰው የሚመለከት ነው። «ከእኔ በቀር ሌሎች አመልክት አይሁኑልህ» ተብሎ ተነግሯልና። «ሌሎች አማልክት» ሲልም በሰው እጅ የተጠረቡትንና ሰው ያቆማ ቸውን፣ በፀሐይ፣ በባሕር፣ ወይም በእሳት ወዘተ የተሰየሙትን ጣዖታት ብቻ አይደለም። ከእነዚህ ሌላ በሰዎች የሚመለኩ እጅግ ብዙ ጣዖታት አሉ። አንዳንድ ሰዎች ኃይላቸውን ያመል ካሉ። ሌሎችም ሥልጣናቸውን የተ ቀሩት ደግሞ ክብራቸውን፣ ገንዘባ ቸውን፣ ውበታቸውን ወዘተ. ያመል ካሉ። በየፊናቸው የየራሳቸው ጣዖታ ትና አማልክት አሏቸው ማለት ነው። ነገር ግን ሁሉም ሰዎች ‹በእውነት አንዱን እግዚአብሔርን እናመልካ ለን። በእርሱም እናምናለን› ሲሉ ይሰማሉ።

በቀደምት ዘመናት የነበሩ ሰዎች ከፍርሃት ወይም ከመጠን በላይ በሆነ ፍቅር፣ አሊያም ለጥቅም ሲሉ እንግዳ አማልክትን ያመልኩ እንደነበረ ታሪክ ያስረዳል። በእነርሱ አመለካከት ጥሩና መጥፎ የሚሏቸው አማልክትም ነበሯ ቸው። ጥሩ ከሚሏቸው ጥቅምን ፍለጋ፣ መጥፎ የሚሏቸውን ደግሞ በመፍራት ያመልኳቸው ነበር። ለም ሳሌ ታላላቅ ነገሥታትን ለጥቅም ሲሉ፣ መናፍስትን፣ ታላላቅ ወንዞች ንና ፏፏቴዎችን፣ እሳትን ወዘተ. ደግሞ በመፍራት ያመልካሉ። መላ.3፥8–14። ቀጥሎ የአምልኮ ዓይነቶችን በዝርዝር እንመልከት።

1. ገንዘብን ማምለክ

ገንዘብ ብዙ ሰዎች የሚያመል ኩትና የእግዚአብሔርን አምላክነት የሚቀናቀን ጣዖት ነው። ስለዚህም መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በተራራው ስብከቱ ለሁለት ጌቶች መገዛት የሚቻለው ማንም የለም ወይም አንዱን ይጠላል ሁለተ ኛውንም ይወዳል ወይም ወደ አንዱ ይጠጋል ሁለተኛውንም ይንቃል። ለእግዚአብሔርና ለገንዘብ መገዛት አትችሉም» በማለት ነግሮናል። ማቴ.6፥24

ማንም እግዚአብሔርን አመልካ ለሁ እያለ ገንዘብን ከመጠን በላይ የሚያፈቅር ከሆነ ራሱን ያሞኛል። ይህም የገንዘብን መገልገያነት መቃ ወም አይደለም። የገንዘብ አገል ግሎትም ቢሆን ደግሞ ለአምልኮ ጣዖትና ለገቢረ ኃጢአት ከዋለ ገንዘብ አምላክ ሆኖ እየተመለከ ነው ማለት ነው።

በይበልጥ ደግሞ በአንዳች አገልግ ሎት ላይ ሳያውሉ ገንዘብን በማከማ ቸት የሚረኩ ሰዎች ለገንዘብ የተገዙና ገንዘብን አምላካቸው ያደረጉ ናቸው። እንደዚህ ዓይነት ሰዎች የሳንቲም ሽራፊ እንድትወድቅባቸው የማይሹና በፈቃዳቸውም ገንዘብን የማይሰጡ (የማይመፀውቱ) ናቸው። እንዲህ የሚያደርጋቸውም ፍቅረንዋይ ነው። ገንዘብን ከማንም በላይ ስለሚወዱ እንደጣዖት ያመልኩታል። ጌታችን «ለእናንተ በምድር ላይ መዝገብ አትሰብስቡ» ሲል የተናገረው ለዚህ ነው። ማቴ.6፥19።

የሰው ልጆች የሆንን እኛም የገን ዘብ ፍቅር ወደልቡናችን እንዲገባና እንዲሠለጥን ከፈጣሪአችንም ጋር እንዲያጣላን መንገድ ከመክፈት በጽኑ ልንጠነቀቅ ይገባል። አንድ አባት መንፈሳዊ ልጃቸውን ሲመክሩ «ገን ዘብ ካለህ በሥራ ላይ አውለው። ገን ዘብ ከሌለህ ግን ምንም አትሰብስብ» ማለታቸው አደገኛነቱን የሚያስረዳ ነው።

2. መልካም ያደረጉልንን ማምለክ

ብዙ ሰዎች ውለታ የዋለላቸውን ሰው ያመልካሉ። ወይም ፈጽመው ይገዙለታል። ይህ ሰው ከሚከፋ እግዚ አብሔር ቢያዝን መልካም እንደሆነ ይቆጥራሉ። አንድ ደራሲና ገጣሚም «ለሰዎች መልካምን አድርግ ልቡና ቸውንም የአንተ ታደርጋለህ» ሲል የተናገረው በመልካም ሥራቸው በሌ ሎች ዘንድ የሚመለኩትን ለመጥቀስ ነው። መልካም የምንሠራው ግን የሌሎች ገዦች ላመሆን ብለን መሆን የለበትም።

መልካም ላደረገልን መልካም ውለታ መዋል ከሰብአዊነታችንና

የእግዚአብሔር ሕግ
ካለፈው የቀጠለ
ከዲ/አሸቱ ታደሰ

©ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org

ከክርስትናችን ሕግ የተነሣ የሚጠበቅብን ከመሆኑ በቀር መልካም የሠሩልንን ሰዎች እንደፍጹማን አማልክት ቆጥረን በደባልነት ልናመልካቸው ደግሞ የማይገባ መሆኑን ማስተዋል ያስፈልጋል። ለመልካም ሥራቸው ሰማያዊ ዋጋ ከእግዚአብሔር ማግኘት ሲገባቸው በውዳሴ ከንቱ ተይዘው ድካማቸውን እንዳያስቡ እንቅፋት በመሆን በምድራዊ ዋጋ ሰማያዊውን በረከት እንዲያጡ እኛ ምክንያት ከመሆን መጠበቅ አለብን።

3. ዝናን ማምለክ

አንዳንድ ሰዎች በሚገባ ወይም በማይገባ ነገር ለዝናቸው ወይም ለሚያውቁት ሰው ዝና ሲሟገቱ ይታያሉ። የራሳቸውን ወይም የሚሟገቱለትን ሰው ስህተት በመሸፈን ጥፋቱን ከቤተ ክርስቲያን ከሕዝብ ወይም ከመንግሥት በላይ አድርገው ዝናውን ለመጠበቅ ይጥራሉ። መሳሳታቸውን ወይም የሚሟገቱለት ሰው ስህተት መፈጸሙን ቢያውቁም ስለምድራዊ ዝና ሲሉ እውነትን ይደብቋታል። ይህ ደግሞ ለዝና መገዛትና ዝናን ማምለክ ነው። ጸሐፊው ስለዝና የሚሟገቱትን አስመልክቶ «የባልንጀራ ዓይን ለስህተት የተደፈነች ናት። የጠላት ዓይን ግን እያንዳንዱን ጥፋት ትገልጣለች» ብሎአል። የዚህ ዓይነቱ ባልንጀራ ጠቃሚ አይደለም። ጥፋቴን ዓይቶ ካልነገረኝ እንድስተካከልም ካልመከረኝ ለባዶነቱ ቢሟገትልኝ በመጨረሻ ከውድቀቴ ሊያነሣኝ አይችልምና አይረባኝም። «እውነተኛ ባልንጀራ መስተዋት ነው» ይባል የለ።

ለሰው ዝና ተብሎ ‹እውነት› መሥዋዕት መሆን የለባትም። ለጥቅም ተብሎም የሰው ዝና መጠበቅና የሐሰት ተሟጋች መሆን አይገባም። ስለዚህ ነገርም መጽሐፍ «ኃጥኡን የሚያጸድቅን በጻድቁ ላይ የሚፈርድ ሁለቱ በእግዚአብሔር ዘንድ አስጠያፊዎች ናቸው» ብሏል። ምሳ.17፥15። እውነትን ስለዝና መለወጥ የእውነት አምላክና እውነት የሆነውን እግዚአብሔርን ክዶ ባለዝና የሆነውን ሰው ማምለክ ነው። ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ «እኔ መንገድ እውነት ሕይወትም ነኝ» ብሏልና እውነትን ለዝና መለወጥ ጣዖትን ከእግዚአብሔር መጣላት ነው። ዮሐ.14፥6።

ለእግዚአብሔር የሚገባውን ክብር ለሰው የሚሰጥ ከእግዚአብሔር ይልቅ ሰውን ያመልካል። እግዚአብሔርን ከማስደሰት ይልቅ ሰውን በማይገባ ነገር የሚያስደስት የሚያስደስተውን ያመልካል። ለእግዚአብሔርም ከመታዘዝ ይልቅ ለሰው የሚታዘዝ ሰው የታዘዘለትን ያመልካል። ቅዱስ ጳውሎስም «ሰውን ወይስ እግዚአብሔርን አሁን እሻ አሰኛለሁን? ወይም ሰውን ደስ ላሰኝ እፈልጋለሁን? አሁን ሰውን ደስ ባሰኝ የክርስቶስ ባሪያ ባልሆንኩም።» በማለት መናገሩ ለዚሁ ነው። ገላ.1፥10።

ማንም ሰው ቢሆን የሚያደርገውን ነገር ሁሉ በንጹሕ አእምሮ እግዚአብሔርን ብቻ ለማስደሰት ማድረግ አለበት። ለእግዚአብሔር የሚገባውን ፍቅር አክብሮትና አምልኮት ለማንም ሳይለውጥና ማንንም ሳያወድስ ጎሊና ውን ክዶ ለሌሎች ዝና ሳያጎበድድ በተገቢው መንገድ መኖር አለበት። አለበለዚያ «ከእኔ በቀር ሌሎች አማልክት አይሁኑልህ» ያለውን የእግዚአብሔር ትእዛዝ እንዴት ማክበር ይችላል?

4. መሪዎችን ወይም ታላላቆችን ማምለክ

መጽሐፍ ቅዱስ «ለዋኖቻችሁ ታዘዙና ተገዙ። እነርሱ ስለነፍሳችሁ ይተጋሉ» ይላል። ዕብ.13፥17። ይህ የሐዋርያው አባባል ታዘዙአቸው አታምፁባቸው እንጂ በእግዚአብሔር ፈንታ አምልኳቸው የሚል አይደለም። መሪዎችንም ሆነ መንፈሳዊ አባቶችን ለመሪነታቸውና ለአባትነታቸው በሚገባው መጠንና ወሰን በመታዘዝ ልንገዛላቸው ከሚገባ በቀር ከእግዚአብሔር ጋር አወዳድረን ልናመልካቸውና ከፈጣሪአችን የሚያጣላን ትእዛዝ በሚያዝዙን ጊዜም በጆ ብለን ልንቀበላቸው አይገባም።

መሪ ወይም አባት ከሚገባው መንገድ የወጣ እንደሆነ ከበታቹ ያለውም የግድ ተከትሎት እንዲሄድ ሕግ አልተሠራም። መንፈሳውያን መሪዎችና አባቶች የነበሩት እነ አርዮስ፣ መቅዶንዮስ፣ ንስጥሮስ አውጣኪ የመሳሰሉት ከእውነት ባፈነገጡ ጊዜ መንፈሳውያን ልጆቻቸውም አብረው አላፈነገጡም። ከሃይማኖት የሚያወጣ፣ ከምግባር የሚለይ ሥራቸውን መንፈሳውያን ነበሩ ብለው አልተቀበሉትም አወገዙት እንጂ። «ከሰው ይልቅ ለእግዚአብሔር ልንታዘዝ ይገባል» ተብሏልና። የሐዋ. 5፥29። ከእግዚአብሔር ይልቅ የእነዚህን መናፍቃን ትምህርት አምላካቸው ያደረጉት ጠፍተዋል—ተለይተዋል።

ከጎሊና ጋር የሚቃረን ለእእምሮ የማይመች የሰውን የማንነት ሚዛን ያለፉ እንዲሁም እግዚአብሔርን ከማምለክ ጋራ የሚጋጭ መታዘዝ እግዚአብሔር የሚሻው አይደለም። ሰው ውስጣዊ ሰላሙን የሚያናጋውን ከራሱ ነፃ ጎሊና ጋር የሚያጣላውን፣ ሃይማኖቱንና የክርስትና ሕይወቱን የሚፈታተነውን ትእዛዝ እንዲቀበል የእግዚአብሔር ፈቃድ አይደለም። መንፈሳዊ መሪና አባትም የእግዚአብሔር እንደራሴ በመሆኑ የመንፈሳዊ ልጁን ውስጣዊ ሰላም የሚያናጋ፣ መንፈሳዊ ቅድስናውን የሚያደፈርስና የሚፈታተን ትእዛዝ ማዘዝ የለበትም። ይህን መሰሉ ሥራ አባታዊ አይደለምና።

ስለዚህ ታላላቆችንና መሪዎችን በሚገባ መጠን መታዘዝ እንጂ ማምለክ፣ ከእግዚአብሔር ሊያጣላ የሚችል ትእዛዛቸውንም መቀበል አይገባም። ታላቅነታቸው የልጆችን መንፈሳዊም ሆነ አካላዊ ችግር የሚያቃልል እንጂ በራሱ ችግር መሆን የለበትም። ይህም ከፍርሃት የተነሣ ወደ አምልኮ ሊለወጥ ይችላልና።

ወለ እግዚአብሔር ስብሐት ይቅጥላል

©ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org

ትንሣኤ ሙታን

ክብርሃኑ ጉበና

ሰው ሙቶ ከፈረሰ ከበሰበሰ በኋላ በእግዚአብሔር ፈቃድና ከሃሊነት አካል ሠርቶ ነፍስ ዘርቶ ሕያው ሆኖ ይነሣል። ሥጋና ነፍስ በመጨረሻው ዘመን እንደገና ተዋሕደው ዳግመኛ በማይፈርስና በማይበሰብስ ሥጋ የሚነሡ መሆናቸውን የሚገልጸው የቤተ ክርስቲያን እምነትና ትምህርት ትንሣኤ ሙታን ይባላል።

ስለ ትንሣኤ ሙታን ስናነሣ በቅድሚያ ልንገነዘበው የሚገባን ነገር አለ። ይኸውም የሰውን ተፈጥሮ ነው። ሰው በስድስተኛ ቀን በዕለተ ዓርብ «ሰውን በመልካችን እንደ ምሳሌ ያችን እንፍጠር» ዘፍ.1፥26። በሚለው አምላካዊ ቃል መሠረት ከአራቱ ባሕርያተ ሥጋና ከሦስቱ ባሕርያተ ነፍስ የተፈጠረ ነው።

ሥጋ ሟች ፈራሽ በስባሽ ሲሆን ነፍስ ግን እንደ መላእክት ፍጹም፣ የማትሞት፣ የማትፈርስ፣ የማትበሰብስ፣ ዘወትር ሕያው ሆና የምትኖር ናት። የነፍስን ሕያዊት መሆንም መጻሕፍት በየስፍራው ይመሰክራሉ።

«ሥጋንም የሚገድሉትን ነፍስን ግን መግደል የማይቻላቸውን አትፍሩ ይልቅስ ነፍስንም ሥጋንም በገሃነም ሊያጠፉ የሚቻለውን ፍሩ» ማቴ. 10፥28። ከዚህ አባባል የምንረዳው አንድ ሰው ሞተ ሲባል የሚሞተው ሥጋ መሆኑን ነፍስ ግን የማትሞት መሆንዋን ነው።

«ጌታ ኢየሱስ ሆይ ነፍሴን ተቀበል...» የሐዋ.7፥59 በማለት ቅዱስ እስጢፋኖስ ነፍሱን ፈጣሪው እንዲቀበልና በክብር ሥፍራ እንዲያኖራት መጠየቁ የሥጋና የነፍስን ልዩነት ይገልጽልናል።

«በሥጋ ሞተ በመንፈስ ግን ሕያው ሆነ በእርሱም ደግሞ ሄዶ በወኅኒ ለነበሩት ነፍሳት ሰበከላቸው» 1ጴጥ.3፥19።

ጌታ በዕለተ ዐርብ በአካለ ነፍስ ወደ ሲኦል ወርዶ በሲኦል ላሉት ነፍሳት ነጻነትን ማወጁን ቅዱስ ጴጥሮስ ገልጾልናል። ነፃነትን የሰበከው ለሞቱት ሰዎች ሥጋ ሳይሆን ነፍስ ነው።

«...እርስዋም ስትሞት ነፍስዋ በምትወጣበት ጊዜ...ዘፍ.35፥16። ስለ ራሔል ሞት በተገለጸበት በዚህ ስፍራ የሞትን ትክክለኛ ትርጉምና የነፍስን ሕያውነት መረዳት ይቻላል።

ሞት ማለት የሥጋና የነፍስ መለያየት ነው። የራሔል ነፍስ ከሥጋዋ መለየትዋ ተገልጿአል።

ታላቁ ነብይ ኤልያስም ትመግበው የነበረችውን መበለት ልጅ ከሞት ሲያስነሣው «አቤቱ አምላኬ ሆይ የዚህ ብላቴና ነፍስ ወደ እርሱ ትመለስ ዘንድ እለምንሃለሁ» ብሎ ነበር የጸለየው። ነገ.17፥19–23። በዚህም የብላቴናው ነፍስ በአጸደ ነፍስ እንደነበረችና ሞትም የሥጋና የነፍስ መለያየት መሆኑን ያስገነዝበናል።

የጌታ ወንድም የሚባለው ያዕቆብ ምግባርና ሃይማኖት የተዋሐዱ መሆናቸውን በምሳሌ ሲገልጽ «ከነፍስ የተለየ ሥጋ የሞተ እንደሆነ እንዲሁ ደግሞ ከሥራ የተለየ እምነት የሞተ ነው» ብሏል። ያዕ.2፥26። በዚህም ሞት ማለት የነፍስ ከሥጋ መለየት መሆኑን አረጋግጦልናል።

ከነፍስ የተለየው ሥጋ እስከ ጊዜ ምጽአት በመቃብር ፈርሶ በስብሶ እንደሚቀር መጻሕፍት በየስፍራው ዘግበዋል።

«ደመና ተበትኖ እንዲሄድ እንዲሁ ወደ ሙታን ሥፍራ የሚወርድ አይወጣም ወደ ቤት ደግሞ አይመለስም ሥፍራውንም አያውቀውም እንዲሁም ሰው ከተኛ በኋላ አይቆምም ሰማይ እስኪያልፍ ድረስ (ምጽአት እስኪሆን) በሥጋው ከእንቅልፉ አይነቃም አይሰማም» ኢዮብ.7፥9–10፤ ኢዮብ.14፥12–24።[1]

ከላይ በተገለጸው መሠረት ሰው በሥጋው በመቃብር ውስጥ እስከ ዕለተ ምጽአት ድረስ እንደ እንስሳት ፈርሶ በስብሶ እንደሚቆይና በዕለተ ምጽአት ግን ሥጋው፣ አጥንቱ፣ ጅማቱ፣ የራስ ቅሉ ባለበት ሥፍራ ተሰብስቦ ሕያዊት ነፍስ ተዋሕዳው እንደሚነሣ ነው።

ጌታችንና መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በእርሱ ያመኑ ሁሉ የክብር ትንሣኤ እንደሚነሱ ሲያስተምር «እኔም ከምድር ከፍ ከፍ ባልኩ ጊዜ ሹሉን ወደ እኔ እስባለሁ» ብሏል። ዮሐ.12፥32። በዚህ ተስፋ መሠረት የክብር ትንሣኤ ተነሥተን በዘለዓለም ሕይወትና ክብር ከሱ ጋር እንኖራለን።

በኩረ ትንሣኤ

«አሁን ግን ክርስቶስ ላንቀላፉት በኩራት ሆኖ ከሙታን ተነሥቷል። ሞት በሰው በኩል ስለ መጣ ትንሣኤ ሙታን በሰው በኩል ሆኖአልና። ሁሉ በአዳም እንደሚሞቱ እንዲሁ ሁሉ በክርስቶስ ደግሞ ሕያዋን ይሆናሉና። ነገር ግን እያንዳንዱ በራሱ ተራ ይሆናል ክርስቶስ እንደ በኩራት ነው በኋላም በመምጣቱ ለክርስቶስ የሆኑት ናቸው» 1ቆሮ.15፥20–24።

ፍርድ ሰጪው ፍርድ ተቀባዩ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ «ሰውነቴን አሳልፌ ለሞት ልስጣት በመቃብር ልጣላት ዳግመኛም ላስነሣት ሥልጣን አለኝና በፈቃዴ ሰውነቴን ለበጎች ቤዛ አድርጌ ለሕማም ለሞት አሰጣታለሁ ዳግመኛ አስነሣታለሁ» ዮሐ. 10፥14–18። ባለው ቃል መሠረት አስገዳጅ ሳይኖርበት በሰውነቱ የወደደውን ሊያደርግ ያሰበውን የተና ገረውን ለመፈጸም ፈቱን ለጽፋት፣ ጀርባውን ለግርፋት፣ ራሱን በበትር ለመመታት፣ የሾክ አክሊል ለመቀ

©ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org

ዳጀት፣ አፉን ለመሪር ሐሞት፣ እጅና እግሩን ለችንካር፣ ጕኑን ለጦር በፈቃዱ ሰጥቶ ለካዱት ለሰቀሉት «ባለማወቅ ይሠራሉና አባት ሆይ ኃጢአታቸውን ይቅር በላቸው» ብሎ ከጸለየላቸው በኋላ «አባት ሆይ ነፍሴን በአንተ እጅ አሰጣለሁ» ብሎ በታላቅ ድምፅ ጮኾ ቅድስት ነፍሱን ከቅዱስ ሥጋው በገዛ ሥልጣኑ ለየ። ዮሐ.19፥1–30።

በዚህ ጊዜ ምድር ተናወጠች፣ አዕባን ተፈተኩ፣ መቃብራት ተከፈቱ፣ ከቅዱሳን ወገን ብዙ ሙታን ተነሡ። የቤተ መቅደስ መጋረጃ ተቀደደ። ማቴ.27፥47–53።

ሦስት መዓልት ከሦስት ሌሊት በከርሰ መቃብር አድሮ ሞትና መቃብርን፣ ኃጢአትና ሰይጣንን ከሥልጣናቸው ሽሮ፣ በክብር ተነሥቶ አዳምንና ልጆቹን ከእሥራታቸው ፈታቸው።[2]

የትንሣኤ ሙታን ማስረጃ በመጽሐፍ ቅዱስ

በመጽሐፍ ቅዱስ ስለ ትንሣኤ ሙታን መናር በተለያየ ስፍራ ተጽፎ ይገኛል። ዐበይት ነቢያት ከሚባሉት ውስጥ አንዱ የሆነው ነቢዩ ዳንኤል የሙታንን መነሣት አስመልክቶ ሲያስተምር «በምድር ትቢያ ውስጥ ካንቀላፉት ብዙዎች ይነቃሉ፤ እኩሌቶቹ ወደ ዘላለም ሕይወት እኩሌቶቹም ወደ እፍረትና ወደ ዘለዓለም ጕስቁልና» ዳን.12፥2።

ነቢየ እግዚአብሔር ኢሳይያስም «ሙታንም ሕያዋን ይሆናሉ። ሬሳዎችም ይነሣሉ። በምድር የምትኖሩ ሆይ ጠልህ የብርሃን ጠል ነውና ምድርም ሙታንን ታወጣለችና ንቁ ዘምሩ» ብሏል። ኢሳ.26፥19።

ጌታችንም በመዋዕለ ትምህርቱ የሙታን ትንሣኤ እንዳለ ሲያስተምር «በመቃብር ያሉት ሁሉ ድምፁን የሚሰሙበት ሰዓት ይመጣል መልካም ያደረጉ ለሕይወት ትንሣኤ ክፉም ያደረጉ ለክፉ ትንሣኤ ይወጣሉና» ብሏል ዮሐ.5፥28።

ብርሃነ ዓለም ቅዱስ ጳውሎስ ለተሰሎንቄ ሰዎች በላከው ክታቡ የሙታንን መነሣት አስመልክቶ ሲጽፍላቸው «ኢየሱስ እንደሞተና እንደ ተነሣ ካመንን እንዲሁም በኢየሱስ ያንቀላፉትን እግዚአብሔር ከእርሱ ጋር ያመጣቸዋልና» ብሏል 1ተሰ.4፥14።

ይኸው የቤተ ክርስቲያን የንጋት ኮከብ ቅዱስ ጳውሎስ ለቆሮንቶስ ክርስቲያኖች ስለ ትንሣኤ ሙታን አበክሮ ሲያስገነዝባቸው «ሁሉ በአዳም እንደሚሞቱ እንዲሁ ሁሉ በክርስቶስ ደግሞ ሕያዋን ይሆናሉና...እንዲያማ ካልሆነ ስለ ሙታን የሚጠመቁ ምን ያደርጋሉ? ሙታንስ ከቶ የማይነሡ ከሆነ ስለ እነርሱ የሚጠመቁ ስለምን ድር ነው? በጌታችን በክርስቶስ ኢየሱስ ባለኝ በእናንተ ትምክህት እየማልሁ ወንድሞች ሆይ ዕለት ዕለት እሞታለሁ። እንደ ሰው በኤፌሶን ከአውሬ ጋር ከታገልሁ ሙታንስ የማይነሡ ከሆነ ምን ይጠቅመኛል። ነገር ግን ሰው ሙታን እንዴት ይነሣሉ? በምንስ ዓይነት አካል ይመጣሉ? የሚል ይኖር ይሆናል። አንተ ሞኝ አንተ የምትዘራው ካልሞተ ሕያው አይሆንም። የምትዘራውም ስንዴ ቢሆን ከሌላም ዓይነት የአንድ ቢሆን ቅንጣት ብቻ ነው እንጂ የም ትዘራው የሚሆነውን አካል አይደ ለም። እግዚአብሔር ግን እንደወደደ አካልን ይሰጠዋል...» 1ቆሮ. 15፥20–58።

የሙታን አነሣስ እንዴት ነው?

የሞትህ ተነሥ የሚል አዋጅ በመላእክት አለቃ በቅዱስ ሚካኤል ይታወጃል። «ጌታ ራሱ በትዕዛዝ በመላእክት አለቃ ድምፅ በእግዚአ ብሔር መለከት ከሰማይ ይወርዳልና» 1ኛተሰ.4፥16።

የመጀመሪያው ረቂቅ ነጋሪት ሲመታ አውሬ የበላው ነፋስ የበተነው፣ ያለቀው የደቀቀው ሁሉ ራሱ በፈረሰበት ቦታ ላይ ይሰበሰባል[3]

ሁለተኛው ረቂቅ ነጋሪት ሲመታ አጥንትና ሥጋ ተዋሕደው ሳይንቀሳቀስ ትኩስ በድን ይሆናል። አጥንቶችና ጅማቶች ከሥጋና ከደም ጋራ ይያያዛሉ። እስኪነሡ ያለመንቀሳቀስ ፍጹም በድን ይሆናሉ።

ሦስተኛው ረቂቅ ነጋሪት ሲመታ በቀዋሚ አካል በምትናገር አንደበት ከራስ ጠጕራቸው እስከ እግር ጥፍራቸው ከቁጥር ሳይጐድሉ ከሰውነታቸው ሳይከፈሉ ወንድ በአቅመ አዳም የሠላሳ ዓመት ጕልማሳ፣ ሴት በዐቅመ ሔዋን የአሥራ አምስት ዓመት ቆንጆ ሆነው በጎም ይሁን ክፉ ሥራቸውን ይዘው ይነሣሉ። ጌታ ራሱ እንደተናገረው በጐቹን በቀኝ ፍየሎቹን በግራ ያቆማቸዋል። ማቴ.25፥31–46።

በበግና በፍየል የተመሰሉት እነማን ናቸው?

ጻድቃን በበግ፣ ኀጥአንን በፍየል መሰሎአቸዋል። እንዴት ተመሰሉ?

ሀ. በጐች በደጋ እንጂ በቆላ አይኖሩም። ደጋ ብርድ ውርጭ ያለበት ቢሆንም በጎች ይህን ይቋቋማሉ ጻድቃንም በመከራ ሥጋ እንጂ በተድላ ደስታ ለመኖር ሲሉ ሃይማኖታቸውን ለወርቅ ለብር ብለው አይለውጡም። ፍየሎች በቆላ እንጂ በደጋ አይኖሩም ኀጥአንም በተድላ ደስታ ለመኖር ሲሉ ሃይማኖታቸውን ለወርቅ ለብር ብለው ይለውጣሉ።

ለ. በጐች እረኛቸው ባሰማራቸው ሥፍራ እንደሚገኙ ጻድቃንም እረኛቸው ክርስቶስ ባሰማራቸው በአንዲት ሃይማኖት ጸንተው ይኖራሉ። ፍየሎች ግን እረኛቸው ባሰማራቸው ሥፍራ ጸንተው አይቆዩም። እንዲሁ

©ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org

ሲባዝኑ አረኛቸውንም ያደክሙታል ኃጥአንም እንዲሁ በሃይማኖት በምግባር ጸንተው አይቆዩም።

ሁሉም በየግብሩ ይነሣል

አንዳንድ ሰዎች የሙታን ትንሣኤ መኖሩን ያምኑና ጻሩ ግን ጻድቃንና ኃጥአን በስህተት ተቀላቅለው አይነሡምን? የሚል ጥያቄ ሲጠይቁ ይሰማሉ። ሁሉም በየግብሩ ይነሣል እንጂ ጻድቁ ኃጥአ ኃጥኡ ጻድቅ ሆኖ አይነሣም። ጻድቃን በምድር ላይ ሳሉ በሠሩት የጽድቅ ሥራ እንደ ፀሐይ አብርተው እንደ ጨረቃ ደምቀው ይነሣሉ። ለዚህም በምሳሌነት የምን ጠቅሰው ኑግና ስንዴን ነው።

ኑግና ስንዴ በአንድነት ተቀላቅለው በአንድ መሬት ላይ ቢዘሩ ኑግ ኑግ ሆኖ ቢበቅል እንጂ ስንዴ ሆኖ አይበቅልም። ስንዴውም ስንዴ ሆኖ ቢበቅል እንጂ ኑግ ሆኖ አይበቅልም።

አውሬ የበላቸው ወንዝ የወሰዳቸውስ እንዴት ይሆናሉ? እነዚህም ቢሆኑ አይቀሩም። ይነሣሉ። ከትንሣኤ የሚቀር ሰው የለም። አውሬ የበላው ሰው ሥጋው ከአውሬው ሥጋ ተለይቶ ይነሣል። ለዚሁ ማስረጃ የሚሆንን የአፈርና እህል ተቀላቅሎ መዘራት ነው። አፈርና እህል በአንድነት ቢዘራ አፈሩ እዚያው ሲቀር እህሉ ግን ይበቅላል። አውሬ የበላቸው የሰዎች ሥጋም በትንሣኤ ወቅት በእግዚአብሔር ትእዛዝ የሰዎቹ ሥጋ ከአውሬው ሥጋ ተለይቶ ሲነሣ የአውሬው ሥጋ ግን ትንሣኤ ስለሌለው ፈርሶ በስብሶ ይቀራል መክ.3፥21።

ስለ ትንሣኤ ሙታን የሥነ ፍጥረት ምሳሌ

ለትንሣኤ ሙታን ምሳሌ የሚሆኑ ከሥነ ፍጥረታት በኩል ብዙዎች ናቸው። ከነዚህ ውስጥ ጥቂቶቹ እንደሚከተለው ተገልጸዋል።

የሐኩራ የተባለ ትል አለ። ይህ ትል በሚሞትበት ጊዜ ራሱን ከጉድፍ ውስጥ አግብቶ ይቀብረዋል። ከራሱ ከበሰበሰ በኋላ እንደገና ሕያው ሆኖ ይነሣል።

ፈልፈል የተባለው ፍጥረት በተወለደ በሰባተኛው ወሩ ይሞታል። እንደገናም ሕያው ሆኖ ይነሣል።

ፈንቆን የተባለ በዓረብ አገር የሚገኝ ዎፍ አለ። ይህ ዎፍ ብዙ የሚያስደንቅ ነገር አለው አምስት መቶ ዓመት ይኖራል። ከአምስት መቶ ዓመት በኋላ የሚሞትበት ጊዜ መድረሱን ያውቃልና በክረምት ወራት ብዙ አበባዎችን አከማችቶ ተሸክሞት ወደ ግብጽ ይመጣና (ኤሊዮስ) ከተባለው ቦታ ላይ ይቀመጣል። ከዚህ በኋላ ደረቱን በከንፉ አራግቦ ሲመታው ከሰውነቱ ውስጥ እሳት ይወጣል።

የበሰበሰውን አበባ ሲያቃጥለው ከእሳቱ ውስጥ ገብቶ አጥንቱ ሳይቀር መላ አካሉ ተቃጥሎ አመድ ይሆናል። ከዚህ በኋላ በእግዚአብሔር ትእዛዝ ደመና ደምኖ ዝናም ይዘንምና የተቃጠለበት እሳት ይጠፋል። በዚህ ጊዜ ከአካላቱ የማይቃጠል አንድ ክፍል አለና ለአንድ ቀን ይሸታል። ወድያውም ከሥጋው ውስጥ ትል ይወጣል። ትሉም ክንፍ አውጥቶ አካል ይሠራና በሦስተኛው ቀን ፉፍቶና አድጎ በአቅራቢያው ላሉት ሰዎች ይታያቸዋል። ቀስ በቀስ አካላቱ ሲጠነክር ተመልሶ ወደ አገሩ ወደ ዓረብ ይመለሳል።[4]

ቀጥሏል

የዉ መጽሐፍ
1. ዝክረ ሃይማኖት፣ ገጽ 163
2. የኢትዮጵያ እምነት ወግስቱ ሕግጋት፣ ገጽ 172
3. ያዕቆብ ዘሥሩግ፣ ቁ. 91
4. መርሐ ጽደቅ ሳሕለ ሃይማኖት፣ ገጽ 27።

እርማት

ባለፈው የሐመር መጽሔት ዕትማችን (4ኛ ዓመት ቁ.1) ላይ በወጣው የአንደራቻ መድኃኔዓለም ገዳም ታሪክ ላይ የተፈጠሩ አንዳንድ ስህተቶችን እናርም ዘንድ በደቡብ ኢትዮጵያ ሕዝቦች ክልል የካፈቶ ዞን ባህልና ስፖርት መምሪያ እና መ/ር ተመስገን በቀለ (ከቦንጋ) የላኩቸው ደብዳቤዎች ደርሰውናል። ስሕተቶቹ የተፈጠሩት በታይፕ ስሕተት ምክንያት መሆኑን እየገለጽን ለተፈጠሩትም ስሕተቶች ይቅርታ እንጠይቃለን።

ማስተካከያ

ገጽ	አንቀጽ	መስመር	ግድፈት	ማስተካከያ
14	1	3	የከኾና	የካፈኾና
14	2	3	ዲንቻና ግቻ	ባርታና ግቻ
14	2	11	የበርታ	የባርታ
14	3	6	1932	1532
14	3	6	ገዳመ	ገደማ
14	3	8	የጊዲ	የጊዳ
14	8	10	በተርልቹ	በተርበቾ

©ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org

አዲስ ኪዳን በብሉይ ኪዳን

(ክፍል ሁለት –ካለፈው የቀጠለ)

ሊ/ደጀኔ ሽፈራው

የተወደዳችሁ አንባቢያን እንደምታስታውሱት ባለፈው እትማችን በዚህ ርእስ መነሻነት ብሉይ ኪዳን ለአዲስ ኪዳን አምላልና መርገፍ መሆኑን በሚገባ ተመልክተናል። በዚህም ሁሉ አዲስኪዳን ለብሉይ ኪዳን ትርጓሜ፤ ብሉይ ኪዳን ለአዲስ ኪዳን መነሻ፣ አዲስ ኪዳን ደግሞ ለብሉይ ኪዳን መድረሻ ነው ወደሚለው መደምደሚያ ደርሰናል። በዛሬውም ጽሑፋችን ለመመልከት የምንሞክረው ካለፈው የቀጠለ ይሽንኑ የተመለከተ ነው።

‹እንግዲህ በመብል ወይም በመጠጥ ወይም ስለ በዓል ወይም ስለ ወር መባቻ ወይም ስለ ሰንበት ማንም አይፍረድባችሁ። እነዚህ ሊመጡ ያሉት ነገር ጥላ ናቸውና። አካሉ ግን የክርስቶስ ነው።› ይላል ቆላ.2፥16። ከዚህ ጥቅስ መብል መጠጥ፤ በዓል መባቻ ሰንበት የተባሉትን አራት ነገሮችን እንመለከታለን።

ቅዱስ ጳውሎስ ለቆላስይስ ሰዎች ይህንን ያለምክንያት አልጻፈላቸውም። ቢጽ ሐሳውያን (ውሸተኞች ወንድሞች) ወደዚህች አገር ገብተው ወንጌል ያለ አሪት አትረባም አትጠቅምም ብለው አውከዋቸው ስለነበረ ለዚህ ብሎ ጽፎላቸዋል። ይሁን እንጂ የተጻፈበትን ምክንያት እና ዓላማ ያልተረዱ ሰዎች መብል መጠጥ የሚለውን ከጾም፣ በዓል የሚለውን ከቤተ ክርስቲያን መንፈሳውያን በዓላት ጋር ወዘተ...በማመሳሰል ቤተ ክርስቲያናችንን ሲተቹ ይደመጣሉ። መምህራንን ጠይቀው ከመረዳት ይልቅ ምሥጢሩ ባልገባቸው ጥቅሶች ምእመናንን ግራ ያጋባሉ።

ቅዱስ ጳውሎስ ለቆላስይስ ሰዎች ለመንገር የፈለገው በብሉይ ኪዳን ዘመን በአይሁድ ዘንድ ይደረግ የነበረውን እና አሁን ደግሞ ምን መሆን እንዳለበት ነው። ዘጸ.12፥14–20፤ 23፥10–19፤ 34፥18፤ 35፥1–31 ዘዳ.15፥1፤ 16፥1–16፤ ዘሌ.21፥1–4።

1ኛ. ‹ስለ መብል መጠጥ ማንም አይፍረድባችሁ› የተባለው አይሁድ እንደ አሪቱ ሥርዓት በፋሲካ (በቂጣ) በዓል የቦካ ለምን ይበላል? እያሉ ያስቸግሩ ስለነበረ ነው። ሌላው ደግሞ አይሁድ ውኃቸው የኩሬ ነው፣ ጉድፍ የወደቀበት እንደሆነ ያንን ጠርገው ጥለው ርኩስ እስከ ሰርክ ይሉ ስለነበረ ለዚህ የተነገረ ነው። የአዲስ ኪዳን መብል መጠጥ ነፍስ የተለየው መለኮት የተዋሐደው የክርስቶስ ሥጋና ደም ነውና በዚህ መሠረት ዋነኛውና ምሥጢራዊው መልእክት እናንተ መለኮት የተዋሐደውን ሥጋውን እንበላለን፣ ደሙንም እን ጠጣለን በምትሉበት ጊዜ ፈጽመው ያላመኑ ሰዎች ክርስቶስ ዕሩቅ ብእሲ እንጂ አምላክ ወልደ አምላክ አይደለም፣ ደግሞም የሰው ሥጋ ደም ቢበሉት ቢጠጡት ደዌ ይሆናል እንጂ ከፍዳ ያነጻልን? እያሉ አይፍረዱ ባችሁ (እያሳንፏችሁ) ማለቱ ነው። ምክንያቱም ጌታ ስለሥጋውና ደሙ ሕይወትነት ባስተማረ ጊዜ አይሁድ ይህ ሰው ሥጋውን ልንበላ ይሰጠን ዘንድ እንዴት ይችላል? ደግሞም የሰው ሥጋ ቢበሉ ደዌ ይሆናል እንጂ ሕይወት ይሆናልን? ይሁንስ ቢባል የአንድ የእሱ ሥጋ ለአእላፈ እሥራኤል ይበቃልን? ብለው ነበርና። ዮሐ.6፥52። ሌላው ቀርቶ ደቀ መዛሙርቱ እንኳ «ይህ የሚያስጨንቅ ንግግር ነው ማን ሊሰማው ይችላል?» እስከማለት ደርሰው ነበረ። ዮሐ.6፥60።

2ኛ. ‹ስለ በዓል ማንም አይፍረድባችሁ፤› የተባለው ደግሞ እሥራኤል በብሉይ ኪዳን የሚያከብሯቸው ታላላቅ መንፈሳውያን በዓላት ነበሯቸው እነዚህም።

- የሰንበት በዓል ዘሌ.23፥2።
- የቂጣ በዓል (ፋሲካ) ዘዳ.12፥1–20፤ ዘሌ.23፥5–8።
- የመከር በዓል (ሰዊት) ዘዳ. 23፥16፤ 34፥22፤ ዘኍ. 28፥26፤ የሐዋ.2፥1።
- የዳስ በዓል ዘሌ.23፥26–32።
- ፋሪም (በአስቴር ዘመን) አስቴ. 9፥16–28 ናቸው።

እንግዲህ ቅዱስ ጳውሎስ በዓል ያለው ከሰባቱ በዓላት አንዱ የሆነውን የቂጣን በዓል ፋሲካን ነው። ይህም በሚያዝያ ወር እሥራኤል ዘሥጋ ከግብፅ የወጡበትን ዕለት እንዲያ ከብሩ በመታዘዙ የሚያከብሩት በዓል ነው። ዘዳ.12፥14–20። በዓሉም ራሱን የቻለ የራሱ የሆነ ሥርዓት አለው። በአዲስ ኪዳን ግን እስራኤል ዘነፍስ ለምንባል ክርስቲያኖች ፋሲካችን የክርስቶስ ትንሣኤ፣ ከግብፅ መውጣትም ከሲኦል መውጣት ነውና ለዚህም ነው ሐዋርያው

©ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org

ፋሲካ ብላችሁ የክርስቶስን ትንሣኤ በምታከብሩ በእናንተ ግንም ስለቂጣ በዓል አይፍረድባችሁ ያላቸው። ምሳሌነቱ ግን እንዳለ ነው። ይህም:-

- ከነዓን፣ የገነት ምሳሌ ናት፣
- ግብፅ፣ የሲኦል ምሳሌ ናት፣

እሥራኤል ወደ ግብፅ መውረዳቸው፣ ነፍሳት ወደ ሲኦል የመውረዳቸው ምሳሌ ነው።

የምድረ ግብፅ መከራ፣ የ5500 ዘመን የሲኦል መከራ ምሳሌ ነው።

እሥራኤል ከሞተ በኩር የዳኑ በት–ነውር የሌለበት በግ፣ የኢየሱስ ክርስቶስ ምሳሌ ነው። 1ቆሮ.6፥7፤ ዮሐ.1፥29።

እሥራኤል የበጉን ደም የቤቱን መቃን መቀባታቸው፣ የክርስቶስ ደም በመስቀል ላይ ለመፍሰሱና ክርስቲያኖች በክርስቶስ ደም የመታተማቸው ምሳሌ ነው።

እሥራኤል በእሳት የተጠበሰውን ሥጋ መብላታቸው፣ ክርስቲያኖች ነፍስ የተለየውን እሳተ መለኮት የተዋሐደውን ሥጋ የመብላታቸው ምሳሌ ነው።

እሥራኤል ከመራራ ቅጠል ጋር መብላታቸው፣ ክርስቲያኖች 18 ሰዓት ጾመው ለአፋቸው ምረት ሲሰ ማቸው የመቁረባቸው ምሳሌ ነው።

3ኛ. ‹መባቻ› የተባለው ደግሞ በብሉይ ኪዳን ፀሐይ ልክ ሳትገባ ጨረቃ ተወልዳ በከፊል የምትታ ይበት ቀን መባቻ እየተባለ ይከበር ነበረ። ይህም የወር መጀመሪያ ቀን ነበረ። ቀኑም የተቀደሰ ነው። ነቢዩ ዳዊት በመዝሙሩ «በረድኤታችን በእግዚአብሔር ደስ ይበላችሁ፣ ለያዕቆብም አምላክ እልል በሉ ዝማሬውን አንሡ፣ ከበሮውንም ስጡ፣ ደስ የሚያሰኘውን በገና ከመሰንቆ ጋር፤ በመባቻ ቀን በከፍተኛው በዓላችን ቀን መለከትን ንፉ፤ ለእሥራኤል ሥርዓቱ ነውና።» መዝ.80፥1–4። እያለ የዘመረው ለዚህ ነበር። እንደ ዳዊት መዝሙር መባቻ ታላቅ በዓል ተብሏል። በአዲስ ኪዳን ግን ለእሥራኤል ዘነፍስ ክርስቲያኖች ታላላቅ በዓሎቻችን ዘጠኝ ናቸው። እነርሱም 1ኛ. ብሥራት ሉቃ.1፥26–38። 2ኛ. ልደት ሉቃ.2፥1–20። 3ኛ. ጥምቀት ማቴ.3፥13–17። 4ኛ. ደብረ ታቦር ማቴ.17፥1–8። 5ኛ. ሆሳዕና ማቴ.21፥1–17። 6ኛ. ስቅለት ማቴ.27፥1–61። 7ኛ. ትንሣኤ ዮሐ.20፥1–18። 8ኛ. ዕርገት ሉቃ.24፥50፤ የሐዋ.1፥9። 9ኛ. ጰራቅሊጦስ የሐዋ.2፥1። ናቸው። ሌሎቹም መንፈሳውያን በዓላት እግዚአብሔር በቅዱሳን አድሮ ታላላቅ ሥራዎችን የሠራባቸው ዕለታት ናቸው።

4ኛ. ‹ስለ ሰንበት ማንም አይፈርድባችሁ› የተባለውም ስለ አይሁድ የሰንበት አከባበር ነው። ሰንበት በዕብራይስጥም የቃሉ ትርጉም ማቆም መተው ማለት ነው። እስራኤል ሰባተኛውን ቀን ለእግዚአብሔር እንዲቀድሱት በአሠርቱ ቃላት ታዝዘዋል። ዘዳ.20፥8–11። ሰንበት በእግዚአብሔርና በሕዝቡ ዘንድ ምልክት በመሆኑ ሰንበትን አለማክበር ከባድ ቅጣት ያስከትል ነበር። ዘዳ.31፥17፤ ዘኍ.15፥32–36። ሰንበት የእግዚአብሔር ሥራ እንዲታወስ ያደርጋል፣ በመጀመሪያ እግዚአብሔር ስድስት ቀን ሠርቶ በሰባተኛው እንዳረፈ ሁሉ ሰውም በዚህ ዓለም መንፈሳዊ ሥራ ሠርቶ በመጨረሻው ቀን ወደ ዘላለም ዕረፍት እንደ ሚገባ ያመለክታል። ዘፍ.2፥2፤ ዘዳ.20፥11 እሥራኤል ወደ ዕረፍት አገራቸው ሲደርሱ አሠርቱ ቃላት በድጋሚ ተነገራቸው።

እስራኤል ቀኑን በሚገባ ባለማክበራቸው በነቢያት ተወቅሰዋል፣ ሕዝ.20፥12–16፤ አሞ.8፥6። እንዲያከብሩትም ተስፋ ተሰጥቷቸዋል። ኢሳ.56፥2–4። 58፥13–14። ነህምያ ሰንበትን አስከብሮአል ነህ.10፥31፤ 13፥15–22። ኢየሱስ ክርስቶስም የሰንበት ጌታዋ ሲሆን ሰንበትን አክብሮአል ማቴ.12፥1–14፤ ሉቃ.4፥16።

ስለ ሰንበት ክብር የአይሁድ ሊቃውንት ብዙ ዓይነት አተረጓጐም ነበራቸው። «አክብር» የሚለውንም ቃል ለእግዚአብሔር እንደሚስማማ አድርገው ለመተርጐም ያላዩት መዝገበ ቃላት የለም። ካህናቱም ሆኑ ሕዝቡ በዚህች ዕለተ ሰንበት ሥር መማስ፣ ቅጠል መበጠስ ይቅርና የዘረጉትን አያጥፉም፣ ያጠፉትንም–አይዘረጉም፤ የዘጉትን–አይከፍቱም፣ የከፈቱትንም አይዘጉም ነበር። አይሁድ በዕለተ ሰንበት ወደ ሽንት ቤት እንኳ አይሄዱም ነበር። ከዚህም ጋር ቤት ቢቃጠል፣ ሰው ቢሞት፣ ጦር ቢመጣ፣ በዕለተ ሰንበት ከሆነ መንቀሳቀስ ክልክል ነው። ለምሳሌ በመቃብያን ታሪክ እንደሚታወቀው 36 ሺህ አይሁዳውያን በወራሪ ጦር በአንድ ቀን ያለቁት በዚህች በዕለተ ሰንበት ነበር። ለዚህም ነው ቅዱስ ጳውሎስ እንደዚህ አድርጋችሁ ካላ ከበራችሁ ብሎ ግንም አይፍረድ ባችሁ ያለው። ጌታ በወንጌል እንደ ተናገረው በሰንበት መልካም መሥራት ተፈቅዶአልና። ማቴ.12፥12። መልካም የሚባለው ደግሞ መንፈሳዊ ሥራ ነው። ጌታ እጁ የሰለለችበትን ሰው ማቴ.12፥10፤ ሆዱ የተነፋውንም ሰው የፈወሰው በሰንበት ነው። ሉቃ.14፥2። መጻጉዕንም የፈወሰው በሰንበት ነው። ዮሐ.5፥10። ከመወለዱ ጀምሮ ዕውር የነበረው

©ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org

ብላቴናም ፈውስ ያገኘው በዚሁ ዕለት ነበረ። ዮሐ.9፥14።

በቤተ ክርስቲያናችን ቅዳሜንና እሑድን እንደ አንድ ቀን አድርገን አስተካክለን እናከብራለን። የቅዳሜ መከበር በብሉይ ኪዳን የታዘዘ ሲሆን እሑድ ደግሞ ጌታ ከሙታን ተለይቶ ስለተነሣበት «የጌታ ቀን» ተብላ በአዲስ ኪዳን የከበረች ናትና ነው። ራእ.1፥10። አከባበራችንም እንደ አይሁድ አይደለም። ፍትሐ ነገሥት 19 ላይ ‹ለክርስቲያን እንደ አይሁድ ዕለተ ሰንበትን ማክበር አይገባም። ለክርስቲያን እንደሚገባ በመንፈሣዊ ሥራ ተጠምዶ ማክበር ይገባል እንጂ› ይላል። ቅዱስ አትናቴዎስም በቅዳሴው ‹ዕለተ ሰንበት የዕረፍት ቀን ናት ሲባል በደዌ እንደተያዘ ሰው ከአልጋ ተጣብቆ ተኝቶ በመዋል አይደለም። የዕለቲቱ ወዳጆች ለመሆን በመሣልትም በሌሊትም ለመንፈሳዊ ሥራ በመትጋት ነው እንጂ› ብሏል። በመሆኑም በመዝሙር፣ በቅዳሴ በመንፈሳዊ ጉባኤ፣ የታሠረ–በመጐብኘት፣ የታመመ–በመጠየቅ፣ ለድኾች በመመጽወት፣ የተጣላ በማስታረቅ ወዘተ. ማክበር ይገባል።

5. በመጨረሻም ቅዱስ ጳውሎስ «እነዚህ ሊመጡ ያሉት ነገሮች ጥላ ናቸውና» ማለቱ ይህ ይመጣ ዘንድ ላለው ወንጌል አምሳል እና መርገፍ ነውና ማለቱ ነው። «አካሉ ግን የክርስቶስ ነው» የተባለውም ቤተ ክርስቲያን የክርስቶስ መሆኗን የሚያመለክት ነው። ምክንያቱም በእግዚአብሔር ደም (የሐዋ.20፥28) በኢየሱስ ክርስቶስ ደም ላይ የተመሠረተች ቤተ ክርስቲያን የክርስቶስ አካሉ ናትና ፊል.3፥14።

6. «ትሕትናንና የመላእክትን አምልኮ እየወደደ ባላየውም ያለፈ ታድ እየገባ በሥጋዊም አእምሮ በከንቱ እየታበየ ማንም አይፍረድባችሁ» ይላል። ቆላ.2፥18። ይህንንም ቀጥታ የሚያገናኙት የመላእክት አማላጅነት እና ተራዳኢነት አያስፈልግም ከሚለው ጠማማ አሳባቸው ጋር ነው። መላእክት የተባሉት እነማን ናቸው? አምልኮ የተባለውስ ምንድን ነው?

ሐዋርያው ‹መላእክት› ያላቸው የአይሁድን ረበናት (ሊቃውንት) ነው። ቅዱስ እስጢፋኖስ ‹በመላእክት ሥርዓት ሕግን ተቀበላችሁ› ያላቸው ለዚህ ነበር። የሐዋ.7፥53። ቅዱስ ጳውሎስም በሮሜ መልእክቱ ‹መላእክትም ቢሆኑ› ያላቸው ምድራውያን ሹማምንትን ነበረ ሮሜ. 8፥38። በዮሐንስም ራእይ ላይ የሰባቱ አብያተ ክርስቲያናት አለቆች ሥጋ የለበሱ ሰዎች መሆናቸው ይታወቃል። ነገር ግን መላእክት ተብለዋል። ራእ.1፥20፤ 2፥1–18፤ 3፥1–7። በአንጻሩም መላእክት የእግዚአብሔር ልጆች፣ ሰው የተባሉበትም ጊዜ ነበረ። ኢዮ.1፥6፤ 2፥1። ኢያ.5፥13። በተጨማሪም «ገናም በጸሎት ስናገር አስቀድሜ በራእይ አይቼው የነበረው ሰው ገብርኤል እነሆ እየበረረ መጣ።» እንዲል ዳን.9፥20። እንግዲህ ቃሉ እንዲህ ይበል እንጂ ገብርኤል መልአክ እንጂ ሰው እንዳልሆነ በግንም ዘንድ የተረጋገጠ ነው። ያም ባይሆን እየበረረ የሚለው ቃል መልአክ መሆኑን ያረጋግጥልናል። በወንጌልም መልአኩ ቅዱስ ገብርኤልን በእግዚአብሔር ፊት የሚቆመው ይለዋል ሉቃ.1፥11፤ 19፥26።

‹አምልኮ› ለአምላክ ብቻ የሚሰጥ ነው። ይህም ስግደትን፣ ውዳሴን፣ አክብሮትን፣ መገዛትን፣ ጸሎትን፣ መሥዋዕትን፣ መልካም ሥራን፣ ፍርሃትንና ፍቅርን ወዘተ...በጠቅላላው የአምልኮ ሥርዓትን ያጠቃልላል። የአምልኮ ሥርዓት ለአምልኩ የመገዛት ምልክት ነውና። ቅዱስ ጳውሎስ ግን አምልኮ ያለው ሥርዓተ ረበናትን ነው። ይኸውም በብሉይ ኪዳን ዘመን የነበረውን የአይሁድን የበዓላት አከባበር ሥርዓት ነው።

በሌላ በኩልም ቅዱስ ጳውሎስ ትሕትናን የጠቀሰው ትሕትና አያስፈልግም ማለቱ ሳይሆን ‹ማንም በተየውሆ፣ በመለዘብ፣ ራስን በማታለል አያታልላችሁ› ማለቱ ነው። መናፍቅ ሌላውን ሲሰብክ ራሱን አታልሉ በማስመሰል ትሕትና ነውና። «ነገር ግን ወንድሞች ሆይ እናንተ የተማራችሁትን ትምህርት የሚታወሙትን መለያየትንና ማሰናከያን የሚያደርጉትን ሰዎች እንድትመለከቱ አለምናችኋለሁ። ከእነርሱ ዘንድ ፈቀቅ ብሉ፣ እንዲህ ያሉ ለገዛ ሆዳቸው እንጂ ለጌታችን ለኢየሱስ ክርስቶስ አይገዙምና፣ በመልካምና በሚያቆላምጥ ንግግርም ተንኮል የሌለባቸውን ሰዎች ልብ ያታልላሉ።» እንዲል ሮሜ.16፥17።

በሥጋዊም አእምሮ በከንቱ እየታበዩ በሌሎች ይፈርዱ የነበሩትም አይሁድ ናቸው። ጌታም በወንጌል የገሰጻቸው ለዚህ ነበር ማቴ.23፥1–39። ስለ ፍርድም «እንዳይፈረድባችሁ አትፍረዱ በምትፈርዱበት ፍርድ ይፈረድባችኋልና። በምትሰፍሩበትም መስፈሪያ ይሰፈርባችኋል። በወንድምህም ዓይን ያለውን ጉድፍ ስለምን ታያለህ? በዓይንህ ግን ያለውን ምሰሶ ስለምን አትመለከትም? ወይም ወንድምህን ከዓይንህ ጉድፍ ላውጣ ፍቀድልኝ እንዴትስ ትለዋለህ? እነሆም በዓይንህ ምሰሶ አለ። አንተ ግብዝ አስቀድመህ ከዓይንህ ምሰሶውን አውጣ። ከዚያም በኋላ ከወንድምህ ዓይን ጉድፉን ታወጣ ዘንድ አጥርተህ ታያለህ።» ማቴ.7፥1–5። ብሏቸዋል። እንግዲህ ከዚህ የምንማረው ዛሬ ሁሉም ራሱን ፍጹም አድርጎ በእምነታም በሥርዓቷም ጉድፍ የማይገኝባትን ቤተ ክርስቲያን ከብቦ ከመተቸትና ከመዘበት ይልቅ በዓይኑ ያለውን ምሰሶ (ታላቅ ክህደት እና በደል) ማስወገድ ይገባዋል። ግብዝነት አያዋጣምና። የእግዚአብሔር ቸርነት የድንግል ማርያም አማላጅነት አይለየን። አሜን። ✥

(ይቀጥላል)

©ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org

ሒነ—ጥቦ

አባ በቀኝ እጃቸው የያዙትን መስቀል በግራ እጃቸው መዳፍ ላይ እየጠበጠቡ ያስባሉ። ይተክዛሉ። ከገዳሙ ፊት ለፊት ካለው ትልቅ ዋርካ ሥር ወድቆ ያገኙትን እንግዳቸውን ተሸክመው ካስገቡት ጀምሮ ግንኙቱንና ከየት እንደመጣ ለማወቅ እንደጓጉ ናቸው። ያንን የግብፅ በረሃ አቋርጦ፣ የቀን ሐሩሩን፣ የሌት ቁሩን ታግሦ የደረሰውን ወጣት በጥሞና ይመለከቱታል። ግንባሩን በነጭ ጨርቅ ሸብ አድርጎ አሥሮታል። በአጭሩ የተቆረጠው ላዛ ፀጉሩ ወደ ግምባሩ ደፋ ብሎ ደጋፊ ያጣ የወይን ሐረግ መስሏል። ቀጭን ሰውነቱ ከወንድነት ይልቅ ወደ ሴትነት ያደላል። እርሳቸው በዚህ ሀሳብ ተመስጠው ሳሉ ያለፈ ድካሟ ያልለቀቃት ሶልያናም እንደ ከበዳት ሁሉ ጭንቅላቷን በመዳፏ ይዛ ትቆዝማለች። ከዝምታ ጋር ያበረው ጨለማም አንዳች ግርማ ተላብሦ የነገሠ ይመስላል። በመሀሉም አባ ጉሮሮዋቸውን ጠራረጉ ‹ምነው ዝም ተባባልን?› ለማለት። «ለመሆኑ ቤተሰቦችህን ትተህ ለመውጣት ያስገደደህ ነገር ምንድር ነው?» አሉ። ከየት የመጣህ እንግዳ ነህ ለማለት የፈለጉ ይመስል። ቀና ብላ ተመለከተቻቸው። ግንባራቸው ድረስ ደፋ ያለችው ቆብ በሽበት ከተወረረው ረጅም ሪዛቸው ጋር ተዳምሮ አዛውንት አስመስሏቸዋል። ሰውን በጥልቀት የሚያዩት ዓይኖቻቸው ውስጣዊ ማንነትን የሚመረምሩ ይመስላሉ። አይኗን ከዓይናቸው ነቅላ ወዳሳለፈቻቸው ዓመታት ገባች— ሶልያና። ታሪኳን ከየት ጀምራ ትንገራቸው? ፈደል ሲያስቆጥራት፣ ጽሕፈት ሲያስተምራት፣ የወንጌልንም ቃል፣ የክርስትናን ፍቅር በልቧ የሳለውን የምሥኪኑን የዕዝራንም ታሪክ ትንገራቸው? ከራሷ ጋር ከተሟገተች በኋላ እንዲህ ትላቸው ገባች።

...አባቷ በላዕላይ ግብፅ በገንዘብ ወዳድነታቸው ይታወቁ፣ አምጣ እንጂ እንካን የማያውቁ መቀበል እንጂ መስጠት ያልለመደባቸው ዘረ—ነዌ፣ ገንዘብ የሚገኝበት ከሆነ ምንም ነገር ከማድረግ የማይመለሱ ንፉግ ናቸው። ‹ገንዘብ ክብር ነው። ገንዘብ ዘመድ ነው። ገንዘብ ወገን ነው› ብለው ገንዘብን መርጠው ሰውን የተዉ ናቸውና ለሀብታቸው ስሱ መሆናቸው ደስታ እየፈጠረላቸው ራሳቸውን ባሰቡ ቁጥር በልባቸው ይስቃሉ። የእርሳቸው እምነት፣ መታመኛቸው ገንዘብ ነው። ገንዘብ ካለ ሁሉ ነገር አለ የሚለውን አባባል መመሪያቸው ያደረጉ ነበሩ። የሰማዩን ደስታ በምድሩ የለወጡ፣ የምድር ክብር ያሸነፋቸው መሆናቸው የሚያሳዝነው የሶልያናን ልብ ብቻ ነበረ።

ሶልያና

(ካለፈው የቀጠለ)

በተቀመጠችበት ሆና የዓመታት የታሪክ ክር ሲጠነጠን የአባቷ ያለፈ ሕይወትም በየተራው ያልፍ ገባ። ገንዘብ...አባት...ክብር...ዝና...ሁሉም የሶልያናን ልብ ያቆሰሉ ጦሮች ናቸው።

«አየሽ ሶልያና» ይሏታል አባቷ ከልጅነቷ ጀምሮ «አየሽ ገንዘብ ካለሽ ሁሉ ያከብርሻል። ሁሉ ይገዛልሻል። ጉልበት የሌለሽ ደካማ ብትሆኚም እንኳን ገንዘብና ሀብት ከንድ ይሆኑሻል። ባለሽ ጊዜ ሁሉ ወዳጅሽ፣ ሁሉ ታዛዥሽ ነው። ስለዚህም የሰውን ልብ በፍቅር ለመግዛት ከመሽቀዳደም፣ ወጪትሽን በገንዘብ ለመሙላት ጣሪ። ከዚያ በኋላ እንዲወድሽ የምትፈቅጂን ሰው በገንዘብሽ ትገዢ ዋለሽ። ፈቃዱን በሀብትሽ ታስለው ጪዋለሽ» ያሏት ሁሉ አንድ በአንድ ትውስ አላት። እንደ ነጭ ወረቀት ንጹህ በሆነው የልጅነት አእምሮዋ ላይ የሳሉባት የሀብትና የክብር ፍቅር በሚምሀሯ በዕዝራ የጥበብ ቃላት ተፍቆ ባይጠፋ ኖሮ አባቷን ተከታታይ የምትኖር ሆና በቀረች ነበር።

በጠባቡ የተከፈቱት ዓይናቿ በፊቷ የተቀመጡትን አባት መመልከት አቁመው የዓመታት የታሪክ ድር ማጠንጠን ይዘዋል። ልብ እንጂ ዓይን መቼ ያይና። ቀጠለች ሶልያና—ታሪኳን።...«...አባቷ በአገራቸው በገንዘቡ ወደር ያልተገኘለትን ሀብታም ወዳጃቸውን በእህቷ ፍቅር አስነድፈው ሀብቱን የጠቀሉበት ምሥጢር ትዝ አላት። የልጃቸውን እጅ ይዘው ሊሰጡት፣ ወዳጅነታቸውን በጋብቻ ማጎተምነት ሊያፀኑት ቃል ገቡለት። የሞቀ ትዳር፣ የሰላ ንብረት ለመመሰረት የቋመጠውን ሀብታም በሴት ፍቅር ዓይኑን አሳውረው ወደሚታረድበት ቦታ መሩት»። በመጨረሻም ትዳር በመሠረቱ ዓመት ከመንፈቅ የልጃቸውን ባል በመርዝ አሰናብተው ከአባቷ ፈቃድ የማትወጣ ልጃቸውና ተቆጥተው ሀብቷን ጠቀለሉት።

አባ አጋቶን ‹በታፈሩና በተከበሩ ቤቶች ዙሪያ ያለው ኃጢአት ብልጭ አለላቸው። ከሀብት በስተጀርባ የሚፈስ ደም፣ የሚጠፉ ነፍሳት ስንት ይሆኑ?› የሚል ሀሳብ መጣባቸው። ነገር ግን የሶልያና ንግግር የበለጠ እንዳይሄዱ ገታቸውና ጆሮዋቸውን ወደ እርሷ አደረጉ። ...ዛሬም ያለፈውን ታሪክ ሊደግሙ አባቷ ሶልያናን ታራጁ በሬ ፊት የሚቀርብ አሞሌ ጨው አድርገው ሲያዘጋጇት እምቢ አለች። የመሀሯ የዕዝራን ቃል አስታወሰች። «ጊዜያዊ ደስታን ለዘለዓለማዊ ደስታ የሚለውጥ ሰው ታላቅ ሰው ነው» ያላት ትዝ አላት። ለሚታረደው በሬ ቢላዋ ላለመሳል አሻፈረኝ ብላ ተቃውሞዋን ገለጸች። እናም ገንዘብ እንጂ ፍቅር፣ ጥርጥር እንጂ እምነት፣ ጠብ እንጂ ሰላም ከሌለበት ቤት አመለጠች። በምድራዊ ክብር የተከበበን ኃጢአት፣ በወርቅ ጽዋ የተሞላን ርኩሰት አሸነፈች። ይህንን ለመወሰን ግን ብዙ ሌሊቶችን ያለ እንቅልፍ ለማሳለፍ ተገዳ ነበረ።

©ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org

ምድራዊ ተድላና ደስታ በአንድ በኩል፣ የእግዚአብሔር ቃል ደግሞ በሌላ በኩል ውጊያ ገጥመው ነበርና። የአባቷን ቃል ብትፈፅም፣ ታፍራና ተከብራ በምድር ላይም የፈለገችውን አድርጋ እንደምትኖር ታስባለች። በሌላ በኩል ደግሞ ዕዝራ «ሰው ዓለሙን ቢያተርፍ ነፍሱን ግን ቢያጎድል ምን ይጠቅመዋል?» ያላት ይመጣባታል። መውጫ ቀዳዳ ማም ለጫ መንገድ ብታጣ ያንኑ መከረኛ እንባዋን ትጠራዋለች።

«መተከዣ መሸሽጊያዬ፣
መረጋጊያ ጓደኛዬ፣
አንተ ናልኝ ዕንባዬ።»

እያለች ታጫውተዋለች። ዙሪ ያው ገደል ሲሆንባት ዕንባዋ ድልድይ እንደሆነ ሁሉ በርሱ ትረጋጋበታለች። ለጸሎት ስትቆምም ዕንባዋ ከእንደበቷ ይቀድምና የልቧን ይነግርላታል — ለአምላኳ። ደስ ይላታል፥ ስታለቅስ ‹የደም አረቄ› የሆነ መስዋዕቷን— ዕንባዋን—ስታቀርብ። እናማ መልሱን አገኘችው ‹ጨክኚ ሶልያና› አላት ውስጧ። ‹የነገን እግዚአብሔር ያውቅልሻል፣ ወይ በርባንን አሊያም ኢየሱስን ምረጪ። በደም የሚመጣውን ሀብት፣ በወንጀል የሚገኘውን ንብረት ግፈው። መምህርሽ ዕዝራ ስለ ዮሴፍ የነገረሽን አስታውሺ። የይሁዳን ሠላሳ ብር አሽቀንጥረሽ ወርውሪው። አትጠቀሚበት። የደም መሬት— አኬልዳማ—የሚገዛበትን ወርቅ እምቢ በዪው» አላት። እና ወሰነች።

በኃጢአት የሚገኝ ክብርንና ሀብትን ንቃ በእውነት የሚገኝ ድህነትን መረጠች። ግን ወደየት ልትሄድ? አሁንም ሌላ ጥያቄ። መምህሯ ዕዝራ ምን ነበረ የሚላት? አዎ። «አብርሃም ከዑር ሲወጣ የት እንደሚሄድ መች ያውቅና? ቅዱስ ማርቆስስ ወደ ግብፅ ሲመጣ ምን ዘመድ ነበረው?» ነበረ ያላት። ‹አምላክ ማርቆስ አንተ ምራኝ› አለች። ያው ልማደ ጓደኛዋ— ዕንባዋ—አይዞሽ ይል ይመስል እየፎከረ መጣ። መንታ ሆኖ በጉንጮቿ ላይ ሊወርድ። መበደሏን ለአምላኳ ሊያስረዳላት—የደም አረቄዋ።

አባ አጋቶን ሶልያና የምትነግራቸውን ታሪክ ልቅም አድርገው ይሰማሉ። ታሪኩ የሚፈጥርባቸው የልብ መረበሽ ሲያይልም እነኚያ ትናንሽ ዓይኖቻቸውን ጨመቅ አያደረጉ ዕንባቸውን በመጐናፀፊ ያቸው ያደራርቁታል። በገዳመ ቆሮንቶስ ድል የተመታ የገንዘብ ፍቅር ዛሬ የቆሰለው ሰውነቱ አገግሞ ሰዎችን ወደ ገሃነም ሲያግዝ ታያቸውና ልባቸው በሀዘን ጦር ተወጋ። ከሁሉ በላይ ደግሞ ሴት ሆና ሳለ ሴትነቷ እንዳይገለጥባት እግዚአብሔር እንዴት እንደከለላት አሰቡና በልባቸው አምላካቸውን አመሰገኑ። የሰይጣንን ውጊያ ሸሽታ ወደ ሌላ የጦር ሜዳ የመጣችውን ይህችን ምሥኪን አተኩረው ተመለከቷት። ‹አንዱን ወጥመድ ያመለጠች ሌላ የሚጠብቃት ሚዳቋ› አሉ ለራሳቸው። ክርስትና ያለበትን መከራ ሊነግሯት፣ ሰይጣን ሰዎችን ከአምላካቸው ለመለየት የሚጠቀምበትን ጥበብ ሊያስረዷት ፈለጉ። ነገር ግን የዕድሜዋን ለጋነት በመንፈስም አለመበርታቷን ተመለከቱና ከምላሳቸው ጫፍ መለሱት። ልቡናቸው ግን አሁንም ማረፊያ ያጣችውን የኖህ ርግብ ይመስል ይበርራል...ይሄዳል... ይሽከረከራል። በክብርና በሀብት በታጠሩ ቤቶች ውስጥ የሚፈፀመውን ጉዳይ ይመለከታል። ገንዘብ ለማግኘት የሚደረገውን ኃጢአት ይተነትናል። «አይ ነዌ ዛሬም አትማርም። በበርህ ደጃፍ የወደቀውን አልአዛርን አትመለከተውም? ከኋላ ልቅሶ ዛሬ ሣቅን መቀነስን አትመርጥም?» ይላል ልባቸው። በፈንታዋ ሶልያናም በሀሳብ ማዕበል የሚዋኙትን አባ አጋቶንን ትመለከታቸዋለች። እርሳቸው ግን የሉም። የዓለምን ምሥጢር... በወርቅና በዕንቁ፣ በከበሩ ድንጋዮችም የተሸለመችውን ዓለም፣ ለዮሐንስ የተገለጠለትንም ድብቅ ስሟን ይመረምራሉ። እንደተለመነ መቃብር ያጌጠችውን ይህችን ዓለም። በመጨረሻ ርግቢቱ ወደመርከቧ ተመለሰች...አባም ወደልባቸው። ወደ እንግዳቸው ዘወር አሉ፣ ወደ ሶልያና።

በበነጋው ጠዋት ከጸሎት በኋላ የመለያያቸው ሰዓት መድረሱን ልባቸው ነግሯቸዋልና ሁለቱም በሃሳብ ተውጠው ዝም ብለው ቆዩ። አባ አጋቶን ለእንግዳቸው ዘላቂ ማረፊያ ሲያስቡ ሶልያና ደግሞ ከዚህ በኋላ ስለሚኖራት ሕይወት ስታሰላስል። ልቧን በእምነት አፅንታ የሚሆነውን ለመጠበቅ ስትቆርጥ ያወላዋይ ሥጋዋ ደግሞ አለሁ ብሎ ብቅ ይላል። እንዲህ ስትብሰከሰክ የአባ ንግግር ወደልቧ መለሳት።

«ምን አስበሻል ታዲያ የእኔ ልጅ?»

«ምኑንም አላውቀው አባቴ።»

በጭንቀት ላይ መሆኗን ለማወቅ ብዙም አልተቸገሩም። መልሷም ከዚህ ውጪ ሌላ ሊሆን እንደማይችል ገምተዋል። የራሳቸውን ሃሳብ ከማቅረባቸው በፊት የርሷኑ ማወቅ ስለፈለጉ እንጂ። «እንግዲህ ከዚህ ከገዳማችን ወደ ምሥራቅ የአንድ ቀን የእግር መንገድ ተጉዘን የሚገኝ ቤተ ክርስቲያን አለ። በዲቁና ያገለገልሁበት፣ የቤተ ክርስቲያንንም ትምህርት የተማርሁበት ነው። በዚያም አንድ ጥሩ አባት አሉ። ትዳር መሥርተው ልጆች ወልደው የሚኖሩ ጥሩ ካህን ናቸው። እኔንም አስተምረው ለዚህ ያበቁኝ እርሳቸው ናቸው። እግዚአብሔር ፈቅዶ የወደደውን እስኪያደርግ ድረስ በዚያ ትኖሪያለሽ። የአንድዬ ፈቃድ እንደ እኛ እንድትኖሪ ከሆነ ደግሞ ቀኑ በደረሰ ጊዜ ያመለክትሻል።» አሏት።

አየሩ ብቻ እንኳን መንፈስን ከሚያድሰው ሥፍራ ወደ ዓለሙ የምትቀላቀልበት ሰዓት ደረሰ። ነገር ግን መሆን አለበት። ወደ ምሥራቅ መጓዝ። በጥንቃቄ ሁኔታዋን ሲያጤኑ የነበሩት አባም ንግግራቸውን ካቆሙበት ቀጠሉ። «የአባትሽን ትክክል ያልሆነ ሕይወት ጠልተሽ እንደመጣሽ በዘመንሽም ሁሉ ኃጢአትን ራቂው።

©ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org

ባሪያሽ አድርጊው እንጂ ባሪያው አትሁኚ። ለሚያምን ሁሉ ይቻላልና ዓለምን በእምነትሽ አሸንፊ።» ብለው አንዲት ትንሽ የዛገች የብረት ሣጥን አስታቀፏት። አንዱ ሳጥኗን ሌላ ጊዜ ደግሞ አባን በመገረም ታስተውል ገባች። «ይቺ ሳጥን አባቴ በሞት መዳፍ ተይዞ በነበረ ጊዜ ያስረከበኝ ውርሱ ናት። እኔም የማወርሰው ስፈልግ ብዙ ጊዜ ተቀመጠች። ዛሬ ግን የምሥራቅ መንገደኛ...ስላገኘሁ ላወርስሽ ፈለግሁ» አሉ።

ሶልያና በሚንቀጠቀጥ እጁ ሳጥኑን ከፈተችው። ዓይንን በሚያጥበረብሩ የተለያየ ቅርፅ ባለው ወርቅ ተሞልቷል። ነገሩ ህልምም መሰላት። «ትቺው የመጣሁት ወርቅ» አለች። የተናገረችው ቃል ከአንደበቷ ወጥቶ ከአባ ጆሮ መድረሱን ግን አላወቀችም ነበረ። ይህ ግን ያለኃጢአት የተገኘ በዛገ ሳጥን ውስጥ የተቀመጠ ያልዛገ ሀብት—የአባት ውርስ ነው። ቀና ብላ ተመለከተቻቸው። ዕድሜ በተጫነው ሰውነት ውስጥ የማያረጅ...ዕድሜ የማይጫነውን እምነት... መንፈሳዊ ነትን ጥንካሬን ተመለከተች። ለካስ መምህሯ ዕዝራ የነገራት ይህንን ነውና! ክርስትናን ማንበብ ሳይሆን በአይን መመልከት። እናም ከወርቁ ይልቅ እምነታቸውን በልቧ ሳጥን ውስጥ ያኖሩ መሰላት።

እንደ ወርቅ ተፈትና ነጥራ እንድትወጣ መምከራቸው መሆኑ ገባት። ጀማሪ ብቻ ሳይሆን ፈፃሚም ለመሆን...ለመዝራት ብቻ ሳይሆን ለማጨድም...ለማጨድ ብቻ ሳይሆን ወቅቶ በጎተራ ለመክተትም...የወይን ተክል ለመሆን ሳይሆን ብቻ ለማፍራትም አደራ ተረከበች።

✣ ✣ ✣

አባን ተሰናብታ ስትወጣ የም ሥራቅ አድግስ አሳት ውስጥ የገባ የብረት አለሎ መስሎ አየችው። መምህሯ ዕዝራ ምን ነበረ ያላት? ...አዎ... «፬ሐየ ጽድቅ ኢየሱስ ክርስቶስ የሚመጣው በምሥራቅ ነው።...» እርሷም አሁን ወደ ምሥራቅ ልትጓዝ ነው በምጽአት የክብር ትንሣኤ እንድትነሳ። ወደ ብርሃን...ምሥራቅ...ክርስትና። ✣

ተረፈመ

ወስብሐት ለእግዚአብሔር

አንጢላርዮስ

አንጢላርዮስ ለተቸገረ የማያዝን፣ ለተራበ የማይራራና የማይሰጥ ንፉግ ባለጸጋ ሰው ነበረ። ከዕለታት በአንድ ቀን ነዳያን በመንገድ ተቀምጠው ሳለ አንጢላርዮስ ሲያልፍ አይተው ‹ይህ ጽኑ ጨካኝ ባለጸጋ፣ ለተቸገረ ሰው የማያዝን› ተባባሉ። ከመካከላቸውም አንዱ ግን «ሄጄ ሰጥቶኝ በልቼ ጠጥቼ ብመጣስ?» አላቸው። እነርሱም «አብልቶህ አጠጥቶህ አትመጣም። እንዲያውም አይሠጥህም» ሲሉ መለሱለት።

ነዳዩም በተወራረደው መሠረት ወደ ንፉጉ ባለጸጋ ሄደ። አንጢላርዮስ ምግብ አቅርቦ ለመመገብ ሲዘጋጅ ነዳዩ ደረሰ። ስመ እግዚአብሔርንም እየጠራ ከሚበላው ያካፍለው ዘንድ ይለምነው ገባ። የዝሆን ጆሮ ይስጠኝ ብሉ እንዳይተወው የሚጠራው የእግዚአብሔርን ስም ነው። በዚህም በጣም ተናድዶ በያዘው ዳቦ ወርውሮ ነዳዩን ፈነከተው። ከረሃብ የሚብስ ምንም የለምና ደሙን እያንጠባጠበ ዳቦውን አንስቶ በላ። ለምልክትም እንዲሆን ትንሽ ዳቦ አስቀርቶ ወደ ጓደኞቹ ተመለሰ።

በዚያች ሌሊት ባለጸጋው አንጢላርዮስ ራእይ አየ። ያየውም ራእይ እንዲህ ነበረ። ...ነፍሱ ከሥጋው ተለይታ መላእክተ ጽልመት እያዳፉ ይዘዋት ሲሄዱ፣ መላእክተ ብርሃንም ከኋላ ይከተሏት ነበረ። እርስ በርሳቸውም ሲነጋገሩ ‹እናንተ ከዚህች ነፍስ ምን አላችሁና ትከተሏታላችሁ አሉ – መላእክተ ጽልመት። መላእክተ ብርሃንም ‹ምነው ትናንት ለተራበ ድኃ አብልቶ የለምን?› ብለው ሲመልሱላቸው። ‹መታው እንጂ ለድኃው መቼ ሰጠው› በማለት ይከራከሯቸው ጀመረ። እንግዲያውስ ትክክለኛውን ፍርድ እንዲሰጥ ራሱ ነዳዩ ይጠራ ተባለ። ድኃውም ሲመጣ ‹ትናንት ያጠገብኸኝ ባለጸጋ ሆይ ከዚህ አመጡህን? ከረሃቤ ጽናት የተነሣ በትሩ አልታወቀኝም› ብሎ ሲመሰክር መላእክተ ብርሃን ከመላእክተ ጽልመት ነፍሱን ተቀበሏት...

በበነጋውም ‹በዚህ ዓለም ሳያውቁ የሰጡት ገንዘብ ይህንን ያህል ያስ ጠቀመ አውቀውና ወደው የሰጡትማ ምን ያህል ያስጠቅም› ብሎ ነዳያንን ሰብስቦ ያለ ገንዘቡንና ንብረቱን ሁሉ ጨርሶ ሠጥቶ (አከፋፍሎ) መንና መሄድ ጀመረ። በመንገዱም ገንዘብ መስጠቱን ሰምተው የመጡ ነዳያንን አገኛቸው። ርቧቸውና ጠምቷቸው ስለነበረ ተጨነቀ። «ገንዘብ የለኝም ነገር ግን ሽጡኝና በምታገኙት ገንዘብ ተጠቀሙ» አላቸው። ችግራቸው ለሰው ከማዘን በላይ ሆኗልና በሰላሳ ወቄት ሸጠው ገንዘቡን ተከፋፈሉ።

ወደ ግብፅ የወረደ ዮሴፍን በቸርነቱና በምሕረቱ የጐበኘው የቅዱሳን አምላክ እግዚአብሔር ከአንጢላርዮስም አልተለየም። እረኝነት በገባበት ቤት ሲያርስ ውሎ ግታ ከደረቅ ቦታ ሣር አለምልሞ፣ ከጭንጫ ዓለት ውኃ አፍልቆ ሲያር ሰባቸው የዋላቸውንና የሚጠብታቸውን ከብቶች ይመግብ ጀመረ። ይህንን ኃይለ እግዚአብሔር የሞላበትን ድንቅ ተአምር የተመለከቱ በሙሉ ያደንቁ ነበረ። የነድቃንን ክብር መገለጥ ልማዱ የሆነው እግዚአብሔርም ከተወለደ ጀምሮ ድዳ የነበረ እንዲሁም ምንም መስማት የማይችል ደንቆሮ በአንጢላርዮስ እስትንፋስ ድኅነተ ሥጋ እንዲያገኙ አደረገ። በዚህም ክብሩ ስለተገለጠበት ያንን አካባቢ ትቶ ኮበለለ። ምክንያቱም እግዚአብሔር በሰጠው ጸጋ መኩራት፣ ውዳሴ ከንቱን መፈለግ፣ አቦ...አቦ በሉኝ፣ አክብሩኝ» ማለት የእግዚአብሔር ሰዎች ጠባይ አይደለምና። በተጨማሪም ማንም ራሱን ከፍ ማድረግ ቢፈልግ ዝቅ ይበል የሚለውን ኃይለ ቃል ያረጋግጥልናል። ለታይታ፣ ስምን በዓለም ለማስነገር፣ በሥጋዊ ፈቃድ በመነሳሳት የማይፈጸም ምፅዋት ይህንን ወደመሰለ ክብር ያደርሳል። አንዳንዶች ለቤተ ክርስቲያን ሲረዱ፣ ለነዳያን ሲመጸውቱ ስማቸው ለመላው ምዕመን እንዲነገርላቸው፣ ሲሞቱ እንኳን ሌላው ከሚቀበርበት ሳይሆን ለእነርሱ ብቻ በተለየ ሥፍራ እንዲቀበሩ ይሻሉ። ይህ ሁሉ ግን ሥጋዊና ውጤቱም ውዳሴ ከንቱ ብቻ ነው።

«...ምጽዋት ስታደርግ ግብዞች በሰው ዘንድ ሊከበሩ በምኩራብ በመንገድም እንደሚያደርጉ በፊትህ መለከት አታስነፋ።...(ማቴ.6፥2)።✣

ወስብሐት ለእግዚአብሔር

©ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org

እናስተዋውቃችሁ

ደብረ ጽሙና ገዳም

ከመጋቢ ክንፈ ገብርኤል ተ/ማርያም

የደብረ ጽሙና ገዳም እንግዳውን ሊቀበል እንደወጣ አባወራ በግርማ ሞገስ በቆሙ ተራሮችና በተፈጥሮ ደን ተከቦ ታሪካዊነቱን እንደጠበቀ ዘመን በማይለውጠው የእግዚአብሔር ጥበቃ የተማመነ መሆኑን በሚያሳይ ድንቅ ውበት በምዕራብ ሸዋ በአድአ በርጋ ወረዳ ከሆለታ ገነት እንጪኒ 36 ኪ.ሜትር፣ ከእንጪኒ የሦስት ሰዓት የእግር መንገድ ርቆ የሚገኝ ጥንታዊ ገዳም ነው።

ይህ ቦታ በገዳምነት ከመታወቁ በፊትም ቢሆን በውስጡ ብዙ ቅዱሳን ተጠግተውበት እንደነበረ ገድለ ተክለሐዋርያትና በአካባቢው የሚነገረው ታሪክ ያረጋግጣሉ። ለምሳሌም ያህል አትናቴዎስ የሚባሉ አንድ ጳጳስ በተቀበሩበት ቦታ ላይ ታላቅ ዛፍ በቅሎበት እስከ ዛሬ አለ። የዛፉ ግንድ ዙሪያ ስፋት 42 ክንድ (21 ሜትር) ይሆናል። የእኝህ ጳጳስ አባት ታሪካቸውን ገድላቸው ባይታወቅም በአካባቢው የሚገኙ ምዕመናን በዚያ ቦታ የማኅሌትና የሰዓታት ድምፅ እንደሚሰማና አልፎ አልፎ ምሽት ላይ ብርሃን እንደሚታይ ይናገራሉ። እንዲሁም ከዛፉ ላይ የሚወድቀው ቅርፊት ወይም ደረቅ እንጨት ሲጨስ ጭሱ የአጋንንት በሽታ የለከፋቸውን ሁሉ እንደሚወስ አውንም ይታያል።

በገድለ ተ/ሐዋርያት ላይ አባታችን ቅዱሳንን ለመጐብኘት ለደብረ ሊባኖስ ወጥተው ሙገር ወደምትባል ሀገር ሲሔዱ በቆልት የሚባል ሥፍራ ካለች ቤተ ክርስቲያን ለመግባት እግዚአ–ክብራ የምትባል የእግዚአብሔር አገልጋይ አግኝተው ሲጨዋወቱ ጐል በምትባል ቦታ አትናቴዎስ የሚባሉ ጳጳስ ጳጳስ እንደተቀበሩ እንደነገረቻቸውና እሳቸውም ቦታውን እንድታሳያቸው እንደለመኗት፣ እርሷም ልጇን እንዲያሳያቸው መላኳ፣ ጳጳቁ አቡነ ተ/ሐዋርያትም ከልጁ ጋር በመቃብሩ ቦታ ሲደርሱ ለጳጳቁ መቃብር ሰግደው በአካባቢው ለሰባት ቀን እንደተቀመጡና በዚያም ቦታ ታላቅ ተአምር እንደተገለጸላቸው ተጽፎ ይገኛል።

በሸዋ ክፍለ ሀገር ልዩ ስሟ እና ርእት በምትባል ቦታ ተሹም የሚኖር እንድርያስ የተባለ ሰው ነበር። ለእርሱም እሌኒ የተባለች ሚስት ነበረችው። እሌኒና እንድርያስ ተጋብተው በቅድስና ሲኖሩ እሌኒ አቡነ ተ/ሐዋርያትን ፀንሳ ሳለች ወደ ወላጆቿ ሀገር ወደ ትግራይ ሔደች። በአካባቢዋም ማሪት የሚባል ጣዖት ይመለክ ነበርና በዓለ ማሪትን ለማክበር ውንድ ሴት ሳይባል ሁሉም እጅ መንሻቸውን ይዘው ይሔዱ ነበር።

በአንድ የማሪት በዓል ዕለት የሀገሯ ሰዎች እሌኒን አንቺ ለአምላካችን የማትሰግጂው ስለምንድነው? አሁን ተነሺ እጅ መንሻ ይዘሽ ትሰግጂያለሽ ብለው ይዘዋት ሔዱ። እሌኒ ወደ በዓሉ ቦታ ስትቃረብ ማሪት የተባለው ጣዖት ከሩቅ ያቺን ሴት አታምጡብኝ እያለ ይጮህ ጀመር። ታዳሚዎቹ በጠየቁትም ጊዜ በሆዱ የተሸከመችው የሚያቃጥል እሳት ነው። ስለዚህ እንዳትመጣ ከልክሉ ልኝ እያለ ጩኸቱን ቀጠለ። እሌኒም እየቀረበችው ስትመጣ በማኅፀንዋ ባለው ሕፃን ላይ ያለው መንፈስ አቃጥሎት እየተሰባበረ ነግሦ ከሚኖርበት ቦታ ጠፋ። በዚህም የተነሳ እሌኒና የአካባቢው ሰዎች የተደረገውን ነገር በማየት ከጣዖት አምልኮ ተላቀቁ፣ እግዚአብሔርንም አመሰገኑ። ጳጳቁ አቡነ ተ/ሐዋርያትም እንደ ዮሐንስ መጥምቅ በእናታቸው ማኅፀን ሳሉ በመንፈስ ቅዱስ ተአምራትን በማድረግ ለብዙዎች መዳን ምክንያት ሆኑ። እሌኒ ወደባሏ ከተመለሰች በኋላ አባታችን አቡነ ተ/ሐዋርያትን ወለደች። አባታችን ለወላጆቻቸው እየታዘዙና መዝሙረ ዳዊትን፣ መጻሕፍተ ነብያትንና ሐዋርያትን እንዲሁም የቤተ ክርስቲያንን ታሪክ እየተማሩ አደጉ። ገና ለአቅመ አዳም ሳይደርሱም ከመንግስት ወገን የምትሆን ልጅ ታጨችላቸው። ይሁን እንጂ ልጅቱ በዕድሜ ከእርሳቸው የምትበልጥ መሆኗንና እሳቸው ደግሞ በጣም ትንሽ በመሆናቸው አባቷ ለእንድርያስ ብዙ

©ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org

ገንዘብ ሰጥቶ ወደ ቤቱ ወሰዳቸው። ከዚህም በኋላ ዲቁና ተሹመው ሲያገለግሉ የመጻሕፍት አዋቂ በመሆናቸው በካህናትና በምዕመናን ዘንድ ተወዳጅነት አገኙ። ፈረስ መጋለብን፣ ቀስት መንደፍን፣ አውሬ ማደንንም ጨምረው ተግሩ። ለአቅመ አዳም በደረሱ ጊዜም ካላገባህ የሚለው ግሬት ብዛባቸው። አባታችን ግን «ዘመኑ አጭር ሆኗል ከእንግዲህ ወዲህ ሚስቶች ያሉአቸው እንደሌላ ቸው ይሁኑ የሚያለቅሱም እንደማ ያለቅሱ ደስ የሚላቸውም ደስ እንደ ማይላቸው ይሁኑ። የዚህች ዓለም መልክ ኃላፊ ነውና። ነገር ግን ያለ ሐሳብ ልትኖሩ እወዳለሁ። ያላገባው ጌታን እንዴት ደስ እንደሚያሰኝ የጌታን ነገር ያስባል። ያገባው ግን ሚስቱን እንዴት ደስ እንደሚያሰኛት የዓለምን ነገር ያስባል። ልቡም ተከፍሎአል» የሚለውን የቅዱስ ጳውሎስ ቃል እንዲሁም «ከኔ ይልቅ አባቱን ወይም እናቱን ወንድሙን እህቱን ሚስቱን ልጁን ቤቱን ወይም እርሻውን የሚወድ ለኔ ሊሆን አይገባም። ማንም መስቀሉን ተሸክሞ በኋላዬ የማይመጣ ደቀ መዝሙሬ ሊሆን አይችልም» ያለውን የአምላክ ትምህርት በማሰብ አንዳችም ስንቅ ሳይዙ የሥላሴ ብርሃን እየበራላቸው ከአባታቸው ቤት በሌሊት ጠፍተው ደብረ ሊባኖስ ከአቡነ ተክለሃይማኖት ገዳም ገብተው የምንኩስናን ልብስ ለበሱ— መነኮሱ። ሥጋቸውን በጾም፣ በጸሎት፣ በስግደት ሌትና ቀን ማድ ከምና በኋላም አርባ ቀን ከምግብና ከውሃ እየተከለከሉ መጾምን፣ በባሕር ውስጥ ቆሞ መጸለይን ጀመሩ። በመጨረሻም ከዱር ከሚገኝ ፍሬና ቅጠል በውሃ ከተራሰ አተር በስተቀር መመገብ አቆሙ። ከዚህ ሁሉ ትሩፋት ጋር በየዱሩና በየዋሻው ያሉትን ስውራን (ቅዱሳን) ይጐበኙ ነበር። አቡነ ተክለሐዋርያት ቅዱሳንን ለመጐብኘት ከደብረ ሊባኖስ ወጥ ተው በደብረጽሙና መቃብር ከአቡነ አትናቴዎስ በረከትን ከተቀበሉ በኋላ በዚያው በደብረ ጽሙና አንድ ታላቅ ዋሻ አግኝተው በጾም በጸሎት መኖር ጀመሩ። በመሪር ለቅሶና በብዙ ስግደት ለሥጋቸው ምኞት ለነፍሳ ቸው እረፍትን ከልከለው ብዙ ጊዜ ከኖሩ በኋላ ከስግደት ብዛት የተነሣ ሁለት የእጃቸው ጣቶች ተሰበሩ። ከመቆማቸውም የተነሳ እግሮቻቸው አበጡ። ይህም ሁሉ አልበቃ ብሏቸው በወገባቸው ላይ ስምንት ስለት ያላቸው ነገሮችን ሰውነታቸውን እንዲቆራርጣቸው አደረጉ። እነዚህን ስለት ያላቸው ነገሮች ከጌታችን ልደትና ከፋሲካ ቀን በስተቀር አያወ ልቋቸውም ነበር። ሕማሙም ሲጸ ናባቸው ሰውነታቸውን ‹አንቺ ኃጢአተኛና ዘማዊት ሰውነት ለእኔ ሲል አምላክ በአይሁድ እንደተሰቀለ አታውቂምን?› እያሉ ያነቡ ነበር። በዚህ ሁኔታም እያሉ ጌታችን ከቅዱሳን መላእክቱ ጋር መጥቶ ስለተጋድሏቸው በቦታው የጸመው የጸለየውንና የሰገደውን አስራት አድርጐ ሰጣቸው።

አባታችን አቡነ ተክለሐዋርያት በደብረጽሙናም ሆነ በሌላ ቦታ ብዙ ተጋድሎና ተአምራትን ከማድረ ጋቸው ባሻገር ጌታችን የተቀበለውን መከራ ሁሉ ለመቀበል እንዲያበቃ ቸው አጥብቀው ይለምኑት ነበር። ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስም ልመና ቸውን ሰምቶ በንጉሡ በአጼ ዘርአ ያዕቆብ እጅ መከራን እንዲቀበሉ አደረጋቸው። በዚህ በመከራም ወቅት እመቤታችን ድንግል ማርያም ቅዱስ ጊዮርጊስን ይዛ በመምጣት ‹እንደ ወዳጄ እንደ ጊዮርጊስ ጽና› ትላቸው ነበር። አባታችንም ‹ፈጣሪዬን የለመንኩት በአሕዛብ እጅ መከራ እንድቀበል እንጂ ከክርስቲያን ንጉሥ እጅ አልነበረም› ይሏታል። በመጨ ረሻም «የሰበከውን መከራ አግኝተ ሃል። ዘርአያዕቆብን ግን አትጥላው› ብላ አጽናናቻቸው። የእረፍታቸውም ጊዜ ሲደርስ በተመስጦ 3 ሳምንት የአምላክን ምስጢር ሲመለከቱ ሰነበቱ። በመጨረሻዎቹ ዕለታትም ‹ስምህን የጠራ በጸሎትህ የተማፀነ ሁሉ ክፍሉ በኢየሩሳሌም ሰማያዊት ከአንተ ጋር ይሆናል› በማለት ጌታችን ቃል ኪዳን ሰጣቸው። ጻድቁ አባት ግን ‹ይህን ሁሉ ቃል ኪዳን የሰጠኸኝ አንተን የሚያስደስት ምን ሥራ አለኝና ነው?› በማለት ጠየቁ። ጌታ ችንም «ክፍልህ ከወዳጄ ከሰማዕቱ ከጊዮርጊስ፣ ከዮሐንስ መጥምቅ ጋር ነው» አላቸው። እርሳቸውም ‹ጊዮር ጊስ ሰባት ዓመት ስለስምህ መከራን ተቀብሏል እኔ ኃጢአተኛ ስሆን እንዴት ከጊዮርጊስ አስተካከልከኝ ይህስ አይገባኝም› አሉት። ጌታም ‹ጊዮርጊስን ስሜ በእሱ ላይ እንዲ መሰገን ያፀናሁት እኔ ነኝ። አንተንም ያፀናሁህ እኔ ነኝ› ባላቸው ጊዜ ‹እንዳልክ ይደረግልኝ› አሉ። በዚህ ጊዜ ስለ ንጽሕናቸው፣ ስለ ድንግል ናቸው፣ ቅዱሳንን ስለመጐብኘታ ቸው፣ ስለትህትናቸው፣ ስለ የዋ ህነታቸው፣ ዓለምን ስለመናቃቸውና ተጋድሏቸውን በትዕግስት ስለመፈጸ ማቸው ሰባት አክሊል ወረደላቸው። በመጨረሻም ጌታችን ከእመቤታች ንና ከቅዱሳን ከሐዋርያት ጋር ሆኖ በመንፈቀ ሌሊት ወደ እርሳቸው መጣ። አባታችንም ተደሰቱ። ያቺንም ቀን የተመረጠች በግለት ደስታቸው እጥፍ ሆኖ በጎዳር 27 ቀን ከዚህ ዓለም መከራ አረፉ። ነፍሳቸውን የብርሃን መላእክት በዝማሬና በዕል ልታ ይዘዋት ወደ ሰማይ ዐረጉ። በዚህችም ሌሊት በሥጋቸው ላይ

©ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org

ታላቅ ብርሃን በራ በዚህም የተነሳ በእሥር ቤት የነበሩትና መኳንንት ሁሉ አባታችን ጻድቅ እንደነበሩ መሰከሩ። ካህናትም ሥጋቸውን ገንዘው በደብረ ብርሃን የቸር በምትባል ቦታ በአባ በርሱማ ደብር ቀበሯቸው። ንጉሥ ዘርዐ ያዕቆብም የሆነውን በሰማ ጊዜ ወደ ፈጣሪው አለቀሰ። በመቃብራቸውም ምኅረት ለመነ። ሥጋቸውንም ወደ ተጋደሉበት ወደ ደብረጽሙና እንዲያፈልሱ ለልጁ ለበእደ ማርያም ተናዘ ሞተ። በእደ ማርያምም ደቀ መዛሙርቶቻቸውን አስጠርቶ ሥጋቸውን ለማፍለስ ሲሔድ የሀገሩ ሰዎች ጌጣችንን መድኃኒታችንን አንሰጥም ብለው አመጹ። የንጉሥ ትዕዛዝ ነውና በመጨረሻ ተስማምተው ሥጋቸው በተቀበረ በ13 ዓመቱ ፈልሶ በደብረጽሙና በቀደምት ስሟ ገብርማ በማኅሌት በዝማሬ ተቀበረ። በመቃብራቸውም ላይ ታላቅ ቤተክርስቲያን ተሠርቶ ብዙ ተአምራት ሲደረግ ኖሯል– አሁንም እየተደረገ ነው።

ይህ ቤተ ክርስቲያን በግራኝ ዘመን ተቃጥሎና ቅርሶቹ ተዘርፈው ነበር። በኋላ ግን ንግስት ዘውዲቱ ፋሌ መድኅኔዓለም ሳሉ ይህን ቦታ በማየ ታቸውና በአንድ ባህታዊ አሳሳቢነት ወደዙፋናቸው ከተመለሱ በኋላ ገዳሙን እንደገና መሠረቱ። መጻሕፍትንና ንዋየ ቅድሳቱንም አሟልተው ገዳሙ በአንድነት ማኅበር እንዲሠራ አደረጉ። እስከዛሬም ድረስ ገዳሙ ደብረጽሙና አንድነት ገዳም በመባል ይጠራል። የጻድቁ የአቡነ ተክለ ሐዋርያት አማላጅነት ረድኤታቸውና በረከት አይለየን። አሜን።

ምስጋና:- የገዳሙንና የአባታችንን ታሪክ ጽፈው የላኩልንን የገዳሙን መጋቢ መጋቢ ክንፈ ገብርኤል ተ/ማርያምን በእግዚአብሔር ስም እናመሰግናለን።

ወስብሐት ለእግዚአብሔር

ይህን ያውቁ ኖሯል?

አቡነ ተክለሐዋርያት የጻድቁን ጳጳስ የአቡነ አትናቴዎስን መቃብር ለማየት በሔዱ ጊዜ ቆመው ሲጸልዩ ከእግራቸው በታች በፅዋ ውኃ ሲፈስ አገኙ። ውኃውን ወስደው ቦታውን ላሳዩዋት ለእግዚአ ክብራ ሰጧት። እርሷም መካን ለነበረችው ገረዷ ሰጠቻት። ገረዷም በጻድቁ በአቡነ ተክለሐዋርያት ጸሎት የፈለቀውን ውኃ ጠጥታ ወለደች። የፈለቀው ውኃ እስከዛሬ ድረስ ሲፈስና ሕመማንን ሲፈውስ ይገኛል።

✣ ✣ ✣

አንድ በከባድ በሽታ ይሰቃይ የነበረ ሰው ነፍሴ ከሥጋዬ ሳትለይ ፈጥ ናችሁ ወደ ቤተ ክርስቲያን ውሰዱኝና የጌታችንን ሥጋና ደም ልቀበል ብሎ ቤተሰቦቹን ለመነ። ቤተሰቦቹም ወደ ቤተ ክርስቲያን ወስደውት ሥጋወ ደሙን በተቀበለ ጊዜ ከሆዱ ውስጥ ዥንጉርጉር ደምና ሐሞት ከመግል ጋር ወጣ። በዚህ ጊዜ ካህናቱ ስለሥጋ ወደሙ ክብር ብለው በእቃ ተቀበ ሉት። ሽታው ግን ቤተ ክርስቲያኑን አናወጸው። አባታችን ተክለሐዋርያት ግን ጌታችን ስለእኛ በዕለተ አርብ ሀሞትና ከርቤን እንደጠጣ በማስታወስ ከሰውየው ሆድ የወጣውን ደም የተቀላቀለበት መግልና ሐሞት ስለ ሥጋ ወደሙ ክብር በቤተክርስቲያኑ በተሰበሰቡት ሰዎች ፊት አንስተው ጠጡት። ይህ የሆነበት ዕለት አሁድ ነበርና በቤተ ክርስቲያን ዋሉ። ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስም ወዳሉበት መጥቶ በሰው ሁሉ ፊት እንዳከበርከኝ እኔም በምድራውያንና በሰማውያን ሁሉ ፊት አከብርሃለሁ አላቸው።

ማዕረገ መነኮሳት

መነኮሳት ከብዙ መንፈሳዊ ተጋድሎ በኋላ ከእግዚአብሔር በጸጋ የሚያገኙት ማዕረግ፤

1ኛ. ጽማዌ – ያለ ምግብ የመኖር (ምግብን የመተው) ማዕረግ፤

2ኛ. ልባዌ – ምስጢራትን የማወቅ ማዕረግ፤

3ኛ. አንብዕ – የክርስቶስን መከራ እያሰቡ በልቡና ከሚቀጣጠል ፍቅር መንፈሳዊ የተነሳ የሚልቀስ ማዕረግ።

4ኛ. ጣዕመ ዝማሬ – እንደ መላእክት የማመስገን ማዕረግ፤

5ኛ. ኩነኔ – ሥጋን ለነፍስ የማስገዛት ማዕረግ፤

6ኛ. ፍቅር – ኃጥዕ ጻድቅ ሳይሉ ሰውን ሁሉ የመውደድና ስለ እነርሱም የመጸለይ ማዕረግ፤

7ኛ. ሑሰት – እንደ እግረ ፀሐይ (?) ካሰቡት ሁሉ የመገኘት ማዕረግ፤

8ኛ. ንጻሬ መላእክት – መላእክትን የማየት ማዕረግ፤

9ኛ. ተሠጥሞ – በብርሃን ተመስጠ ራእያትን የማየት ማዕረግ፤

10ኛ. ከሢነ እሳት – የመሰወርና ሥላሴን በመለኮታዊ ባሕርይ ሳይሆን በአምሳል የማየት ማዕረግ፤

- ከተራ ቁጥር 1–3 ያሉት – ሦስቱ ማዕረጋት የንጽሐ ሥጋ ማዕረጋት፤
- ከተራ ቁጥር 4–7 ያሉት – አራቱ ማዕረጋት የንጽሐ ነፍስ ማዕረጋት፤
- ከተራ ቁጥር 8–10 ያሉት – ሦስቱ ማዕረጋት ዳግም የንጽሐ ልቡና ማዕረጋት ይባላሉ።

ምንጭ – አረጋዊ መንፈሳዊ፤ (ገጽ 321–331)

ዲ/ኪዳኔ ከአማኑኤል ካቴድራል

አዲስ አበባ

©ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org

አባ ኢየሱስ ሞዓ

የመጀመርያው የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ዩኒቨርሲቲ መሥራች

ከመርሻ አለኸኝ – አ.አ.ዩ

በጐንደር ክፍለ ሀገር ስማዳ ወረዳ ዳህና በተባለው ቦታ በ1210 ዓ.ም ከአባታቸው ከዘክርስቶስና ከእና ታቸው ከእግዚእ ክብራ ተወለዱ። ዕድሜያቸው 30 ዓመት እስከሚ ደርስ ከቤተሰቦቻቸው ትምህርተ ሃይማኖትንና ግብረገብን ሲማሩ ከቆዩ በኋላ በ1240 ዓ.ም ይኼንን ዓለም በመተው ወደ ደብረ ዳሞ ገዳም ገቡ። በደብረ ዳሞ ገዳም መነኰሳቱን እየረዱ፣ ትምህርተ ቤተ ክርስቲያንን እያጠኑ፣ ቅዱሳት መጻሕፍትን እየገለ በጡ ለሰባት ዓመታት ከቆዩ በኋላ የደብረ ዳሞ 3ኛ አበ ምኔት ከሆኑት አላቸው። አባታችን ‹ቦታውን እን ዴት ዐውቀዋለሁ?› በማለት ቢጠይ ቁት ‹ተነሥ! ጉዞህን ጀምር ቦታውን እኔ አሳይሃለሁ» አላቸው። አባ ኢየሱስ ሞዓ በመልአኩ እንደታዘዙት ከበአታቸው ተነሥተው ተከተሉት። የብዙ ወራት መንገድ የሆነው ጕዳናም በስድስት ሰዓት አለቀላቸው።

በዚያን ወቅት ከሐይቅ ገዳም በስተ ሰሜን ወደነበረው ጴጥሮስ ወጳውሎስ ቤተ ክርስቲያን ደረሱ። ወደ ሐይቅ እስጢፋኖስ ገዳም ከመግባታቸውም በፊት ለ6 ወራት

ከአባ ዮሐኒ ምንኩስናን ተቀበሉ (1247 ዓ.ም)።

አንድ ቀን ሌሊት መልአኩ ቅዱስ ገብርኤል ወደርሳቸው መጥቶ ‹ገድ ልህና ትሩፋትህ በዓለም ሕዝብ ሁሉ ታውቆአል። አሁንም ይኼን ገዳም ትተህ የስምህ መክበርያ ወደሆነው ሐይቅ ወደ ተባለው ሥፍራ ሂድ› ያህል በጴጥሮስ ወጳውሎስ ቤተ ክርስቲያን አገልግለዋል። ያገለግ ሉበት በነበረው ቤተ ክርስቲያን ቀን ቀን ሕዝቡን ሲያስተምሩ በመዋል ሲመሽ ወደ ሐይቁ በመግባት ሲጸልዩ ያድሩ ነበር። በሐይቅ እስጢፋኖስና በዙርያው ለነበሩ አበውም ማታ ማታ አንድ ብርሃን ወደ ሐይቁ ሲገባ ጠዋት ጠዋትም ሲወጣ ይታያቸው እንደነበር ዛሬ በገዳማቸው የሚገኘው ገድለ ኢየሱስ ሞዓ ያስረዳል።

በመጨረሻም በገዳሙ አባቶች ልመናና በልዑል እግዚአብሔር ትዕ ዛዝ ወደሐይቅ ገዳም ገብተው አበምኔት ሆኑ። አባ ኢየሱስ ሞዓ በሐይቅ እስጢፋኖስ በአበምኔትነት በቆዩባቸው 45 ዓመታት ከየገዳማቱ ቅዱሳት መጻሕፍትን በመገልበጥና በማስገልበጥ ብሎም በማሰባሰብ የመጀመርያው ዘመናዊ የቤተ ክርስ ቲያን ቤተ መጻሕፍት በሐይቅ እስጢ ፋኖስ ገዳም እንዲቋቋም አድርገዋል። በዚሁ ገዳም ውስጥም የመጀ መርያውን የቤተ ክርስቲያን ቋሚ ት/ቤት በማቋቋም 800 መነኰሳትን በትምህርተ ሃይማኖት አሠልጥነው በንቡረ ዕድነት ማዕረግ በመላ ሀገሪቱ እንዲሠማሩ አድርገዋቸዋል። ከተማ ሪዎቻቸውም መካከል አቡነ ተክለ ሃይማኖት (ዘደብረ ሊባኖስ)፣ አባ ኀሩተ አምላክ (ዘጣና ሐይቅ)፣ አባ ጊዮርጊስ (ዘጋሥጫ)፣ አባ ዘኢ የሱስ፣ አባ በጸሎተ ሚካኤል፣ አባ አሮን (ዘደብረ ዳሬት) ጥቂቶች ናቸው። አኗ ይኩኖ አምላክንም በት ምህርተ ሃይማኖት ያነፁት እርሳቸው ናቸው።

በዮዲት ጉዲት ተጐድታ የነበ ረችው ሀገራችን ዳግም የወንጌሉ ብርሃን እንዲበራባት ሊቃውንት እንዳይነጥፉባት፣ ቅዱሳት መጻሕፍት እንዳይቆነጻጸሉ፣ መነኮሳት አባቶች ወደደቡብ ወርደው ገዳማትን እንዲያስፋፉ ያደረጉት አባ ኢየሱስ ሞዓ ናቸው። በተለይም የሐይቅ እስጢፋኖስ ‹ዩኒቨርሲቲ› ያፈራቸው 800 ሊቃውንት በመላዋ ሀገሪቱ በመሠማራታቸው ዛሬ የምናያቸውን አብዛኞቹን ገዳማትና ቅዱሳት መጻሕፍት አቆይተውናል።

አባታችን አባ ኢየሱስ ሞዓ ለ45 ዓመታት ሐይቅ እስጢፋኖስ ገዳም ከቆዩ በኋላ ኅዳር 26/1292 ዓ.ም በዕለተ እሑድ ዐረፉ። በዚያች ዕለትም በቦታው የታየው ብርሃን ሀገ ሪቱን ሞልቷት እንደነበረ ገድላቸው ይመሠክራል።

ምልጃና በረከታቸው በሁላችን ላይ ይደር። አሜን

ምንጭ

1. ገድለ ኢየሱስ ሞዓ
2. The Dictionary of Ethiopian Biography v.1, 1975

©ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org

ዓምደ ወራዙት

ንስሐ ለመግባት ምን እናድርግ?

ቃለ እግዚአብሔር በሚነገርበት ቦታ ሁሉ ምእመናን ንስሐ ይገቡ ዘንድ ይነገራል። ቅዱሳት መጻሕፍትም የንስሐን መሥጠር ለክርስቲያናች ሳይገልጡ የቀሩበት ምዕራፍ የለም። ምክንያቱም የእግዚአብሔር ፈቃድ ሁሉ ወደ ድኅነት ይመጡ ዘንድ ነውና። ይሁን እንጂ ሰዎች ሕይወተ እንጂ ሞተ፣ ፍቀር እንጂ ምቀኝነት፣ ራስን መግዛት እንጂ ስካር፣ ምሥጋና እንጂ ዘፈን፣ ቸርነ ትና በጎነት እንጂ ቁጣና አድመኛነት የማይስማማው ቅዱስ ሰውነት ለኃጢ አት አሳልፎ አይሰጥም። ምክንያቱም ሥጋው የክርስቶስ አካል ነውና። 1ቆሮ.6፥15።

ለ. የመንፈስ ቅዱስ ማደሪያ ነው 1ኛቆሮ.6፥19–20።

ንስሐ ለምንና እንዴት?

(ከተሾመ አይቼው)

ንስሐ ለመግባት ቢፈልጉም በተግባር አይፈፅሙትም። ለምንድር ነው? የቀደሙት አበው እግዚአብሔርን በበደሉ ጊዜ ዓይናቸው የእንባጉርፍ እያመነጨላቸው ከአምላካቸው ጋር ታርቀዋል። እኛ ግን ዕለት ተዕለት እየበደልን ንስሐ እንዳንገባ ልቦናችንን ያደነደነውን ድካማችንን እንድናስ ወግድ ምን ማድረግ አለብን? ቀጥሎ እንመለከተዋለን።

1. ራስን ማወቅ።

አንድ ሰው ወደዚህ ምድር እን ዴትና ለምን እንደመጣ፣ እስከመቼስ እንደሚቆይ፣ ከዚያ በኋላስ ያለው ሕይወት ምን እንደሚመስል ከተገነ ዘበ ንስሐ ለመግባት ጊዜ አይወስ ድበትም። እርሱ በኃጢአት ያሳደ ፈው ያ ሰውነት፣

ሀ. በእግዚአብሔር አርአያና አምሳል የተፈጠረ ነው ዘፍ.1፥26

ይህንን በእግዚአብሔር አርአያና አምሳል የተፈጠረ፣ እውነት እንጂ ውሸት፣ ብርሃን እንጂ ጨለማ፣ ያለው ከቡር ከርስቲያን ራሱን ከኃጢአት የሚጠብቅ ንቁ ባለሟል ነው። ምድራዊና ጊዜያዊ በሆነ ደስታ የሚያልፈውንና ዘመን የማይሽረውን ደስታ ለማጣት አይፈልግም። በኃጢ አት ያሉ ሰዎችም ይህንን ዘወትር ቢያስቡ ንስሐ ለመግባት ጊዜ አይፈ ጅባቸውም። ልቅሶና ጥርስ ማፋጨት ወዳለበት ቦታ ለመጣልም ራሳቸውን አያዘጋጁም።

ስለዚህ የማታልፈውን መንግ ሥት በሚያልፈው፣ ዘለዓለማዊውን በጊዜያዊው፣ ሰማያዊውን በምድራ ዊው እንለውጥ። ዓይን ያላየችው ጆሮ ያልሰማው በሰውም ልብ ያልታሰበው እግዚአብሔር ለሚወዱት ያዘጋ ጀው...መንግሥት ወራሾች እንሆን ዘንድ። 1ቆሮ.2፥9።

2. ኃጢአት ምን እንደሆነ ማወቅ።

የኃጢአትን ምንነት የሚያውቅ ሰው ኃጢአትን ከመፈፀም ራሱን ይቆጥባል። ንስሐ ለመግባትም መጀ መሪያ ኃጢአትን መጥላት ስለሚገባ ያንን ለማድረግ ደግሞ የኃጢአትን ምንነት መገንዘብ ይገባል።

ሀ. ኃጢአት ዓመፅ ነው።

ትዕዛዘ እግዚአብሔርን ጥሶ የሥጋውን ፈቃድ የሚፈፅም ሰው ሐዋርያው እንደተናገረው ዓመፀኛ ነው። ዓመፁም በምድራውያን ሰዎች ላይ ሳይሆን በእግዚአብሔር ላይ የሚፈፀም ነው። እርሱ ያዘዘውን ቃል ጥሶ ተቃራኒውን መፈፀም ትዕዛዝ የሰጠውን የሰማይ የምድር ንጉሥ መናቅ፣ በእርሱም ላይ ማመፅ ነውና። በኃጢአት የሚመላለስ ሰው የሚበድ ለው እግዚአብሔርን ነው። ስለዚህም ነው ልበ አምላክ ዳዊት «አንተን ብቻ በደልሁ...» (መዝ.50፥4) ያለው።

©ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org

ይህ ግለት በሥልጣኑ ተጠቅሞ የወሰዳት ቢርሳቤህ፣ በጦርሜዳ ደሙ የፈሰሰው ኦርዮን ያልተጐዱ ሆነው ሳይሆን ኃጢአት በእግዚአብሔር ላይ ግመፅ መሆኑን ስለሚያውቅ እንጂ። 2ጢሞ.2፥19።

ለ. ኃጢአት ሞት ነው።

አንዳንድ ሰዎች ለምን ንስሐ ለመግባት እንደማይፈልጉ ሲጠየቁ ‹ተውኝ ሕይወቴን ልኑርበት› በማለት ኃጢአትን ሕይወት፣ ክርስትናን ደግሞ ሞት አድርገው ይመለከቱ ታል። ያልተረዱት ትልቁ ነጥብ ግን ኃጢአት ሞት፣ ክርስትና ሕይወት መሆናቸውን ነው። ዛሬ ሕያዋን የሚመስሉ ነገር ግን ከእግዚአብሔር በመለየታቸው የሞቱ አያሌ ናቸው። ምክንያቱም «የኃጢአት ደሞዝ ሞት ነው» ሮሜ.6፥23። «ኃጢአት ካደነች በኋላ ሞትን ትወልዳለችና።» ያዕ.1፥15። ይህንንም ቅዱስ ጳውሎስ ለመንፈስ ቅዱስ ልጁ ለጢሞቴዎስ በላከለት መልዕክቱ «...ቅምጥሊቱ ግን በሕይወትዋ ሳለች የሞተች ናት» (ጢሞ.5፥6) በማለት በሕይወት እያሉ መሞትም እንዳለ አስረድቶታል።

ክርስቲያን ከሞት ሕይወትን የመረጠ ነውና በኃጢአት በወደቀ ጊዜ ንስሐ ለመግባት ራሱን በትሕትና ዝቅ አድርጎ ወደ መምህረ ንስሐው ይቀርባል።

ሐ. ኃጢአት ከእግዚአብሔር መለየት ነው።

ነቢዩ ዳዊት «ለእኔስ ወደ እግዚአብሔር መቅረብ ይሻለኛል» መዝ.72፥28 ብሎ እንደተናገረው የቅድስናን ሥራ መሥራት ወደ እግዚአብሔር መቅረብ ሲሆን ኃጢአ ተኛ መሆን ደግሞ ከእግዚአብሔር መለየት ነው። ጌታ «በእኔ ኑሩ እኔም በእናንተ» ያለው ኃጢአተኛውን ሳይሆን በርትዕት ሃይማኖት፣ በመልካም ምግባር የጸናውን ነው። የሐ.15፥4። እርሱ ብርሃን ስለሆነ የእርሱ የሆኑትም የብርሃን ልጆች እንጂ የጨለማው አበጋዝ የሰይጣን ፈቃድ ፈጻሚዎች አይደሉምና።

ከእግዚአብሔር መለየት ማለት ሕጉንና ትዕዛዙን አለመጠበቅ፣ በራስ መንገድና ፈቃድ መመራት፣ ከእግ ዚአብሔር ይልቅ የዓለምን ፍቅር መውደድ ነው። ምክንያቱም የእግ ዚአብሔር ቃል ‹ማንም ዓለምን ቢወድ የአባት ፍቅር በእርሱ ውስጥ የለም› ይላልና። 1ዮሐ.2፥15። በተጨማሪም በኃጢአት መመላለስ ማለት በ40ና በ80 ቀናችን የታተ ምንበትን ቅዱሱን የእግዚአብሔር መንፈስ ማሳዘን ነው። ለዚህም ነው ሐዋርያው «ለቤዛው ቀን የታተማ ችሁበትን የእግዚአብሔርን መንፈስ አታሳዝኑ» ኤፌ.4፥30 ያለው። ስለዚህ ኃጢአትን ሕይወት በማድረግ እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስን አንታወም። የሐዋ.7፥51።

በተጨማሪም ከእግዚአብሔር መለየት ማለት የሰውን ልጅ ዘወትር ከሚጠብቁ ቅዱሳን መላእክት፣ ይህንን ዓለም ድል ከነሡ ቅዱሳንም መለየት ማለት ነው። ለዚህም ነው ሳኦል እግዚአብሔርን አሳዝኖ ጥበቃው ሲለየው የአጋንንት ማደሪያ የሆነው። 1ሳሙ.16፥14። ምክንያ ቱም ‹የእግዚአብሔር መልአክ በሚፈሩት ሰዎች ዙሪያ ይሰፍራል ያድናቸውማልና።› መዝ.33፥7።

መ. ኃጢአት ሽንፈት ነው።

‹እኔ ምንኛ ጎስቋላ ሰው ነኝ! ለዚህ ሞት ከተሰጠ ሰውነት ማን ያድነኛል?› ሮሜ.7፥24።

አንዳንድ ሰዎች የሚሠሩት ሥራ ኃጢአት መሆኑን ቢያውቁም እንኳን በሀሳበ ግትርነት ላለመመለስ አሻ ፈረኝ፣ ካፈርኩ አይመልሰኝ ብለው በያዙት የሞት ጉዳና ላይ ሙጭጭ ይላሉ። ለምሳሌ ከሌላ ሰው ጋር ባይስማሙ በቂመኝነትና በተንኮል ተመልተው ተቃራኒያቸውን ስም አጠራሩን ለማጥፋት እንቅልፍ አጥ ተው ይባዝናሉ። ነገር ግን እነርሱ ተሸናፊዎች እንጂ አሸናፊዎች አይደ ሉም። ምክንያቱም ኃጢአት ሽንፈት ነውና። «ክፉን በመልካም አሸንፍ እንጂ በክፉ አታሸነፍ» ሮሜ. 12፥21። የሚለውን ቃል አልተ ገነዘቡትም። ቃየን በቅናት ተነሣስቶ ወንድሙ አቤልን ገደለው። ነገር ግን ለጊዜው ያሸነፈ ይመስለው እንጂ በቅናትና በአድመኛነት ተሸንፏል። ዘፍ.4፥13–14። ስለዚህም ዘመኑን በፍርሃትና በመቅበዝበዝ አሳለፈ።

ንጉሥ ሄሮድስም መጥምቁ ዮሐንስን ወደ ወኅኒ አስወረወረው። ያም አልበቃ ብሎት አንገቱን አሠየፈው። ነገር ግን ከዚያ በኋላ ሽንፈቱ የእርሱ ነበርና ከሞት የተነሣ እየመሰለው ይጨነቅ ነበረ። ስለዚህ በኃጢአት ላለመሸነፍ እና የሰይጣንም ባሪያዎች ላለመሆን ንስሐ እንግባ።

3. የኃጢአትን ውጤት ማወቅ።

ኃጢአት ወንጀል ነው። ወንጀለ ኛም በሕግ ይቀጣል። ኃጢአተኛም ወንጀለኛ ነውና ቅጣት ይጠብቀዋል።

የኃጢአት ውጤት ምድራዊና ሰማያዊ ቅጣት ነው። ስለዚህም ከእግ ዚአብሔር ይልቅ ሰይጣንን የመረጡ፣ ከቅዱሱ የእግዚአብሔር ትእዛዝ ይልቅ የሥጋቸውን ፈቃድ በመከተል የሰይጣንን ትዕዛዝ የፈፀሙ በሙሉ ይቀጣሉ። ማንኛውም ሰው ይህንን ቢገነዘብ ኖሮ ከኃጢአት ይልቅ ጽድቅን በመረጠ ነበር።

ሀ. ፍርሃትና ሰላም ማጣት።

የኃጢአት አንዱ ውጤት ፍርሃ ትና ሰላም ማጣት ነው። አዳምና ሔዋንም በበደሉ ጊዜ ከእግዚአብሔር ከአምላካቸው የተደበቁት ለዚሁ ነው። ዘፍ.3፥10።

በቅድስና የሚኖር፣ ሰውነቱን በኃጢአት ያላላደፈ ሰው ግን ከልበ አምላክ ዳዊት ጋር «ሠራዊትም ቢሰ ፍርብኝ ልቤ አይፈራም፣ ሰልፍም ቢነሣብኝ በዚህ እተማመናለሁ» (መዝ.26፥3)። እያለ ይዘምራል። ኃጢአተኛው ግን የእግዚአብሔርን ቃል ሽሯልና ዘወትር በፍርሃትና ሰላም በማጣት ተውጦ ይኖራል። አስ

©ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org

ቀድሞ «ለክፉዎች ሰላም የላቸውም ይላል እግዚአብሔር ተብሎ ተጽፏልና» ኢሳ.48፥22። በተጨማሪም «ክፉዎች ግን እንደሚንቀሳቀስ ባሕር ናቸው።» (ኢሳ.57፥20)። ተብሏል።

ይህ ሁሉ የእግዚአብሔር ቃል የሚያስጠነቅቀን ነገር ቢኖር የኃጢአት ውጤቱ የማይገፉት ዳገት፣ የማይቀዝፉት ባሕር፣ ርጠው የማይዘልቁት ሜዳ፣ የማይደርሱበት ሰማይ መሆኑን ነው።

በተጨማሪም ኃጢአተኛ ሰው ዘወትር ያለፈ ኃጢአቱን ስለሚያስታውስ «ለምን ፈፀምኩት» የሚል የጎሊና ወቀሳ እንደጥላ ቀን ከሌሊት ይከተለዋል።

ለ. ከእግዚአብሔር ልጅነት መለየት

በጥምቀት ውሉድ ዘበጸጋ ተብለን የምንናገር ክርስቲያናች በበደል መመላለስ ስንጀምር ከእግዚአብሔር ልጅነት ራሳችንን እናገልላለን። «በእርሱ የሚኖር ሁሉ ኃጢአትን አያደርግም ኃጢአትን የሚያደርግ ሁሉ እንዲያውም አላወቀውም» ተብሏልና። እንዲሁም «የእግዚአብሔር ልጆችና የዲያብሎስ ልጆች በዚህ የተገለጡ ናቸው ጽድቅን የሚያደርግና ወንድሙን የማይወድ ሁሉ ከእግዚአብሔር አይደለም።» 1ዮሐ. 3፥6ና10።

ስለዚህ የኃጢአት ውጤቱ በ40ና በ80 ቀን ያገኙትን ልጅነት መጣል ነውና ከኃጢአት እንሽሽ።

በአጠቃላይ ንስሐ ለመግባት ከዚህ በላይ የተጠቀሱትን ነጥቦች ማጤኑ መልካም ነው። ነገር ግን ሁሉ በዚህ ተጠቃልሏል ባይባልም ፋናወጊ ሊሆኑ ግን ይችላሉ። እግዚአብሔር አምላካችን ኃጢአታችንን የምናስተውልበት ልቡና ይስጠን አሜን።

ንስሐችንን እንዴትና ለማን እንናዘዝ? ከንስሐ በኋላ ያለ ሕይወት ምን መምሰል አለበት? የንስሐ ፍሬ ምንድን ነው? ✥

ወለእግዚአብሔር ስብሐት

አፌን በምሳሌ እከፍታለሁ

መዝ.77፥2

«እናንተ የእፉኝት ልጆች» ማቴ.12፥34

እፉኝት (አርዌ ገሞራዊት) አፈ ግጎፅኑዋ ጠባብ ነው። የወንዱን ዘር የምትቀበለው በአፍዋ ነው። በዚህ ጊዜ ከስሜትዋ የተነሣ የወንዱን አባል ዘሩን ቆርጣ ታስቀረዋለች። በፅንስ ጊዜ አባት ይሞታል። ልጆችዎ በሚወለዱበትም ጊዜ አፈ ግጎፅኑዋ ጠባብ ነውና ሥጋዋን በልተው ሆድዋን ቀደው ይወጣሉ። በዚህ ጊዜ እናት ትሞታለች። አይሁድም እንደ አባት የሚሆኑዋቸውን ነቢያትን እንደ እናት የሚሆኑዋቸው ሐዋርያትን ገድለዋልና በእፉኝት ተመስለዋል።

«ኢየሩሳሌም ኢየሩሳሌም ሆይ ነቢያትን የምትገድል ወደ እርስዋ የተላኩትንም የምትወግር፤» እንዳለ ጌታ። ማቴ.23፥37።

• • •

«መንግሥተ ሰማያት ሰው ወስዶ በእር ሻው የዘራትን የሰናፍጭ ቅንጣት ትመስላ ለች» ማቴ.13፥31ና32።

መንግሥተ ሰማያት ሕገ ወንጌል፣ ሕገ ወንጌል—ተስፋ፣ ተስፋ—ኢየሱስ ክርስቶስ በእርሻው የሰናፍጭ ቅንጣት የሚዘራ ገበሬን ትመስላለች። እርሻ የዚህ ዓለም ምሳሌ ነው።

ሰናፍጭ ፍጽምት ናት፣ ነቅዕ የለባትም—ወንጌልም ነቅዐ ኑፋቄ የለባትምና። ሰናፍጭ ላይዋ ቀይ ውስጢ ነጭ ነው። ወንጌልም በላይ ደግችሁን አፍስሱ፣ ደግችሁን እስክ ግፍሰስ ተጋደሉ ትላለች በውስጥዋ ግን የዘላለም ሕይወት የሚገኝበት ተስፋ ይዛለች። ሰናፍጭ ቁስለ ሥጋን ታደርቃለች። ወንጌልም ቁስለ ነፍስን ታደርቃለችና። ሰናፍጭ ከምት ደቆስበት ተሐዋስያን አይቀርቡም። ወንጌልም ከምትነገርበት አጋንንት መናፍቃን አይቀርቡም። ሰናፍጭ አንድ ጊዜ የዘሯት እንደሆነ ባመት ባመት ዝሩኝ አትልም ተያይዛ ስትበቅል ትኖራለች። ወንጌልም በመቶ ፯ያ ቤተሰብ ተጀምራ እስከ ምጽአት ድረስ ስትነገር ትኖራለችና።

• • •

«ቀኝ ዓይንህም ብታሰናክልህ አውጥተህ ከአንተ ጣላት። ሙሉ ሰውነትህ በገሃነም ከሚጣል ይልቅ ከአካላትህ አንድ ቢጠፋ ይሻልሃልና። ቀኝ እጅህም ብታሰናክልህ ቆርጠህ ከአንተ ጣላት። ሙሉ ሰውነትህ በገሃነም ከሚጣል ይልቅ ከአካላትህ አንድ ቢጠፋ ይሻላልና።» ማቴ.5፥29እና30።

በዓይን የተመሰለች ሚስት ናት ከዓይን የሚሠወር እንደሌለ ሁሉ ከሚስትም የሚሠወር የለምና። ሚስትህ ያልሆነ ሥራ ላሠራህ፣ ሃይማኖትን ላስከድህ ብትልህ አትቀበላት። ፈታዲን አፍርስባት። ዛሬ በዚህ ዓለም የሚስትህን ፈቃድ ፈጽመህ ኑረህ ኋላ ገሃነም ከምትገባ በዚህ ዓለም የሚስትህን ፈቃድ አፍርሰህ ኑረህ ኋላ መንግሥተ ሰማያት ብትገባ ይሻልሃልና። እጅ የተባሉ ልጆች ናቸው ከነተረቱም «ወድቆ ይነሡ በእጅ ዘገይቶ ይከብሩ በልጅ»። ልጆችህ ለሃይማኖትህና ለምግባርህ መሰናክል ቢሆኑብህ ይመሩኖል ብለህ የልጆችን ፈቃድ ፈጽመህ ኑረህ ኋላ ገሃነም ከምትወርድ በዚህ ዓለም የልጆችህን መጥፎ ፈቃድ አፍርሰህ ኋላ መንግሥተ ሰማያት ብትገባ ይሻልሃል።

• • •

«ለርኁቦችና ለሚያጠቡ ወዮላቸው። ሸሽታችሁ በክረምት ወይም በሰንበት እንዳይ ሆን ጸልዩ» ማቴ.24፥19ና20።

እርኁቦች የሚለው ቃል ኃጢአትን በሐልዮ (በሃሳብ) በኀሊናቸው በልቦናቸው የጸነሱ ሰዎችን የሚመለከት ነው። የሚያጠቡ ሲል ደግሞ በልቡናቸው ለሌላ ላይ አስፍረውት የነበረውን የሃሳብ (ሐልዮ) ከገቢር የሚያደርሱና ኃጢአትን በነቢብ ወልደው ዕለት ዕለት በሕይወታቸው በገቢር እያሳደጉ ኃጢአትን ወደው ለምደው የያዙ ሰዎች ምሳሌ ነው።

ሸሽታችሁ በክረምት ወይም በሰንበት እንዳይሆን ግለቱ ክረምት ወርኃ ልምላሜ ነው። ቅጠል ብቻ እንጂ ፍሬ አይታይበትም እንደዚሁም ሁሉ ከኃጢአት ርቀን በሥጋ ወደሙ ታትመን እንኖራለን ብለው ሁል ጊዜ በሐሳብ (በተስፋ) የሚኖሩ ጻሩ ግን እውነትን ዐውቀው በእውነት መንገድ የማይጓዙ ፍሬ ሃይማኖት ፍሬ ምግባር የሌላቸው ተስፋ ብቻ ይዘው በእግዚአብሔር ቃል እየዘበቱ የሚኖሩ ሰዎች ታሉን በመስማት ጆሮአቸውን ብቻ የሚያሰቡ ሰዎች ምሳሌ ነው። ሰንበትም የእረፍት ጊዜ ነው። እናንተም ከምግባረ ነፍስ ተለይታችሁ ዛሬ መንፈሳዊ ሥራ የሚሠራበት ወቅት አይደለም ብላችሁ ተግባረ ሥጋችሁን ብቻ እያከናወናችሁ በተግባረ ነፍስ ግን ተዘልላችሁ ሳለ እንዳልመጣ ተግታችሁ ጸልዩ ማለቱ ነው።

ወስብሐት ለእግዚአብሔር

(ይቀጥላል)

©ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org

«የዘጠኙ ቅዱሳን ሥራ ዛሬም መደገም አለበት!»

ዲ/ን/መስቀል ሳሙኤልስ
(በፋና ጎርጎርዮስ)



ክርስትና ሰዎች ብቻቸውን የሚኖሩበት ሳይሆን ለአያሌ ዘመናት ብዙዎች የተመላለሱበት ዛሬም ያሉት የሚሄዱበት፣ የነገዎቹም የሚረግሙ ዱበት ጉዳና ነው። የአንዱም ሕይወት ለሌላው አርአያ በመሆኑ ለዚህ እትግችን አስተማሪ ነው ያልነውን ታሪክ አቅርበናል።

ቁመቱ ረዥም፣ ሰውነቱ ፈርጠም ያለ የ31 ዓመት ወጣት ነው። የሚያውቃቸውን አንዳንድ የአማርኛ ቃላት መጠቀም ከሰው ጋር ለመግባባት ትልቅ ጉጉት አለው። ኑሮው እና ዜግነቱ በምዕራብ አውሮፓ እንግሊዝ የሆነው ይህ ወጣት ዲያቆን ኃይለ መስቀል ሳሙኤልስ ይባላል። የትናትናው ቴክኒሺያንና አርቲስት የዛሬው በለንደን የምትገኘው የቅድስት ማርያም ቤተ ክርስቲያን ቀዳሽ ዲያቆን ኃይለ መስቀል እዚህ ደረጃ ከመድረሱ በፊት ያሳለፈው የሕይወት ውጣ ውረድ ብዙ ነው። እውነተኛውን የክርስቶስ ቤተ ክርስቲያን አግኝቶ ከመጠመቁ በፊት ይህ ነው የሚባል እምነት ተከታይ አልነበረም። በግሉ መጽሐፍ ቅዱስን የሚያነብ ብቻ ነበረ። በጥቁርነቱም ማንነቱን ለማወቅ የጥቁር ሕዝቦች ታሪክ ለ10 ዓመታት ይመረምር እንደነበረ አጫውቶኛል። ገንዘብ እንጂ መንፈሳዊ ሀብት በሌላቸው አውሮፓውያን መካከል መኖር አስቸጋሪ መሆኑን የገለጸው ዲያቆን ኃይለ መስቀል ሕይወቱ ስለተለወጠበት አጋጣሚ እንዲህ ይተርካል።

«ያቺን ቀን መቼም አልዘነጋትም። ሕይወቴ የተለወጠባት፣ ወደ እውነተኛው የክርስትና ትምህርት የመጣሁባት ናትና። ታሪኩ እንዲህ ነው። እንደተለመደው በቤተ መጽሐፍ ውስጥ ነበርኩ። የአይሁድን ምሳሌያዊ አነጋገሮች፣ የአፍሪካን ታሪክ እየመረመርኩ። በዚህ ጊዜ ነበረ ከቁስጥንጥንያ ተሰፋሚካኤል (የሸዋ ሊቀ ጳጳስ የነበሩት አቡነ ጎርጎርዮስ ከራስ ተፈሪያንነት ለውጠው ካስተማሯቸውና ለቅስናም ካበቋቸው ሰው) ጋር የተገናኘነው። በሀሳብ ተስማማን። ስለኦርቶዶክሳዊት ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ካስተማሩኝ በኋላ ለበለጠ ትምህርት ደግሞ ወደ ቤተ ክርስቲያን እመጣ ዘንድ አድራሻ ሰጡኝና ተለያየን። ከዚያ በኋላማ ማን ከቤቴ ሊያወጣኝ። የቤተ ክርስቲያን ልጅ ሆንኩኝ። ስሜም ተቀየረና ኃይለ መስቀል ተባልኩኝ። ይህንንም ስም የሰጡኝ አስተማሪዬና መከራዬ የነበሩት ሊቀ ብርሃናት ሰሎሞን ነበሩ።»

‹አምላክ ፀሐይ ተናበበኒ› እያለ የሰማይና የምድር፣ የፀሐይና የጨረቃ የእሳትና የውኃ ፈጣሪን ይገለጽለት ዘንድ ለለመነ ለአበብዙኃን አብርሃም የተገለጠ አምላክ አእይንተ እግዚአብሔር በተባሉ ካህናት አማካኝነት ራሱን ገለጠለት። ከዚያ በኋላስ ምን ሆነ? እንከታተለው።

«ከዚያ በኋላማ ስለ እናት ቤተክርስቲያኔ የማወቅ ፍላጐቴ ተነሣሣ። ስለዚህም ሥራዬን ትቼ ብዙ ሺህ ኪሎ ሜትሮችን አቋርጬ ወደ ኢትዮጵያ መጣሁ። እዚህም ቅ/ጳውሎስ ከፍተኛ መንፈሳዊ ትምህርት ቤት ገብቼ ለአንድ ዓመት ያህል ተማርኩኝ።»

ብዙዎች ሁሉ ነገር ተመቻችቶላቸው እንኳን የመማር ፍላጎታቸው ሲሞት እርሱ ግን አገር ቆርጦ መጣ። የእናት ቤተ ክርስቲያኑን መሠረተ እምነትና ሥርዓት ለመማር። በአሁኑ ወቅትስ ለቤተ ክርስቲያኑ ምን ምን አገልግሎቶችን ያበረክታል?

«በመንፈሳዊው በኩል በዲቁናዬ የሚጠበቅብኝን አገልግሎት እሰጣለሁ፣ እቀድሳለሁ፣ እሰብካለሁ፣ በትምህርት ክፍል አባልነቴም ትምህርቶችን በመጻፍ በፓምፍሌት መልክ አሰራጫለሁ። በሌላ በኩልም ሰዐሊ ስለሆንኩ ለቤተ ክርስቲያኔ ሥዕል በመሳል፣ ጽሑፍ በመጻፍ ገንዘብ የሚገኝበትን መንገድ በመክፈት ላይ እገኛለሁ።»

ለመሆኑ የት የት ነው የሚሰብከው?

«መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ እንዳስተማረው በአልጋ ቁራኛ፣ በደዌ ዳኛ የተያዙ፣ በገቢያ ያሉ ነጋዴዎች፣ በከተማ የሚኖሩ ወዘተ. ሕገ ወንጌል ይሰብክላቸዋል። እናም በገበያ ቦታዎችና በእስር ቤቶች እንሰብካለን። ከዚያም ወደ ቤተ ክርስቲያን ይመጡ ዘንድ አድራሻችንን እንሰጣቸዋለን።»

የኦርቶዶክሳዊት ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያንን እምነት ለሌሎች ለማስተማር ያለመታከት ይደክማል። በዘመናዊው እውቀት መጥቆ ከመሰልጠን ወደመሰይጠን ባዘነበለበት ከፍለ አህጉር ነገረ ቤተ ክርስቲያንን ሲያስተምሩ የሚሰማቸው አለ ይሆን?

©ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org

ስለቤተክርስቲያናችንስ ሕዝቡ ምን ያህል ያውቃል?

«በምዕራቡ ዓለም ያለው ጥቁር ሕዝብ ስለ ቤተክርስቲያናችን ብዙም አያውቅም። ግንም የነገረው ሰው የለም። ነጮች ግን ጠንቅቀው ነው የሚያውቋት። የመጀመሪያው አፍሪካዊ የወንጌል መልእክተኛ የንግሥት ሕንደኬ የገንዘብ ሹም ኢትዮጵያዊ ጃንደረባ መሆኑን ያውቃሉ። ትልቁ የማስተዋወቅ ሥራ ያለብን ለጥቁሮቹ ነው።»

በአሁኑ ወቅት በአውሮፓ ውስጥ በዝርወት ያሉ ጥቁሮች ስለ ኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የማወቅ ታላቅ ፍላጎት እንዳላቸው የገለጸው ዲ/ኃይለ መስቀል ቤተ ክርስቲያኒቱ ከዚህ በላቀ ብዙ ነገር ማድረግ እንደሚጠበቅባትም አብራርቶልናል። ለመሆኑ በብዙ ሺዎች ስም የሚጠሩ የአውሮፓውያን የእምነት ድርጅቶች አገር ቆርጠው ወደ አፍሪካ ሲመጡ እንመለከታለን። ለሕዝባችንም ወንጌልን እንሰብካለን በሚል ሰበብ ከእናት ቤተ ክርስቲያኑ ሲለዩት ማየቱ የዕለት ተዕለት ገጠመኝ ሆኗል። በአገራቸውስ ያለው ሁኔታ ምን ይመስላል። ለዚህ ጥያቄ ዲያቆን ኃይለ መስቀል የሚከተለውን መልስ ሰጥቶናል።

«በአውሮፓ በአሁኑ ጊዜ መንፈሳዊ ሰው ሆኖ መገኘት ሞኝነት ሆኗል። ወደ ጸሎት ቤቶቻቸው የሚሄዱት ለጉብኝት ወይም ለጊዜ ማሳለፊያ ብቻ ነው። በሰንበት ዕለት እንኳን በጣት ከሚቆጠሩ ሰዎች በስተቀር በጸሎት ቤታቸው አካባቢ ማንንም አታገኝም። የዘመኑ መመሪያቸው «ሥራ» ብቻ ሆኗል። በዚህም ምክንያት የጸሎት ቤቶቻቸውን ለሆቴሎች፣ ቢሮዎችና የገበያ አዳራሾች በመለወጥ ላይ ይገኛሉ።»

‹ጅብ ከማያውቁት አገር ሄዶ ቁርበት አንጥፉልኝ አለ› እንደሚባለው የራሳቸውን ሕዝብ ሳያስተምሩ፣ በሃይማኖትና በምግባር ሳያንፁ ወደሌላው ሀገር በመሄድ ‹ወንጌል እናስተምር» ይላሉ። በዚህም ከኋላቸው ያለው እውነተኛ ዓላማ ምን እንደሆነ መረዳት ይቻላል። በሌላ በኩል ደግሞ በተለያየ ምክንያት ከሀገራቸውና ከእናት ቤተ ክርስቲያናቸው ተለይተው የሚሄዱ ምዕመናን የበዙበት ዘመን ነውና ለነዚህስ ምን ትመክሪዋለህ ብዬ ለጠየቅሁት ጥያቄ የሚከተለውን መልስ ሰጥቶኛል።

«በእርግጥ ግንም ቢሆን ከአገሩ የሚወጣው ወዶ አይደለም። በተለያዩ ምክንያቶች በተለይም ለመኖር በሚ ያደርገው ጥረት ራሱን ለማሸነፍ ገንዘብ ማግኘት ምድራዊውንም ዕውቀት መገብየት ስላለበት ነው። ነገር ግን አስቀድሚ እንደ ተናገርሁት በምዕራቡ ዓለም ያለው ሥጋዊ እንጂ መንፈሳዊ ሀብት አይደለም። እነርሱ ገንዘብ አላቸው እኛ ደግሞ እምነት አለን። እግዚአብሔር አለን። ስለዚህ ማንኛውም ወደውጪ የሚሄድ ኦርቶዶክሳዊ መጠንቀቅ ይገባዋል። ለምሳሌ ሥራ ለመሥራት ኮንትራት ስትዋዋል። አሐድንም ለመሥራት እንድትስማማ ያደርጉሃል። በሰንበት ቀን እንኳን ቤተ ክርስቲያን መሄድ ካልቻልክ መጨረሻህ ምን ሊሆን እንደሚችል መገመት ትችላለህ። ጌታችን እንዳስተማረው «ሰው ዓለሙን ቢያተርፍ ነፍሱን ግን ቢያጎድል ምን ይጠቅመዋል?» (ማር.8፥36) እኛም ገንዘብ ቢኖረን ነገር ግን እምነታችንን፣ መንፈሳዊነታችንን በሙሉ ብናጣ ምን ፋይዳ አለው? በአገራቸው ለመኖር ያልታደሉት ቢያንስ ቢያንስ በነጮቹ መካከል ሲኖሩ አምላካቸውን፣ ቤተ ክርስቲያናቸውንና አገራቸውን ላለመርሳት መሞከር አለባቸው። ተምሮ ወደ አገር ቤት መምጣቱ አማራጭ የለውም። አለበለዚያ በተስፋ መቁረጥ ብዙ መጥፎ ነገሮችን ወደ መሥራት መገፋፋቱ ይመጣል። ለዚህም ነው ብዙዎች ራሳቸውን በራሳቸው አያጠፉ ሬሳቸው ወደ ሀገራቸው ሲመጣ የምንመለከተው።»

ዲያቆን ኃይለ መስቀል ይህንን ሲናገር በኅሊናዬ የልበ አምላክ ዳዊት ቃል አቃጨለ። «ኢየሩሳሌም ሆይ ብረሳሽ ቀኜ ትርሳኝ (መዝ.136፥5) የሚለው። ቤተ ክርስቲያን ሆይ ብረሳሽ ቀኜ ትርሳኝ ማለት እንደ ሚገባን ያስተምረናል።

በዚያ ከፍለ ዓለም ስለ ቤተ ክርስቲያናችን መማር የሚፈልጉ ብዙዎች ካሉ ጥያቄያቸውን ለመመለስ ቤተ ክርስቲያን ምን ማድረግ አለባት ትላለህ የሚለውን ጥያቄ ሳቀር ብለትም የሚከተለውን መልሥልናል።

«በአሁኑ ወቅት ወጣቶችና ጎልማሶች ብቻ ሳይሆኑ ሕፃናቱም በብዛት ወደ ቤተ ክርስቲያን እየመጡ ነው። ነገር ግን ቤተ ክርስቲያን መሥራት ያለባት አንድ ትልቅ ሥራ አለ። የቋቱ ቅዱሳንን ሥራ። እነርሱ ምዕመኑ በተዋሕዶ ሃይማኖቱ፥ በሥርዓተ ቤተክርስቲያኑ እንዲጸና መጻሕፍትን (ከተለያዩ ቋንቋዎች) ወደ ግዕዝ ቋንቋ ተርጉመዋል። ቤተ ክርስቲያናችንም መጻሕፍትን ወደ እንግሊዝኛ ቋንቋ መተርጉም በውጭ ያለው ምዕመን ያነብ ዘንድ ማዘጋጀት አለባት። የጸሎት መጻሕፍት፣ የታሪክ መዛግብትና ሌሎችም መረጃዎች በመጠኑም ቢሆን መተርጉም ይኖርባቸዋል።»

«በአውሮፓ በአሁኑ ጊዜ መንፈሳዊ ሰው ሆኖ መገኘት ሞኝነት ሆኗል። ወደ ጸሎት ቤቶቻቸው የሚሄዱት ለጉብኝት ወይም ለጊዜ ማሳለፊያ ብቻ ነው። በሰንበት ዕለት እንኳን በጣት ከሚቆጠሩ ሰዎች በስተቀር በጸሎት ቤታቸው አካባቢ ማንንም አታገኝም። የዘመኑ መመሪያቸው «ሥራ» ብቻ ሆኗል። በዚህም ምክንያት የጸሎት ቤቶቻቸውን ለሆቴሎች፣ ቢሮዎችና የገበያ አዳራሾች በመለወጥ ላይ ይገኛሉ።»

©ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org

ዲያቆን ኃይለ መስቀል መደረግ ያለበትን ነገር ሲነግረኝ እኔም ሌላ ነገር ታወሰኝ። እስከ ዛሬ ድረስ ከግዕዝ ወደ አማርኛ እንኳን ያልተተረጉሙትን ብዙ መጻሕፍት፡ ፈረንጆች ወደራሳቸው ቋንቋ መልሰዋቸዋል። ለዐብነትም እንዲሆን መጽሐፈ ሥን ክሳርን መጥቀስ ይቻላል።

ለዲያቆናት ወንድሞቼም የመከረው ምክር አለ። እነሆ። «ለዲያቆናት ወንድሞቼ የምመክረው አንድ ነገር ነው። የቅዱስ እስጢፋኖስን አሰረ ፍኖት ተከተሉ። በመንፈሳዊ አገልግሎታችሁ በርቱ። በሕይወታችሁም ለሌላው አርአያ ሁኑ። በቅዳሴው ብቻ ሳይሆን በሰንበት ትምህርት ቤት አገልግሎቱም መሣተፍ ይጠበቅባችኋል። በተጨማሪም በዲቁናው ብቻ መቅረት ሳይሆን ካህናትና መነኮሳት ሆናችሁ ቤተ ክርስቲያንን ለማገልገል ራሳችሁን ማዘጋጀት አለባችሁ።»

ዲያቆን ኃይለ መስቀልን በእግዚአብሔር ስም አመሰግኜ ከመለያየቴ በፊት ያቀረብኩለት የመጨረሻ ጥያቄ አለኝ። የወደፊቱ ዓላማው ምን ይሆን?

«እግዚአብሔር ቢፈቅድልኝ ቅስና ተቀብዬ ቤተ ክርስቲያኔን ማገልገል እፈልጋለሁ። በተጨማሪም በሰዓሊነቴ የጥቁሮችን የሥዕል ጥበብ ለማሳደግ እፈልጋለሁ። ለዚህም ቆንጆ አርትስ (Konjo Arts) የሚል ድርጅት ሰላቋቋምሁ በዚያ የጀመርኩትን ሥራ በጠነከረ መልኩ እቀጥላለሁ። ለሁሉም እናንተም በጸሎት አስቡኝ።»

ወንድማችንን የጠራው አምላክ ያሰበውን ለመፈጸም እንዲያበቃው የሁላችንም ምኞት ነው። ቤተ ክርስቲያን ዛሬ የሚያስፈልጋት «ሰይፍ ዘክልኤ አፉሁ – ሁለት ወገን የተሳለ ሰይፍ» ማለት ይህ ነው። በመንፈሳዊውም ሆነ በዓለማዊው እውቀት የበለጸገ በሙሉ ልቡ ቤተ ክርስቲያንን ለማገልገል የሚፈልግ ልጅ ማግኘት። የእኛስ ሀሳብ ምንድን ነው?

ወንድማችንን እግዚአብሔር በተዋሕዶ ሃይማኖቱ፣ በሥርዓተ ቤተ ክርስቲያኑ ያጽናልን አሜን! ✣

‹ባሕርዬ ቢከፋ...›

አንድ ያልተማረ ባሕታዊ ሄዶ ከበረሃ ተቀምጦ ሳለ ሰይጣን መጥቶ «ምነው ከዚህ ብቻህን?» አለው። ያ – ከዘመድ – ባዳ፥ ከአገር–ምድረ በዳ ብሎ የመነነ ባሕታዊም ‹አጸድቅ ብዬ ነው› ሲል መለሰለት። ሰይጣኑም ዝም ብሎት ሄደ። ሰውን ከማሣሣት፣ ከእውነት ወደ ሐሰት፣ ከብርሃን ወደ ጨለማ፣ ከሕይወት ወደ ሞት ከመን ዳት የማይመለስ፣ ደከመኝ ሰለቸኝ ብሎ የማይረታ ባላጋራም ለሁለተኛ ጊዜ ወደ ባሕታዊው መጥቶ «ምነው ብቻህን?» አለው። ባሕታዊውም «ክርስቶስን ባገኝ ብዬ» ብሎ መለሰለት። «ያሁኑ ይባስ» ብሎት ሄደ።

በዘመኑ በገድሉና በትሩፋቱ የታወቀው አባ መቃርስም በባሕታዊው የደረሰውን ተረድቶ ኖሮ «ከአንተ ዘንድ ሰው አልመጣምን?» ብሎ ጠየቀው። ባሕታዊውም አልመጣም ሲል መለሰለት። አባታችን አባ መቃርስም ይነግረው ዘንድ ግድ ቢለው «መጥቶ ነበረ» ብሎ እውነቱን ነገረው። አባ መቃርስም «ምን አለህ?» ሲል ሌላ ጥያቄ አቀረበለት። ባሕታዊውም «ብቻህን ለምን ተቀምጠሃል?» አለኝ እኔም ‹አጸድቅ ብዬ› አልሁት። ዝም ብሎኝ ሄደ። ለሁለተኛ ጊዜም ተመልሶ ያንተ ጥያቄ አቀረበልኝ። እኔም ‹ክርስቶስን ባገኝ ብዬ› አልሁት። እርሱም «ያሁኑ ይባስ› ብሎኝ ሄደ።» ብሎ ተረከለት። አባ መቃርስም «ምነው እንዲህ ማለትህ? የምትጸድቀው፣ ክርስቶስንም የምታገኝ አንተ ብቻ ነህን? በዓለሙ ያለው ሁሉ ክርስቶስን የማያገኝ ሆኖ ነውን? ሁለተኛ የመጣ እንደሆነ ግን ግብሩ የከፋ ውሻን አስረው ለብቻው እንዲያኖሩት እኔም ባሕሪዬ ቢከፋ፣ ግብሬ ከሰው ባይስማማ ከዚህ መጥቼ ተቀምጬያለሁ በለው እንጂ እንዲህ አትበለው» ብሎ ሰይጣንን የሚያሳፍርበትን መሣሪያ አስታጠቀው። ከጠላት የሚወረወረውን የትዕቢት ጦር የሚመክትበት የትሕትና ጋሻ ሰጠው። በሌላ ጊዜ ያው ጥንተ ጠላት ሰይጣን ወደዚያ ባሕታዊ መጥቶ «ምነው ከዚህ ብቻህን?» ብሎ ጠየቀው። ከአባቱ ከአባ መቃርስ የተማረ ባሕታዊም «ዐመሌ ቢከፋ፣ ባሕሪዬ ከሰው ባይስማማ ከዚህ መጥቼ ተቀምጬያለሁ» ሲል መለሰለት። በትዕቢት ሊጥለው የመጣውን ጠላት በትሕትና ቢያሸንፈው «ይህንን ያደረገው አባ መቃሪ እንጂ አንተ አይደለህም» ብሎት ሄደ።

በ40ና በ80 ቀን የተጠመቁ፣ በወልደ ውሉድ – በክርስቶስ ክርስቲያን የተሰኙ በሙሉ መለያቸው፣ ሰይጣንን ድል መንሻቸው ትሕትና ቸው መሆኑን የአባ መቃርስ ሕይወት ያስትምረናል። ‹ከእኔ ወንድሜ ይበልጣል...እኔ በምግባርም፣ በሕይወትም ከሁሉ ያነስኩ ነኝ› ማለት የሚቻለው ትሕትናን ገንዘብ ያደረጉ እንደሆነ ብቻ ነው። ትሕትናን ገንዘብ ያላደረጉትማ ‹እኔ የሁሉ አለቃ ነኝ፣ የሁሉ በላይ ነኝ። ከእኔ በላይ ማን አለ? አቦ...አቦ በሉኝ...አክብሩኝ› እያለ ከሌሎቹ ጋር ሲጋጭ ይገኛል።

የእግዚአብሔር ቃልም እንዲህ ይመክረናል። ‹ሁላችሁ እርስ በርሳችሁ እየተዋረዳችሁ ትሕትናን እንደ ልብስ ታጠቁ፣ እግዚአብሔር ትዕቢተኞችን ይቃወማልና፣ ለትሑታን ግን ጸጋን ይሰጣል።› 1ጴጥ.5፥5

እግዚአብሔር አምላክ የትሕትና ሰዎች ያድርገን። አሜን። ✣

©ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org

ክርስትና በማኅበራዊ ኑሮ

በሰው ልጅ ዕለታዊ የኑር ሂደት ውስጥ ጥሩ ወይም መጥፎ የሆኑ ብዙ ክስተቶች አሉ። የእነዚህ ክስተቶች ሁናቴ የሚወሰነው ሰዎች በምናስ በው፣ በምንሠራውና እግዚአብሔር በሾ ላይ ባለው ፈቃድ መሠረት ነው። ይህም ማለት በማንኛውም ዕለታዊ ተግባራችን ውስጥ እግዚአብሔርን አስበን እርሱ እንዲዘዘን፣ እንዲስ ተግረን ሆነን በትንነት ብንንኘና ብን ሠራ «እሺ ብትሉ ለእኔም ብትታዘዙ የምድርን በረከት ትበላላችሁ።» ብሎ እንደተናገረው የእግዚአብሔር ሰላ ምና በረከት ትበላልናለች። (ኢሳ. 1፥19) አልያ ግን በደመ ነፍስ በመራት ብቻ የንስሐና የመልካም ፍሬ ማፍርያ ጊዜአችንን በከንቱ የምናሳልፍ ለምንሠራውም ነገር የእግዚአብሔርን ፈቃድ የማንጠይ ቅና ክብር ምስጋና ለርሱ ይሁንና ጌታተንና መድኃኒታችን ኢየሱስ ክር ስቶስ ከስካር እንድንጠበቅ አስተ ምሮናል። ሉቃ.21፥34

መስከርና ስካርን ማዘውተር ለኃ ጢአት ምክንያት ይሆናል። ሰውነትን ይጐዳል፣ አካልን ያጉድላል፣ ባልን ጀራን እንድንበድል ሕገ እግዚአ ብሔርን እንድንተላለፍ ያደርጋል። ይህንኑ እውነታ ጥበበኛው ሰሎሞን «...የይታ ለማን ነው? ጎዘን ለማን ነው? ጩኸት፣ ያለ ምክንያት መቁሰል ለማን ነው? የዓይን ቅላት ለማን ነው? የወይን ጠጅ በመጠጣት ለሚዘገዩ አይደለምን? የተደባለቀ የወይን ጠጅ ይፈትኑ ዘንድ ለሚከተሉ አይደለምን?...በኋላ እንደ እባብ ይነድፋል። እንደ እፉኝትም መርዙን ያፈሰሳል። ዓይኖችህ ጋለሞታዎችን ያያሉ፣ ልብህም የማናስተውል ከሆነ ፍነሜ የሉለው ጸጸትና ለቅሶ ይውጠናል። ግን ከንቱ ፀፀት።

ከዚህ እውነታ በመነሳት በአለን በት ዘመን በዓለም ላይ ያለውን የሰው ልጆች አጠቃላይና ዕለታዊ የሕይወት ጉዞ ሂደት ስናስተውል ከግናቸውም ጊዜ በበለጠ አሳዛኝ ሆኖ እናገኘዋለን።

የሰው ልጅ በሥልጣኔ እጅግ በመጠቀበት በዚህ በ21ኛው መቶ ክፍለ ዘመን ኃጢአቱ እንደ ጽድት፣ ነውሩ እንደ ክብር ሆኖ ሰውን ከአምላኩ ለይቶ፣ እንደ ባሕር ላይ ኩበት ከወዲያ ወዲህ ሲያንገዋልለው ይስተዋላል።

ይህም የሆነበት ምክንያት ሰው የሰውነቱ ምንጭ፣ የሕይወቱ የልታ የሆነ እግዚአብሔርን ትቶ ልቡናውን ከአምላኩ መልሶ የሥጋ ፈቃዱን ስለተከተለ ነው። «እግዚአብሔርን ለማወቅ ባልወደዱት መጠን እግዚአ ብሔር የማይገባውን ያደርጉ ዘንድ ለማይረባ አእምሮ አሳልፎ ሰጣቸው» ብሎ ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ እንደተናገረው ሰው በደመ ቢዛነት ከሞት አርነት ላወጣው ጌታ፣ ለሕይ ወት ጥሪ ታሉ ምላሽ ባለመስጠቱ እረኛ እንደሌለው መንጋ በመትበዝ በዝ በፈቱ መልካም መስሉ የታየውን ብቻ በመከተል ራሱን በፈቃዱ ለአብ ደት በመዳረጉ ነው። ሮሜ 1፥28።

ሰዎች ወደ ሕይወታቸው የጋበዟ ቸው የፈቃድ ዕብደቶች ብዙ ሲሆኑ በዚህ ጽሑፍ ግን አንዱን ስካርን ብቻ እንመለከታለን።

ጠግግ ነገርን ይናገራል። በባህር ውስጥ እንደተኛ ትሆናለህ። በደቀልም ላይ እንደተኛ። መቱኝ ያውም አልተሰማኝም። ጉሰ ሙኝ አላወቅሁምም። ሙቼ እነሳለሁ ደግሞም ጨምሬ እሻታለሁ ትላለህ» በማለት ስካር የሚያስከትላቸውን የውጫዊና የውስጣዊ የአካል ጉዳትን ይገልጠዋል። (ምሳ.23፥29–35)

በተጨማሪም ይህ የፈቃድ ዕብ ደት ስካር አስጸያፊ መሆኑን፣ ክክብር ማኖረዱንና ከጸጋ እግዚአብሔር መለየቱን ይበልጥ ለመረዳት ከቅዱ ሳት መጻሕፍት የሚከተሉትን ምሳሌ ዎች እንመልከት።

ሀ. ኖኅ

(በኦሪት ዘፍጥረት ምዕራፍ 6፥8 ላይ በተጠቀሰው መሠረት) በዘመኑ (በወቅቱ) በምድር ላይ ከነበሩት ሰዎች ሁሉ ኖኅ አካሄዱን ከእግዚአ ብሔር ጋር በማድረጉ በአምላኩ ፊት ምንስን ያገኘ አንድ ኖኅ ብቻ ነበር። ዘፍ.6፥8 በመሆኑም እግዚአብሔር ኃጥአንን በንፍር ውኃ ሊያጠፋ በወ ደደ ጊዜ ኖኅን ጉበኘው። በዚህም ይመጣ ዘንድ ካለው ቁጣ የሚድ ንበትን ነገረው። ኃይሉ (ቁጣው) በተገለጠ ጊዜም መርከቡን ምክንያት አድርጉ ኖኅን ከነቤተሰቡ አዳነው።

ይሁን እንጂ እግዚአብሔር ቁጣ ውን በትዕግሥት፣ መዓቱን በምሕረት ለውጦ በምድር ፍሬን በሰጠ ጊዜ ኖኅ ካመረተው ወይን ጠጅ በመደባለቀ ልቡናው እስኪለወጥ አብዝቶ ጠጣ። ሰውነቱም ዛለ በእግዚአብሔር ፊት ምንስን አግኝቶ በረድኤቱ ጥላ ተከልሎ እንዳልዳነ ሰውነቱ ዝሎ በድንኳኑ ውስጥ እርቃኑን ተገኘ። ልጁም ሳቀበት። (ዘፍ.9፥20–24)

ዛሬም እንዲሁ የምድር ትቢያ ስንሆን በችግር ቀን የረዳንን፣ ዓለም በድን በዘጋችብን ሰዓት መጠጊያ የሆነንን ጌታ ብርጭቆና መለኪያ በጨበጥንበት ሰዓት የምንረሳው፣ በመጠጥ ብዛት ሞት ሲለን ባመሰ ገንበት አፋችን እግዚአብሔር የባረካ ቸውን የምንረግም፣ እንዲሁም እግዚ አብሔር ለወዳጆቹ ለልጆቹ ያደረ ገውን ቸርነት አስበን በምናከብርበት የበዓል ቀኖች ጥንብዝ ብለን ካልሰከርን በዓል የማይመስለን ብዙ ነን። በዚህም ኖኅ እርቃኑን (ራቁቱን) እንደተኛ በስካር መንፈስ በምንፈጽመው ገብረ–ኃጢአትና ለወገኖቻችን በምንፈጥረው መሰናክል ከልጅነት ክብራችን አንሰን፣ ከጽድቅ ተራቁተን፣ የጎፍረትን፣ የጎዘንና የዋይታን ከል ለብሰን ራሳችንን በፈቃዳችን ለመከራና ለፍርድ እናዘጋጃተናል።

ለ. ሎጥ

ኃጢአት ከሰፈነበትና ከገነነበት የሰዶም ከተማ በእግዚአብሔር ቸርነት በመላእክት ተራዳኢነት በእግዚአብሔር መቅሰፍት (ከቁጣ) የዳነ ታላቅ ሰው ነው። በከተማይቱ ከነበሩት ሁሉ ትንነት ተገኝታበታለችና የርሱ ታዛዥነት የበጀው ለራሱ ብቻ ሳይሆን ለቤተሰቡም ጭምር በመሆኑ ሴቶች ልጆቹ ከርሱ ጋር ወጥተዋል። አባት ያበጀው ለልጅ ይበጀው እንዲሉ። ሆኖም ይህ እግዚአብሔር ከኃጢአት እሳት ያወጣው ሰው በወይን ስካር የማይገባ ሥራ በመሥራቱ በታሪክ ሲወሳ ይኖራል።

እንደዚሁም እግዚአብሔር ከኃጢአት ከተማ ከኃጢአት ኑር ፀዋትው መከራን በሥጋ ተቀብሎ ካወጣን በኋላ የርሱ ማደሪያ (ቤተ መቅደስ) ይሆን ዘንድ የቀደሰውን ሰውነታችንን በአልኮል በማደንዘዝና በመረዝ የተደረገልንን ታላቅ የቸርነት ሥራ በመርሳት የስካር እንቅፋት እየሆነብን በየቦታው በቤታችን፣ በጉረቤቶቻችን፣ በመሥሪያ ቤታችን በአጠቃላይም በዕለታዊ ኑሮአችን ውስጥ ደግመን ደጋግመን በኃጢአት የወደቅን ብዙዎች ነን።

ቸርነት የባሕሪ ገንዘቡ የሆነ እግዚአብ ሔር ራስን የመግዛት ጸጋ አድሉናል። ይህን ተገንዝበን ኃጢአት ሱስ (ልምድ) የሆነብን ሰዎች በሰሚት መመራቱን፣ ለሥጋ ፈቃድ መገዛቱን ትተን፣ በእምነት ሆነን

የፈቃድ ዕብደት

ከዲ.ስንታየሁ አባተ

©ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org

እግዚአብሔርን በመለመን ለዚህ አስነዋሪ ድርጊት ከሚዳርጉት ነገሮች ልንርቅና ልንቆጠብ ያስፈልጋል።

ሐ. ንጉሥ ብልጣሶር:-

የናቡከደነጾር የልጅ ልጅ የናቦኒዶስ ልጅ እና የባቢሎን የመጨረሻው ንጉሥ ብልጣሶር አንድ ቀን ለሺህ መኳንንቱ የመጠጥ ግብዣ አደረገ። ልቡናው በአምልኮ ጣዖት ነድዷልና ወይን ጠጁን አብዝቶ በጠጣ ጊዜ በበደል ላይ በደልን ጨመረ። አባቱ ናቡከደነጾር በኢየሩሳሌም ከነበረው ቤተ መቅደስ ያስመጣቸውን (ያመጣቸውን) ንዋየ ቅዱሳት እንዲያቀርቡ አዘዘ። በእግዚአብሔር ስም የተቀደሱትን ጽዋዎች የወይን ጠጅ መጠጫ አደረገ። አልፎ ተርፎም በንዋያቱ እየጠጣ ልቡናውን ያሰወሩ አማልክትን ያመሰግን ጀመረ።

በመሆኑም እግዚአብሔር መዘነው፣ ናቀው። በምትታይ እጅ በተለሰነው ግንብ ላይ በመቅረዙ አንጻር «ግዔ ቴቄል ፋሬስ እግዚአብሔር መንግስትህን ቆጠረው ፈጸመውም በሚዛን ተመዘንህ ቀልለህም ተገኘህ፣ መንግስትህ ተከፈለ» ለሚዶንና ለፋርስ ሰዎች ተሰጠ።» ሲል አመለከተበት። እርሱ እንደ ተናገረው በዚያች ሌሊት ንጉሥ ብልጣሶር ተገደለ። የእግዚአብሔርም ቃል ተፈጸመ። ዳን.5፥1–ፍ.ም)

በዘመናችን ብዙዎች መጠጥ ባዩ ባሸተቱ እና ቤቀመሱ ቁጥር እንደ ንጉሥ ብልጣሶር በኃጢአት እየባሱ ይሄዳሉ። በሰካርም የእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ የሆነ ሰውነታቸውን ግበላሸቱ ሳያንሳቸው እንደ ንጉሡ በተከበሩና በተቀደሱ ንዋየ ቅድሳትና እግዚአብሔር ቀብቶ በሾማቸው የቤተ ክርስቲያን አባቶቻችን ላይ ከንቱ የሆነውን የሚሠሩና የሚናገሩ ብዙዎች ናቸው።

እነዚህን ለአብነት ያህል አቀረብን እንጂ በታሪክ ውስጥ በዚህ የፈታድ ዕብደት በሆነው ሰካር የተጉዱ፣ ከጸጋ እግዚአብሔር የተለዩ አያሌ ናቸው። በአጠቃላይም ከላይ እንደተመለከትነው ሰካር በሰው ልጅ ሕይወት ላይ ይህ ነው የማይባል ጉዳት የሚያደርስ፣ ከክብር የሚያዋርድ፣ ከእግዚአብሔር የሚያርቅ የረከሰ ድርጊት ነው።

በዘመናችን ካለው እውነታ አንፃር ሰካር በሰው ልጅ ላይ የሚያስከትለውን ጉዳት በጥቂቱ ብንመለከት።

ሰካር:-

ሀ. ሕገ እግዚአብሔርን ያስፈርሳል (ከሃይማኖት ያወጣል) ጥበበኛው ሰሎሞን «...ዓይኖችህ ጋለሞታዎችን ያያሉ...» በግለት እንደ ተናገረው ምጣኔ የሌለው መጠጥ ወደ ሰካር፣ ሰካርም ጎሊናን ወደ መሳት፣ እንደዚያም እያለ ወደ ፍትወትና ምንዝር ይስባል።

- የፍትወት ሰካርም – ሕገ እግዚአብሔር ያስረሳል
- ከጋብቻ ውጪ የሆነ መዋለድን ያመጣል
- ለተለያዩ የውስጥ በሽታዎች ያጋልጣል። በተለይም በዘመናችን ብረት ሰብስብ (ግግኒት) ብረት ብቻ እየለየ እንዲሰብ ለፈጣሪው አልገዛ ብሎ የአምላኩን ሕግ የጣሰ የሰውን ልጅ ብቻ እየለየ በመቅሰፍ ላይ ያለው ቀሳፊ በሽታ ኤድስ በሰፈው ለመዛመት ይህ ዓይነቱ በመጠጥ የደከመ ሕይወት የተመቻቸ ሁኔታን ይፈጥርለታል።

ለ. የአካል (ውጫዊና ውስጣዊ) ጉዳትን ያስከትላል።

ሐ. ቤተሰባዊ ችግሮች

የቤተሰብ ሰላም መታወክ፣ የኢኮኖሚ መታወስ የትዳር መፍረስ ያመጣል። ልጆች ሲጫወቱ «ሰካራም ቤት አይሠራም፣ ቢሠራም ቶሎ አይገባም፣ ቢገባም በር አይዘጋም ቢዘጋም ቶሎ አይተኛም» ይላሉ። ላስተዋለው ግሩም አባባልና ከሰካራሞች ሕይወት ጋር በትክክል የተዛመደ ነው።

በዚህ የተነሣ የብዙዎች ትዳር ፈርሷል። ብዙ ጨቅላ ሕፃናት አላዳጊ አጥተው ለጉዳና ተዳዳሪነት ሕይወት ተዳርገዋል።

መ. የማኅበራዊ ኑሮ ችግሮች

ምንም እንኳን «የሚችለኝ ቤቴ ነው።» የሚል አባባል ሊነገር ቢሰማም ሰው በዕለታዊ ኑሮው ውስጥ በተለያዩ ሂደቶች ከሌሎች ጋር ሕይወቱ (ኑሮው) የተሳሰረ ነው። ሰው በኅዘን፣ በደስታ፣ በጉርብትና በመሳሰሉት ነገሮች ይገናኛል። እንደ ችሎታውና እንደ አውቀቱ መጠን ባለው ሁሉ ይረዳዳል። በተለይም የክርስትናን ሕይወት እውነታ ስናስተውል ግለኝነት (ራስ ወዳድነት) የሚንጸባረቅበት የሕይወት መድረክ ሳይሆን አንዱ የአንዱን ሸክም የሚሸከምበት፣ የላሉ እጆች የሰለሉ ጉልበቶች የሚቀኑበት፣ ፍቅርና ሰላም እንዲሁም መተሳሰብ የሰፈነበት የሕይወት ጉዞ ነው። (ዕብ.12፥12)

ይህ ሁሉ ግን እውን የሚሆነው እያንዳንዱ ክርስቲያን ፍቅረ መስቀሉን በልቡናው ጽፎ በሁለት ልብ ማንከስን አቁሞ መላ ሰውነቱን (ሕይወቱን) ለሕይወት ባለቤት ለእግዚአብሔር በቅንነት አስገዝቶ ሲኖር ብቻ ነው።

ይህ ሁሉ ግን ታላቁ ፍጡር ሰው ሕግን ተላልፎ በበደል ላይ በደልን በመጨመሩ ፍጹም ተዘንግቷል።

ከዚህ እውነታ በመነሳት ሰካራሞች በማኅበራዊ ሕይወት ውስጥ ያላቸውን ገጽታ ስናይ የሚያሳዝን ሆኖ እናገኘዋለን።

ሰካራም

- አደራ አይጣልበትም።
- ክበረታ አያገኝም።
- የመጥፎ ሥነ–ምግባር ማጣቀሻ (ምሳሌ እየሆነ ይቀርባል።)

በአጠቃላይ ሰካር የጤና መታወክ፣ የአካል ጉዳትን፣ የንዝህላልነትን፣ የትዳር መፍረስን፣ የሰላም ማጣትን በሰውና በፈጣሪ ዘንድ መናቅን ያስከትላል።

እንግዲህ ይህ ሰዎች በራሳቸው ፈቃድ በግል ሕይወታቸውም ሆነ በማኅበራዊው ይህ ነው የማይባል ጉዳት የሚያስከትል ከሆነ አባግዕ ልጆቿ ከዚህ እንዲጠበቁና በአጠቃላይ ኦርቶዶክሳዊት ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያናችን ስለመጠጥ፣ ስለ ሰካር ያላት ትምህርት ምንም እንደሚመስል ከብዙ በጥቂቱ ቀጥለን ለማየት እንሞክራለን።

1. «ኃያል (ንጉሥ መምህር ባለአዕምሮ) ኤፒስቆጶስ፣ ንጉሥ፣ የሚፈርድ ሁሉ ወይን አይጠጣ። ምክንያቱም መምህር ማስተማርን፣ ንጉሥ መፍረድን እንዳይተው። ወይን ከጠጣ መምከር፣ ማስተማር፣ እውነት መፍረድ አይችልምና። ለካህናትም ለምዕመናንም ይህንን እንነግራቸዋለን።» ፍ.ነገሥት – ምዕ.50 (በእንተ ሰካር)

2. ሀ. «ወይን አትጠጣ፣ ቀምሰህ ፈጣሪውን ለማመስገን ያህል ብቻ ይሁን እንጂ። እንደጢሞቴዎስ ብትታመም፣ ከገድል ጽናት የተነሣ በጽኑ ደዌ ብትያዝ ግን ከወይን ጥቂት ጠጣ እርሱ ለሥጋ ሕይወት ይሆንልሃልና» (1ኛ ጢሞ.5፥23፣ ሉቃ.21፥34–36) ሃይማኖተ አበው – ዘሠለስቱ ምዕት – ምዕ.21፥17–18

«ወይን አብዝቶ ወደ መጠጣት ብትመለስ ግን ራስህን ለሁለት ደዌ (ለደዌ ነፍስ ለደዌ ሥጋ) አሳልፈህ መስጠትህ ነው። አንተስ ከአንዱ ጥዋ አትተላለፍ። ቢበዛም ሁለት ይሁን። ይህ ትእዛዝ ለመነኮሳት፣ ለካህናት፣ በትሩፋት ለሚጋደሉና ጸምን ለሚያዘወትሩ፣ በሕግ ኑረው ለመነኮሱ፣ በድንግልና ለጸኑ፣ በንጹሕ ግቢ ላሉ ክርስቲያኖች ሁሉ ነው።»

«ወይን በመጠጣት አትስከሩ። ዝሙት ነውና። የቀናውንም ነገር ይከለክላልና»

በአጠቃላይ ከላይ በተጠቀሱት መጻሕፍቶቿና በየትምህርት አደባባይዋ ቅድስት ቤተ ክርስቲያናችን ስካርንና የስካር ውጤቶችን ስታወግዛቸው ኖራለች። አሁንም

©ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org

ልጆቿ በስካር እንዳይጠመዱ አጥብቃ ታስተምራለች።

እዚህ ላይ አንድ በአፅንኦት ልናተኩርበት የሚገባው ጉዳይ አለ። ይኸውም ምንም እንኳን ከላይ ስለስካር ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያናችን ያላትን ትምህርት ብንጠቅስም ብዙውን ጊዜ ሰዎች ይህን ቃል ተላልፈው አለልክ በመጠጣት ሲሰክሩና ለወገኖቻቸው መሰናክል ሲሆኑ በመናፍቃንም ቤተ ክርስቲያናቸውን (እምነታቸውን) የሚያስዘልፉ አንዳንድ ሰዎች አይታጡም። ሌሎች የቤተ ክርስቲያኒቱ ተቀናቃኞችም ቤተክርስቲያንን ለመንቀፍና ለማስነቀፍ ሥራ ፈቶችን እያ ጨው በልብሱ-ካህን የሚያዘምቱ መኖራቸው ይታወቃል።

ብዙውን ጊዜ መናፍቃን በዚህ በተሳሳተ መንገድ ተመርተው በእምነቱ ጸንቶ የሚኖረውን ምእመን የሰከረውን እንደ ምሳሌ በማቅረብ ሊያስቱት ከመጣራቸውም ባሻገር መንፈሳውያን አባቶችን በመንቀፍ ኢ-ክርስቲያናዊ ሥራ ሲሰሩ ይስተዋላሉ።

ከብዙ በጥቂቱ ከላይ እንደ ተገለጠው ሰውነታችንን ከስካርና ክርኩሰት ሁሉ ጠብቀን እንደ እግዚአብሔር ቃል ልንኖር ያስፈልጋል።

«ስካርን ለመከተል በጠዋት ለሚግልዱ የወይን ጠጅም እስኪያቃጥላቸው እስከ ሌሊት ድረስ ለሚዘገዩ ወየውላቸው።...የወይን ጠጅም በግብዣቸው አለ። የእግዚአብሔርን ሥራ ግን አልተመለከቱም። እጁም ያደረገችውን አላስተዋሉም» ይላል እግዚአብሔር በነቢዩ ኢሳይያስ አንደበት። ኢሳ.5፥11-12

ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስም በ1ኛ ቆሮ.6፥10 ላይ «...ሰካራሞች ተሳዳቢዎች...የእግዚአብሔርን መንግስት አይወርሱም።» ሲል በፈቃድ ዕብደት የነጉዱ ሰዎች የሚጠብቃቸውን ፍርድ አውቀው በጉ ምግባር ወደ መፈፀም እንዲመለሱ አበክሮ ይመክራል።

እንግዲህ ጥበበኛው ሰሎሞን «አላዋቂነትን ትታችሁ በሕይወት ኑሩ በማስተዋልም መንገድ ሂዱ።» ብሎ እንደተናገረው (ምሳሌ 9፥6) ክርስቲያኖች ከእግዚአብሔር መንግስት ውጪ የሚያደርገንን ስካር ከሕይወታችን ልናርቅ ይገባል። መድኀኒተ ዓለም ክርስቶስ ባሳየን መንገድ፣ በተወልን ምሳሌ በቀን፣ በብርሃን እንደምንሆን በአግባብ ልንመላለስ ይገባናል እንጂ በመጠጥ ሱስ ልንያዝ አይገባንም። የእግዚአብሔር ሰዎች በእምነት፣ በምግባር በትሩፋት ይኖራሉ እንጂ ለሱስና ለስሜት አይገዙም።

ከዘመኑ ትውልድ ብዙውን ለዚህ ለፈቃድ ዕብደት ከዳረገው ስካር ተለይተን ሰውነታችንን ለርሱ ቅዱስ መስዋእት አድርገን እንድናቀርብ የአምላካችን ቅዱስ ፈቃድ ይሁንልን። የወላዲተ አምላክ ረድኤት በረከት አይለየን። አሜን። ✥

መስከረም ለእግዚአብሔር

ክርስትናና ከአንድ በላይ የትዳር ጓደኛ (Polygamy)

‹አይ የዘመኑ ልጅ...› እያሉ ወላጆች ሲማረሩና ሲያዝኑ መስማታችን ተለምዷል። የሚገርመው ግን ይህ አስቸጋሪና እነርሱ ዘወትር የሚማረሩበት ትውልድ ከየት እንደመጣ መለስ ብለን ስንመለከት ራሳቸው የዘመኑ ወላጆች ናቸው አስገኚዎቹ። ታዲያ መማረሩን ምን አመጣው? ‹አይ የዘመኑ ወላጅ›። በዚህም ርዕስ ለመጻፍ የተነሣነው ይህንን የዘመኑን ትውልድ ያፈራውን የዘመኑን ወላጅ ሕይወት በመጠኑ መዳሰስ አስፈላጊ ሆኖ በማግኘታችን ነው።

እንደሚታወቀው ክርስቲያናዊ ጋብቻ ከሌሎች ጋብቻዎች ሁሉ የተለየና ቅዱስ ነው። የሚመሠረተውና የሚመራው በቅዱስ እግዚአብሔር መንፈስ ነውና። በክርስቲያናዊ ጋብቻ ከአንድ በላይ ሚስት ለአንድ ባል ወይም ለአንድ ሚስት ከአንድ በላይ ባል አይፈቀድም። «ለእያንዳንዱ ለራሱ ሚስት ትኑረው ለእያንዳንዲቱ ደግሞ ለራሷ ባል ይኑራት።» 1ቆሮ.7፥2። በተጨማሪም ሁለቱ ተጋቢዎች ፍጹም በሆነ ውሕደት አንድ ይሆናሉ። ስለዚህም ሚስት በገዛ ሥጋዋ ላይ ሥልጣን የላትም። ሥልጣን ለባልዋ ነው እንጂ፤ እንዲሁም ደግሞ ባል በገዛ ሥጋው ላይ ሥልጣን የለውም ሥልጣን ለሚስቱ ነው እንጂ። 1ቆሮ.7፥4።

እውነቱ ይህ ሆኖ ሳለ የዘመናችንን ሰውኑሮ ስንመለከት ግን ክርስትናን በስም እንጂ በግብር አያውቁም ያሰኛል። የቀብር ሥፍራ እስካገኘ ድረስ የቤተ ክርስቲያንን ጉዳይ እንደራሱ ጉዳይ አይመለከትም። ለነገረ-ቤተ ክርስቲያን ሁል ጊዜም ዳር ቆሞ ታዛቢ ነው። በሥርዓተ ተክሊል ግባባትን፣ ቅዱስ ቁርባን መቀበልን፣ በአንድ ሚስት ጸንቶ መገኘትንና መተማመንን፣ ወዘተ. ከረሳ ሰንብቷል። አሁን አሁንማ የንስሐ አባት ያላቸውን ቤተሰቦችና የክርስትና ስማቸውን የሚያስታውሱ ምዕመናንን ማግኘት እየከበደ መጥቷል።

ጥንት በሐዋርያት ዘመን የቆሮንቶስ ክርስቲያናች የሐዋርያው የቅዱስ ጳውሎስን ትምህርት ረስተው፣ ትዕዛዙንም ተላልፈው አንዱ ብዙ ሚስቶች ያገባበት ጊዜም ነበር። ያ ሰው ሲሞት ሚስቶቹን ልጆቹ ይወርሳሉ። እንጀራ እናቶቻቸውንም ያገባሉ» ነገር ግን «ክርስቲያናች» ናቸው! ይህንን በአረማውያን እንኳን የማይደረግ ኃጢአት ሲሰማ ሐዋርያው እጅግ አዝኖ ገሰጻቸው። እንዲህ ዓይነቱን ሰው ከመካከላችሁ አስወግዱት እስከ ማለትም ደረሰ። 1ቆሮ.5፥1-2።

ለምሳሌ በዘመናችንም ያለው የአንዳንድ ክርስቲያኖች ክርስቲያናዊ ሕይወት ይህን ያህል ልቅና የተጋነነ ሆኖ ባናገኘውም የሚመሳሰልበት ሁኔታ አለ። ከአንድ በላይ ሚስት አግብቶ መኖር የተለመደ ነውና። በሥራ ምክንያት ከቦታ ቦታ የሚዘዋወሩ ሰዎች የግድ «ቅምጥ» ወይም ተጨማሪ ሚስት ይኖራቸዋል። በቀድሞ ጊዜ አንድ ሰው ሚስት እያለችው ወደ ሌላ ቢሄድ አልታመነምና በሥራው ያፍራል። ሃሜቱም አያስቆመውም።

ስለዚህ አላስችል ብሎት ቢያደርገው እንኳን በድብቅ ነው። እያደር ግን ይህ ሁኔታ ተለወጠና አንድ ሰው በአንድ አካባቢ ሦስትና አራት ጕረቤታም ሚስቶች ማግባት ተለመደ። እንደ ትክክለኛ ነገርም ተቆጠረ። በተለይ ከ16ኛው መቶ ክፍለ ዘመን ወዲህ በነገሡት ነገሥታትና መሳፍንት ዘንድ የጭን ገረዶችንና ቅምጦችን ማዘውተር ለመለመዱና ለመስፋፋቱ ትልቅ አስተዋጽኦ አድርጓል።

እንግዲህ አንዳንድ የዘመኑ ወላጅም የዚያ ትውልድ ወራሽ ነውና የሚስቶቹን ሰምና የልጆቹን ብዛት ለማወቅ ቢቸገር አይፈረድበትም። ግን ምን ያደርጋል ሁሉም ክርስቲያን ነን ይላሉ፣ ከክርስትናው ሕግ ግን ወጥተዋል። ለመሆኑ ይህ ኢ-ክርስቲያናዊ የሆነ ምግባር እንዴት ሊዘውተርና ሊስፋፋ ቻለ? የተወሰኑትን ምክንያቶች ለማየት እንሞክራለን።

1. የባሕል ተጽዕኖ፤

ማንኛውም ሰው በዓለም ሲኖር የሚኖርበት አካባቢ ተጽዕኖ ያደርስበታል። በመሆኑም ቀስ በቀስ በአኗኗሩ፣ በአመጋገቡ፣ በአለባበሱና በአጠቃላይ የአኗኗር ሁኔታው አካባቢውን ሊመስል ብሎም በአካባቢው ሊዋጥ ይችላል። በክርስቲያኑ ዘንድ እየተለመደ የመጣው የዚህ ከአንድ በላይ የማግባት ባሕልም ከዚህ የተለየ አይደለም። ከሌሎች እምነት የለሾች ወይም ከአንድ በላይ ሚስት ማግባትን የሚያዘወትሩ ሰዎች ጋር አብሮ በመኖር እነርሱ የሚያደርጉትን ማድረግ ለመደ። እያደርም ለልማዱ ተገዥ ሆኖ እንደ ሕግ ቆጥሮት በአንድ ሚስት ብቻ ተወስኖ መኖር ይከብደው ጀመር። በተለይ በቂ ሀብት ካለው ሁለትና ሦስት ማግባት እንደ ሀብት ማሳያ ተቆጠረ።

ነገር ግን የክርስትና ሕይወት አካባቢው ሊመቸን የምንኖረው፣ ሳይመቸን ደግሞ የምንተወው ሳይሆን በሄድንበት ሁሉና እስከ ሕይወታችን ፍጻሜ ልንኖረው የሚገባን ነው። ለዚህ ነው ጌታም የክርስቲያኖችን ሕይወት ተራራ ላይ ባለች መብራትና ዓለምን በሚያጣጥጥ ጨው የመሰለው። ማቴ.5፥14። ክርስቲያን ብርሃን ነውና በሄደበት ሁሉ በአካባቢው የነበረውን ጨለማ ያስወግዳል። ጨውም ነውና አልጫውን ያጣፍጣል።

©ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org

2. ከቃለ እግዚአብሔር መራቅ

ክርስቲያን ከቃለ እግዚአብሔር እየራቀ በሄደ ቁጥር ኃጢአትንና ጽድቅን መለየት ያቅተዋል። በአእምሮው አስቦ የሠራው ሁሉ ትክክል እየመሰለው ይመጣል። አንዳንድ ጊዜ ትክክል አለመሆኑን ቢያውቅም ከቃለ እግዚአብሔር በመራቁ ትሕትናው ስለሚጠፋበት በመመለስ ፈንታ ለሥጋ ፈቃዱ የሚያመቸውን ይፈጽማል።

ለምሳሌ ከአንድ በላይ ሚስቶች ያሉትን ሰው ቢጠየቅ፣ ከአንድ በላይ ሚስት ማግባት ኃጢአት እንደሆነ ያውቃል። ስለ ራሱ ግን ሲነግበት በዓለም መኖር በጣም አስቸጋሪ እንደሆነ ብቻ ተናግሮ ግለቱን ይመርጣል። እንዲያውም የሚያውቀውና የሚኖረው አልገናኝ ሲለው ስለዚያ ጉዳይ እንዲነሳበትም አይፈልግም። ስለዚህ እስከ መጨረሻው በሰው የንዝብ ብዛት ልክ በሚስት ላይ ሚስት እየጨመረ መኖርን ይመርጣል።

‹እኔም ዛሬ አንተን የማዝዘውን ይህን ቃል በልብህ ያዝ። ለልጆችህም አስተምረው፣ በቤትህም ስትቀመጥ፣ በመንገድም ስትሄድ፣ ስትተኛም፣ ስትነሣም ተጫወትው።› ዘዳ.6÷6–9

3. የንስሐ አባቶችና የምዕመናን ግንኙነት መላላት

በቤተክርስቲያን ሥርዓት አንድ ምዕመን ግንኙነቱን ሥራ ሊሠራ ሲያስብ የንስሐ አባቱን አማክሮ የሚሆነውንም ተወያይተ ውበት ነበር። በዘመናችን ግን አንዳንድ የንስሐ አባቶች ልጆቻቸውን በሚገባ መከታተል ተስኗቸው ምዕመኑ የማይገባ ሥራ ሲሠራ እያዩ በዝምታ ያልፋሉ። ምዕመናኑም ቢሆን የንስሐ አባት የሚይዙት ሊማሩና ሊመከሩ ሳይሆን የንስሐ አባት የላቸውም እንዳይባሉ በማሰብ ብቻ ነው። ስለሆነም የምዕመናንና የንስሐ አባቶች ግንኙነት ላልቷል። በዚህም የምዕመናን የክርስትና ሕይወት ተዳክሞ ብዙ ሚስቶች እስከማግባት ተደርሷል። እንዲያውም አንድ ሚስት ብቻ የሚያገባው ሥልጣነ ክህነት ያለው ብቻ እንደሆነም ይታሰባል። በዚህ ሁኔታ ከቀጠለ ወደፊት የምዕመናን ሕይወት ወዴት እንደሚያመራ መገመት አያስቸግርም። (ፍትሐ.ነገ.መንፈ. አንቀጽ 6)

በአጠቃላይ በማናቸውም ምክንያት ይፈጸር ከአንድ በላይ ሚስት ወይም ሴል ወይንድ ጊዜ ማግባት (Polygamy) በክርስቲያናዊ ሕይወት ሊኖር የማይገባ ሌላ የሥነ ዝሙትና ሥርዓት አልበኝነት ነው። እንደዚህ ዓይነቱ ሕይወት በምድር ልጆች በእውነ ተኛው የወላጆች ፍቅር እንዳያድጉ ያደርጋል፤ ራስን ለአባላዘር በሽታ ያጋልጣል፤ የኑር ሰላምን ያሳጣል፤ አንዲት ሔዋን ለአንዱ አዳም፣ አንድ አዳም ደግሞ ለአንዲቷ ሔዋን መፈጠራቸውን አውቆ ራስን በመግዛት በታማኝነት በአንድ መጽናት ያስፈልጋል። ለሁሉም የድንግል አማላጅነት የቅዱሳን ጸሎት አይለየን።

አሜን

ቤተ ክርስቲያንህን ዕወቅ

ኢትዮጵያ ሀገራችንን በመላው ዓለም ደረጃ እንድትታወቅ ካደረጓት የታሪክ ቅርሶች አብዛኞዎቹ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ሀብቶች ናቸው። እነዚህ ሀገራቱን የሚዳ ላይ ቤተ መዘክሮች ያሰጀት ሀብቶችም በቅዱሳት አባቶቻችን ታታሪነት ከጥፋት ድነው እዚህ የደረሱ ናቸው። በተለ ይም በጥቁሩ ዓለም ያለች ሐዋርያዊት ቤተ ክርስቲያን መሆኗን የማይፈልጉ ጠላቶቿ ትም ህርቷን ለማጥፋት መጀመሪያ ንዋየ ቅድሳትን ማጥፋት አስፈላጊ መሆኑን ስለተገነዘቡ ይህንን ዓላማቸውን ከገብ ለማድረስ ያላደረጉት ጥረት አልነበረም። ይህንንም ባለፈው ዕት ማችን በዝርዝር ማቅረባችን ይታወሳል።

በእሳት ከመጋየቷ በፊት ንጉሡ የሰበሰቧቸው መጻሕፍት በሙሉ እንዲዘረፉ ተደረገ። ቁጥራቸው ከ300 በላይ የሆኑት እነዚህ ውድ ሀብቶችም ተዘርፈው ባሕር ማዶ ተሻገሩ። እነዚህ የሀገራችን ቅርሶች ወደ ጥንቱ የብሪቲሽ ሙዚየም (British Museum) የዛሬው ብሪትሽ ላይብረሪ (British Library) ቦድሌይን ላይብረሪ (Bodlain Library) ካምብሪጅ ዩኒቨርሲቲ ላይብረሪ፣ ርያል ላይብረሪ እና ወደተለያዩ የእንግሊዝ የትምህርት ተቋማት ተወሰዱ። በመላው አውሮፓ ዝናቸው የተሠራጨው የእነዚህ ቅርሶችም ድንቅነት ሌሎችም ዓይናቸውን በቤተ ክርስቲያናችን ሀብት ላይ እንዲጥሉ አደረጋቸው።

የንዋየ ቅድሳት ዝርፊያ ከትናንት እስከ ዛሬ

(ከኤፍሬም አሸቴ – ክፍል ሁለት)

በዘመነ መሳፍንት ቤተ ክርስቲያን ከደረሰባት ችግር ሙሉ በሙሉ ሳትላቀቅ በስመ–ክርስቲያን ለዘመናት ቤተ ክርስቲያናችንን ሲያደሙ የነበሩት የሮማ ካቶሊኮች ቋስል (የቅብዓትና የጸጋ ትምህርት) በማመርተዙ የተዋሕዶ ሊቃውንትና ምዕመናን በትብዓ ቶችና በጸጋዎች ተሳደዱ–ተንገላቱ። ነገር ግን በደሙ የመሠረታት ኢየሱስ ክርስቶስ ነውና አልተናወጸችም። ጠላቶቿ አለቁ–እርሷ ግን ሕያው ናት።

5. እንግሊዞችና የመቅደላ ዝርፊያ (The British Expedition and Looting at Maqdala)

እንግሊዞች ባሕር ተሻግረው ድንበር ጥሰው፣ ክተት አስነግረው አፄ ቴዎድሮስን ጦርነት በገጠሙ ጊዜ የተፈጠረው ሁኔታም ቤተ ክርስቲያንን የሚነካ ታሪክ ትቶ ወግለፉ ለመተተስ እንገደዳለን። በመትቱ አፄ ቴዎድሮስ ራሳቸውን ገደልና ጦርነቱም ፀፈረንጆቹ አሸናፊነት ተፈጸመ። ከዚያ ወዲህ መቅደላ ከመቅደላም በፊት ሆነ በኋላ የተደረጉ ብዙ ዝርፊያዎች ነበሩ። ለምሳሌ በ18ኛው መቶ ክፍለ ዘመን ወደ ኢትዮጵያ የመጣው ስኮትላንዳዊ የወሰዳቸው መጻሕፍት ዛሬ ድረስ አክስፎርድ በሚገኘው የቦድሌይን ላይብረሪ ይገኛሉ። ሌላው ጀርመናዊ ላይንቲስት ኤድዋርድ ሩፐል (Edward Rupell) እጅ የገቡትን ወደ ፍራንክፈርት ሲወስድ፣ ፈረንሳዊው አንቶኒ .ዲ. አዲዲ የወሰዳቸውም ቢፓሪሱ ቢብሉቴክ ናሽናሌ ተቀምጠዋል። ቢሆንም ግን የመቅደላው ዝርፊያ ይቋጫቱ ተመላሽ አልተሞከሰትም።

6. 1863 ዓ.ም እስከ 1933 ዓ.ም

አፄ ዮሐንስ ሥልጣን ከጨበጡበት 1863 ዓ.ም እስከ ጣሊያን ፋሺስት ከኢትዮጵያ መባረር (1933 ዓ.ም) ያለው ዘመንም ቤተ ክርስቲያን ከመከራ ያልተለየችበት ትርሶጅም ለጥፋት የተጋለጡበት ወቅት ነበረ።

«ዶሪኖው የቁስ ንጉሥ» የሚባሉት አፄ ዮሐንስ መንፈሳዊ ሰው ስለነበሩ በግራኝ አህ

©ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org

የቤተ ክርስቲያን ታሪክ

(ከብርሃኑ ነበና – ካለፈው የቀጠለ)

መድ ወረራ ዘመን ከጠፉት አብያተ ክርስቲያናት አብዛኛዎቹን አሳንፀው ነበረ። ለምሳሌም የደብረ ሊባኖስን ገዳም ግራኝ ካቃጠለው በኋላ በመጀመሪያ ያሠሩት እንዲሁም በቅድስት ሀገር ኢየሩሳሌም የምትገኘውን የደብረ ገነት ኪዳነ ምሕረት ቤተ ክርስቲያንም ያሳነፁት እርሳቸው ነበሩ።

አፄ ዮሐንስ በሱዳን መሐዲስቶች (ደርቡሾች) ከተገደሉ በኋላ ቤተ ክርስቲያን ብዙ መከራ ደርሶባታል። ወራሪዎቹ ጎንደር ድረስ በመግባት አያሌ አብያተ ክርስቲያናትን የዓለም ውድ ንብረት ሊለውጣቸው ከማይችላቸው ነዋያተ ቅድሳት ጋር አቃጠሉ፣ የቀረውንም ዘረፉ።

ከዚህም በኋላ ቢሆን ቤተ ክርስቲያን በባዕዳን ይደርስባት የነበረው መከራና ችግር ባይቀልላትም በተለይ በጣሊያኖች የተፈጸመው ግን ገደብ ያለፈና ታሪክ የማይዘነጋው ነው። በ1928 ዓ.ም ፋሺስት ጣሊያን በሙሶሎኒ መሪነት በኢትዮጵያ ላይ ባወጀችው ጦርነት ዋና የጥፋት ዓላማ የነበሩት አብያተ ክርስቲያናት፣ ገዳማትና አድባራት፣ ካህናትና ዲያቆናት፣ ምእመናን፣ ባሕታውያንና መነኮሳት እንዲሁም ዘመን የማይተካቸው ንዋያተ ቅድሳት ነበሩ።

በተባበሩት መንግሥታት ስታቲስቲክስ መሠረት 2ሺህ አብያተ ክርስቲያናትና ገዳማት ተቃጥለዋል። የታሪክና የሃይማኖት ቅርሶችም ተዘርፈው ጦርነቱን ባርካ ላለጀመረችው ለቫቲካን (የሮማ ካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን) ተሰጥተዋል።

ማጠቃለያ

ቤተ ክርስቲያን ይህንን ሙሉ መከራ ትቀበል እንጂ ሀብቶቿን በልጆቿ ታታሪነት፣ በእግዚአብሔር ቸርነት ለዚህ ትውልድ አድርሳለች። ይህም ትውልድ አባቶቹ ያቆዩለትን መንፈላዊ ውርስ ጠብቆ የማስረከብ አደራ አለበት። ለዚህም በዘመናችን ያለውን ሁኔታ ጠንቅቆ መረዳቱ ተገቢ ስለሆነ ከ1933 ዓ.ም በኋላ ምን ተፈጠረ ለሚለው ጥያቄ ምላሽ ለመሥጠት መዛግብት አገላብጠን፣ የሚመለከታቸውን ጠይቀን መልሳችንን ሰንቀን እንቆያችኋለን። ለሁሉም የእግዚአብሔር ቸርነት፥ የድንግል ማርያም አማላጅነት አይለየን። አሜን።

ወስብሐት ለእግዚአብሔር

(ይቀጥላል)

ከዕርገት በኋላ

መድኀኒ ዓለም ኢየሱስ ክርስቶስ ከትንሣኤው እስከ ዕርገቱ ድረስ ለሐዋርያቱ እየታያቸውና (እየተገለጠላቸው) እያስተማራቸው ከቆየ በኋላ በአርባኛው ቀን እጁን በመጫን ባረካቸው። ሥልጣነ ክህነት ሰጣቸው። ጸጋአነትም ሾማቸው። መምህራን አደረጋቸው። በምስጋናም ፈጽሞ ወደ አልተለየው ወደ ባሕርይ አባቱ ዐረገ። በሥጋና በነፍስ፣ በእጥንትና በደም፣ በሥርና በጅማት፣ በፀጉርና በጽሕም እንዳለ በጥንት አነዋወሩ ተቀመጠ። ሥልጣናትም፣ ኃይላት፣ መናብርት፣ ሊቃናት፣ መኳንንት፣ አጋእዝት፣ መላእክት፣ ኪሩቤል፣ ሱራፌል፣ ሠራዊትም ሁሉ አንድ ሁነው ሕይወት ያላቸው ሕያዋን ሁሉ በሥውርም በግልጥም ያሉት የሆነውም የሚሆነውም በሰማይና በምድር ያለ መንፈስ ሁሉ ተገዛለት (1)

አስቀድሞም ለሐዋርያቱ «እናንተ ግን ከላይ ኃይል እስክትለብሱ ድረስ በኢየሩሳሌም ከተማ ቆዩ»(2) ብሎ ባዘዛቸው መሠረት ሐዋርያት ጸጋ መንፈስ ቅዱስ ከላይ ከአርያም እስኪሰጣቸው ድረስ በኢየሩሳሌም ጸኑ። በዐረገ በአሥረኛው ቀን በዓለ ሃምሳ (ፔንጤከንጤ) (3) ተብሎ በሚጠራው ዕለት ድንገት እንደሚነጥቅ ዓውሎ ነፋስ ከሰማይ ድምፅ መጣ። ተቀምጠው የነበሩበትንም ቤት ሁሉ ሞላው። ጸጋ መንፈስ ቅዱስ በእያንዳንዱ ላይ አደረ። በተለያየ ልሳን (ቋንቋ) መናገራቸውም ብዙዎችን አስደነቀ። (ቅዱስ ጴጥሮስ ከተለያየ ሀገር የእሽት በዓልን ለማክበር ለተሰሰቡት አይሁድ ስለ ጌታችንና መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የባሕርይ አምላክነትና አዳኝነት አስተማረ። በዚያች ቀን ሦስት ሺ ሰዎች አምነው ተጠመቁ። ይህች ዕለት የቤተ ክርስቲያን የልደት ቀን ትባላለች። (4)

በሐዋርያት እጅ የሚያስገርምና የሚያስደንቅ ብዙ ተአምራት ይደረግ ስለነበረ (5) ከዕለት ዕለት የምዕመናን ቁጥር ይበዛ ነበር። ስለዚህም ሐዋርያት ምእመኑን የሚያገለግሉ ሰባት ዲያቆናትን ሾሙ። እነርሱም በመልካም ተግባራቸው የተመሰከረላቸው ጸጋ መንፈስ ቅዱስን የተመሉ ነበሩ።

ሊቀ ዲያቆናት እስጢፋኖስ ጸጋንና ኃይልን ተሞልቶ በሕዝቡ መካከል ድንቅና ታላቅ ምልክትን ያደርግ ስለነበር አይሁድ በእርሱ ላይ ተነሡበት። ጥርሳቸውንም አፋጩበት። የአሪት ትምህርት አቢጋዝ የነበረው እስጢፋኖስ በእፍ በመጽሐፍ ስላልተቻለ አይሁድ በድንጋይ ወገሩው ገደሉት። (6)

ከቅዱስ እስጢፋኖስ ሞት በኋላ ስምንት ሺ ማኅበረ እስጢፋኖስ በየአቅጣጫው ተበተኑ። ወንጌልንም በብርታትና በፅናት ይሰብኩ ጀመረ። አይሁድ አንድ እስጢፋኖስን ከገጸ ምድር በማጥፋት ወንጌልን የሚያጠፉ መሰሉአቸው ነበር። ዳሩ ግን ይህ የመንፈስ ቅዱስ ሥራ ነውና በእስጢፋኖስ ሞት ምክንያት ወንጌል ይበልጥ ተስፋፋች።

የቤተ ክርስቲያን የንጋት ኮከብ የተባለ ቅዱስ ጳውሎስ ለወንጌል አገልግሎት በተአምር ተጠራ። የጌታን ደቀ መዛሙርት በየሑበት አሳስውል ባደሩበት አላሳድር እንዳላለ ሁሉ «በድካም አብዝቼ በመገረፍ አብዝቼ በመታሰር አትርፌ በሞት ብዙ ጊዜ ሆንሁ አይሁድ አንድ ሲንድል አርባ ግረፉት አምስት ጊዜ ገረፉኝ።...የቀረውንም ነገር ሳልቆጥር፣ ዕለት ዕለት የሚከብደኝ የአብያተ ክርስቲያናት ሁሉ አሳብ ነው» (7) ሊል በቃ። የመውጊያውን ብረት መቃወም የሚጎዳው ራሱን እንጂ ብረቱን አለመሆኑን ተረድቷልና። የክርስቶስ ተቃዋሚነቱን ትቶ ምርጥ ዕቃው ሆነ። ሊቁ እንደተናገረው በቅዱስ እስጢፋኖስ ጸሎት ቤተ ክርስቲያን የጠፋው ሳውልን አገኘች።

የሰናፍጭ ቅንጣት ወንጌል ስለተደቆሰች የአይሁድና የአሕዛብን የክሕደት አፍንጫ እየሰነፈጠች ግዛትዋን አስፋፋች። ከመካከለኛው ምሥራቅ ከኢየሩሳሌም አልፋ ጽንፍ እስከ ጽንፍ ደረሰች። የጌታ ደቀ መዛሙርት እየተባሉ ይጠሩ የነበሩ አማንያን በአንጾኪያ ለመጀመሪያ ጊዜ ክርስቲያኖች ተባሉ። የሐዋ.11፥26።

©ማኅበረ ቅዱሳን www.eotcmk.org

... ዝርወተ እስራኤል

ነገደ አይሁድ የሮም የቅኝ ገዣት ቀንበር ትካሽቸውን ሰላንበጠው እንደ ውኃ የጠግ ቸውን ነፃነት ለግተኛት የነፃ አውጪ ግንባር በጎቡዕ ግደራጀት ጀመሩ። ዳሩ ግን መደራ ጀታቸው የፈየደላቸው ነገር አልነበረም። እንዳውም «ደሙ በእኛና በልጆቻችን ላይ ይሁን»(8) እንዳሉት የጌታ ደም ደርሶባቸው አይሁድ ከሮማውያን ቄሳሮች ጋር ባደረጉት የመጨረሻ ጦርነት ጊዜ በገዛ አገራቸው ላይ አንድ ሚሊዮን ተኩል ያህል የሚሆኑ አይሁድ ታረዱ። ድል ያደረጋቸው ቄሣር አይደለም። ቄሣሩ ቲቶ የኢየሩሳሌምን ቅጥሮች አፈራረሰ፣ ቤተ መቅደሱ የተሠራበት ኮረብታ ከእሳቱ ቃጠሎ የተነሣ ሊፈነዳ የደረሰ እስኪመስል ድረስ ሁለተኛ ጊዜ በዘሩባቤል ዘመን የተሠራውን የእግዚአብሔርን ቤተ መቅደስ አቃጠለ (9)

ጌታችን በመዋዕለ ትምህርቱ ደቀ መዛ ሙርቱ የመቅደሱን ግንቦች ባሳዩት ጊዜ «ይህን ሁሉ ታያላችሁን? እውነት እውነት እላችኋለሁ ድንጋይ በድንጋይ ላይ ሳይፈርስ በዚህ አይቀርም» (10) ባላቸው በሠላሳ ሰባተኛው ዓመት ይህ ሆነ።

ድኅረ ልደተ ክርስቶስ ከ70 ዘመን በኋላ ሠላ እስራኤል በዓለም ሁሉ ላይ እንደ አፈር ተበተኑ። እንደ እህል ተዘሩ። ከዚህ ጊዜ ጀምሮ የክርስቲያኖች መናሸሪያ ኢየሩሳሌም መሆኗ ቀርቶ ሮም፣ እስክንድርያ፣ አንጾኪያ ሆኑ።

(ይቀጥላል)

መስቀሐት ለእግዚአብሔር

ዋቤ መጻሕፍት

1. የሐዋ.1፥1–5። 1ጴጥ.3፥22
2. ሉቃ.24፥49
3. ዘኍ.23፥15–22፤ የሐዋ.2፥1።
4. የሐዋ.2፥14–47፤ ዮሐንስ አፈወርቅ
5. የሐዋ.5፥12–16፤ የሐዋ.19፥11።
6. የሐዋ.7፥54–60።
7. 2ቆሮ.11፥23–29።
8. ማቴ.27፥25።
9. ታላላቅ ሃይማኖቶች እንዴት እንደ ተጀመሩ ገጽ 227
10. ማቴ.24፥2

ከአንባብያን...

ትሕትና በአባቶች አንደበት

- መድኅን ነው – ከሰይጣን አሸክላ ያድናልና (አባ እንጦንስ)
- የሰው ዘውድ ነው (አባ አሞን)
- ግማይናድ ደልዳላ መሬት ነው። (አባ ዲዶሮስ)
- ክርስቲያናዊ ምልክት ነው። (አባ መቃርስ)
- ከትሩፋት ሁሉ ይበልጣል። (አባ ባሞዋ)
- መስቀል ነው። (አባ ታድራ)
- የተባሕትዎ ጋሻ ጦር ነው። (አባ ቢሾይ)
- ግድግዳን የሚያስጌጥ የአፈር ወይዘር ነው። (አባ አጋቶን)
- የትሩፋት ግድግዳ ነው። (አባ አጋቶን)
- የባሕታውያን ፍፁምነት ነው። (አባ ጳኩሚስ)
- የመንግሥተ ሰማያት መመላለሻ በር (መግቢያ) ነው። (አባ ሚልኪ)
- ሕጸጽን የሚያስታውቅ መስተዋት ነው። (አባ ጳርዶ)
- የነፍሳት ወደብ ነው። (ዮሐንስ)
- የትሩፋት ወደብ ነው። (ዮሐንስ)
- የትሩፋት ሁሉ መረጻሚያ ነው። (አባ ሰራብዮን)
- የወንጌል ትእዛዝ መጀመሪያ ደገኛ ነው። (ዮሐንስ ሐፂር)
- ወደ ንጽሐ ልቡና ሰገነት የሚወጡባት ዕፀ ሕይወት ናት (አባ መቅራስ)
- የትሩፋት መጽኛ መሠረት ናት። (አባ ዛጥራ)
- የትሩፋት መታመኛ ናት። (አባ ኢሳይያስ)
- መሥዋዕት ነው። (ነቢዩ ዳዊት)

ቤካ መገርሣ (ከአሜሪካ)

ታሪክ አበው

እየረገጣችሁኝ ውጡ...

በአንድ አገር የሚኖር የምዕመናን አባት የሚሆን ኤጲስ ቆጶስ ጾር ተነስቶበት ሳለ «ቀድሰህ አቁርበን» አሉት። ‹ዛሬስ ተውኝ አይቻለኝም› ቢላቸው ግድ አሉት። ‹ግድግ ካላችሁኝ ቀድሼ አቁርቤአችሁ ሳበቃ ያልኋ ችሁን ታደርጋላችሁ?› አላቸው። ‹አዎን› አሉት። «እንኪያስ ይሁን» ብሎ ቀድሶ አቆረባቸው። በመጨረሻም «እንግዲህ እኔ ሳላሰናብታችሁ ሰው አይውጣ» ብሎ አስጠ በታቸው። ኋላ ጉዳዩን ፈጽሞ ወጥቶ ከመድ ረኩ ላይ በልቡ ተኝቶ «በሉ እያንዳንዳችሁ አቤቱ ኃጢአቴን ይቅር በለው እያላችሁ እየረ ገጣችሁኝ ውጡ አላቸው።» እየረገጡት ሲወጡ «...ስለ ትሕትናህ ኃጢአትህ ተሰር ዮልሃል» የሚል ድምፅ መጣለት። «ራሱን ከፍ የሚያደርግ ሁሉ ይዋረዳልና፣ ራሱን የሚያዋርድ ከፍ ይላል።» (ሉቃ.14፥11)።

- «ቅዱሳን በመለኮታዊ ግዕጠንት የተቀ ጣጠሉ ዕጣን ሲሆኑ የተቀጣጠሉትም በፈጣሪያቸው ፍቅር ነው።»

(ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ሺኖዳ 3ኛ)

ሥነ ግጥም

የአምላካችን ጥሪ – ይኸው ያስተጋባል፣
የተራራው ስብከት – አሁንም ይጣራል፣
ከኃጢአት ርቃችሁ – ኑ ወደእኔ ይላል።
በጣም ያዘናችሁ – ተሰብሮ ልባችሁ፣
ሁሉ የምታነቡ – ስለኃጢአታችሁ፣
ሰላም መጽናናትን – እርሱ እንዲያድላችሁ፣
ቅረቡ ወደጌታ – ወደፈጣሪያችሁ።

(አለነ ጌታሁን – ቫምቡ ሆስፒታል።)

ተዘጋጅተን እንኑር

በግይሆነን ሁሉ ስንል ወጣ ገባ፣
ያ ቀን ሳይመጣብን ሳናውቅ እንደሌባ፣
ተዘጋጅተን እንኑር ንስሐም እንግባ።
(እሸቱ ኃ/ማርያም – አዲስ አበባ)

ማስተዋልን ስጠኝ።

በኢምንት ዕውቀቴ አጉል ተራቅቄ፣
በፍልስፍና ክር ራሴን አንቄ፣
ጥቂት ጽፈ አንብቤ ብዙ እንዳልታበይ፣
ቃል ገብቼ ኖሬ እንዳልሆን ቃል አባይ፣
ለታይታ ብዬ ምንም እንዳልሠራ፣
ጥቂት ገንዘብ ሳገኝ ደርሼ እንዳልኮራ፣
የለበስኩኝ ዕለት ሰውን እንዳልጠላ፣
የልቤ ውዴታ ያን ጊዜ እንዳይላላ፣
የኃጢአቴን ድር ድሪቶውን ጥለህ፣
በደለኛ ልቤን በቃልህ አንጽተህ፣
ለአንተ የሚስማማ መልካም ሰው አድርገህ፣
ማስተዋልን ስጠኝ በእሸታህ ደግፈህ።

(ስንታየሁ ዓለማየሁ–አዲስ አበባ)

©ማኅበረ ቅዱሳን

ይህን መጽሔት ያለ ማኅበረ ቅዱሳን ፈቃድ በከፊልም ሆነ
በሙሉ ማሳተም ፣እንዲሁም በማንኛውም መልኩ
ለሽያጭ ማዋል በህግ የተከለከለ ነው።።